# ቅሌት

ከአንዳርጌ መስፍን

ነሐሴ 1986
አዲስ አበባ::

ስታሰር ጠያቂዬ፣ ስታመም አስታማሚዬ በመሆን ምንጊዜም ከጎኔ ለማትለየኝ እህቴ ለወይዘሪት ፀሀይቱ እማኙ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው::

ደራሲው


መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved.


ነሐሴ 1986
አዲስ አበባ::

# መግቢያ

ስለ ደርግ የሰቆቃ አገዛዝ አንድ መፅሃፍ መፃፍ እንዳለብኝ የተገነዘብኩት ለአራት አመታት በተለያዩ እስር ቤቶች አማቅቅ በነበረበት ወቅት ነው:: ጉግማንጉግ በሚል ርእስም አረቂቁን የነደፍኩት ከዚያው እስር ቤት እንዳለሁ ነበር:: ይሁን እንጂ ከእስር ቤት ከወጣሁ በኋላ ደርግ በህይወት እያለ እንደዚህ አይነት መፅሃፍ ማሳተም ስለማይቻል የደርግ ውድቀት እስከሚደርስ ድረስ ለአይኔ ትኩረትን፣ ለአእምሮዩ ጭንቀትን የሚፈጥሩትን እየመዘገብኩ ማስቀመጥ ያዝኩኝ::

ደርግ የፈለገውን ያህል ቢፎክርም በህዝቡ ዘንድ ከመወደድ ይልቅ መጠላትን፣ ከመከበር ይልቅ መዋረድንና መናቅን እያተረፈ መጣ:: የህዝብ ድጋፍና ፍቅር በማጣቱም ተንፈራጦ መቆየት አልቻለም:: እንዳንበሳ ባገሳባት አገር እንደ ውሻ ሙሆ በየአቅጣጫው ፈረጠጠ:: ከዚህ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ግልብጥብጥ አሉ:: ጦሩም ፍርክስክሱ ወጣ:: ኢህአዴግም ባሸናፊነት አዲስ አበባ ገባ:: እኔም ለመፃፍ ያቀድኩትን መፅሃፍ ከደርግ አስከሬን ላይ ለመቋጨት ወሰንኩ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከም/መ/አ እስከ ኮሎኔል ማእረግ ድረስ ያላችሁ ጃንሜዳ ከቀድሞው 1ኛ/ጦር መምሪያ እንድትከቱ ተብሎ በሬዲዮ ጥሪ በመተላለፉ እኔም "የደርግ ማእረግተኛ" ስለነበርኩ አብሬ ከተትኩኝ:: ይህ አጋጣሚ አዳዲስ ክስተቶችን እንዳይ አረዳኝ:: ከጃንሜዳ ወደ ሆለታ መጋዛችን ደግሞ የበለጠ እድሉን አሰፋልኝ::

ገነት ጦር ት/ቤት ለወር ያህል ስንቆይ የብዙዎቹ መኮንኖች መዝረክረክና ክብር ማጣት "ለካ እንደዚህ ኖረናል?" ብዬ እራሴን እንድጠይቅ አስገደደኝ:: የሚኒስትሮቹና የጀኔራሎቹ እጅ አሰጣጥም ህሊናዬን አቁስሎት ስለነበር በፊት እየፃፍኩ ካስቀመጥኩት ጋር እያይገር ለመፃፍ ሳስብ የሚጎዛዛብኝ መስሎ ታየኝና የበፊቱን አዘግይቼና እራሱን አስችየ ወቅታዊ የሆነ መጽሀፍ ለመፃፍ ወሰንኩኝ:: የበለጠ ያነሳሳኝ ደግሞ ከሆለታ ወደ ጦላይ ተጋፈን መወሰዳችን ነበር::

ለሶስት ቀናት ለተሃድሶ ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን፣ ከዚያ ደግሞ ወደ ጦላይ ጠራርገው ከወሰዱን በኋላ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር የተሃድሶ ትምህርቱን ያጓትቱት ጀመር:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በጥቅም በመከፋፈል አንድነታችንን አሳጥተው ውሻ እንደገባበት የዝንጀሮ መንጋ በታተኑን:: ከዚህ በኋላ በያዳራሾቹ ይታዩ የነበሩት ትርኢቶች እጅግ አሳፋሪዎች ነበሩ:: ለዚህም ነው እያሌ ቅሌቶችን በማየቴ የመፅሃፌን ርእስ ቅሌት ብዬ የሰየምኩት::

በወቅቱ የፕሬስ ነፃነት ስላልነበር ይህን ሁሉ ካጠናቀኩ በኋላ አስተይቤ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ለቅድመ ምርመራ /ሳንሱር/ አቅርቤ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲታተም ተፈቅዶልኝ ሳለ ማተሚያ ቤት ሳላስገባው በጠና በመታመሜ ምክንያት ስራው በመጓተቱ ስበሳጭ በሌሊት ከመኖሪያ ቤቴ ባፋኞች ታፈንኩኝ::

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለረጅም ጊዜ እየፃፍኩ ያጠራቀምኳቸው አንድ ሳይቀሩ ተለቃቅመው፣ ይኸው ቅሌት እራሱ ከኔው ጋር ለእስር ተዳረጉ::

ከእስር ቤት እስር ቤት ስዘዋወር ቆይቼ ከ10 ወራት በኋላ እኔ ስፈታ ፅሁፎቼ ግን ከኔ የከፉ ወንጀለኞች ሆነውም እንደሆን አላውቅም

በዚያው ሰጥመው ቀሩ። በተለይም ደም በደም የተሰኘው አረጅም ታሪካዊ ልብ ወለድ ፅሁፌ ምን ጊዜም ቢሆን የጎን ውጋት ሆኖብኝ ይኖራል። ቀሪ ስለሌለኝ መልሽ ለመፃፍ አልቻልኩም። የተወለደን ህፃን መልሶ እንደመፀነስ ይቆጠራል። ይህን ችግር ደራሲዎች ብቻ ናቸው ሊፈርዱኝ የሚችሉ።

ለአሳሪዎቼ ከመፈታቴ በፊትም ሆነ ከተፈታሁ በኋላ ፅሁፎቼን እንዲመልሱልኝ በፅሁፍም፣ በቃልም በተደጋጋሚ አመልክቼ ሳይሳካልኝ ቀርቷል።

ቅሌትን ግን ከስር ቤት እንደወጣሁ ያለና የጠፋ ንብረቴን ሳፈላልግ አረቂቅ የነደፍኩበትን ካልባሌ ቦታ ተወሽቆ በማግኘቴ እንደገና ጀምሬ እነሆ ከግብ ላደርሰው ችያለሁ።

እንግዲህ ዋና ዓላማዬ አንዱን ከቤ ሌላውን ለማዋረድ ወይንም የሌለ ታሪክ ዕፌ ስም ለማጥፋት አይደለም። ከኛ ውድቀት የነገው ትውልድ ትምህርት እንዲያገኝበት ማድረግ ነው። በተለይም በወያኒዎች እጅ ላይ ከወደቅን በኋላ ለጥቂት ጊዜ እራሳችንን መቆጣጠር አቅቶን እጅግ አሳፋሪ ድርጊቶችን ሰርተናል። በእርግጥ ቆፍጣና መኮንኖች የነበሩም ቢሆን አብዛኞቹ ተበሻቅጠው አበሻቅጠውናል። አገሪቱም የሞተችው ገና ከማለዳው ሀላፊነት በጎደላቸው ወመኔዎች እጅ የወደቀች እለት ነበር።

በወያኔዎች ጻዝ ባይነት አጋላጭና ተጋላጭ ጠላይ ሲተናነቁ ማየት የሚያሳፍርም፣ የሚያሳዝንም፣ የሚያስቅም ነበር። የበደለና የተበደለ ቢተናነቅ ባልከፋ ነበር። የሚገርመው ግን ትንሹ ዘራፊና ትልቁ ዘራፊ ርስበርሳቸው ሲናከሱ ማየታችን ነው።

እንግዲህ ወጣቱ ትውልድ ከዚህ ውርደት ምን ይማራል? በራሱ ተማምኖና ኮርቶ እንዲኖር ካሁኑ መዘጋጀት አለበት። ኢትዮጵያንም እንደ ጥንቷ የከራችና የታፈረች አገር ልናደርጋት የምንችለው ኩሩ ወጣቶችን ማፍራት ስንችል ብቻ ነው። አለበለዚያ ሁልጊዜም ጦርነት፣ ሁልጊዜም የጎሳ ሆያ ሆዬ የትም አያደርሰንም። ሁልጊዜም የሚሹት ከታሪካዊ ጠላቶቻችን የቤት ስራ ረሃብ ነው። ይህን ሆያሆዬ የሚሹት ከታሪካዊ ጠላቶቻችን የቤት ስራ የተቀበሉ ብቻ መሆን አለባቸው። ይህን ሴራ ማምከን ያለበት ወጣቱ ነው። የዛሬውን ሳይሆን ነገና ከነገ ወዲያ የሚከተለውን መዘዝ በመረዳት በሆደ ሰፊነት መቋቋም አለበት። አለበለዚያ ጎሰኞች ኢትዮጵያን ከማፈራረስ ወደኋላ አይሉም። ተልእኳቸው ነውና!

ቡተረፈ በፈለኩበት ጊዜ ባይደርስልኝም በህይወት ቆይቼ ዛሬ ይህን ዘገባ በማድረሴ ከፍተኛ እፎይታ አግኝቻለሁ። እንግዲህ ወደ ዋናው ፅሁፍ የምታደርስ ግጥም ጣል አድርጌ ልሰናበት።

ግብሩንም፣ታክሱንም ሁሉን ሲምሩት
እስራትን ብቻ ነው አንተውም ያሉት።
ደራሲው



# ምዕራፍ አንድ

«ባህያ ቀርበት የተሰራ ቤት
ብትንትን ይላል ጅብ የጮኸለት!»

## 1

አዲስ አበባና ዙሪያዋ በጭጋግ ተሸፍናለች። የሰውም ፊት ጨፍግጓል። መሽቶ የማይነጋ፣ነግቶ በሰላም የማይውል፣ ተውሎ የማይታደር አይመስልም። ሁሉም በደመነፍስ ወደየእለት ከስቡ ይንቀሳቀሳል። ሰላምታ በቅጡ የሚለዋወጥ የለም። ሁሉም በስጋት ተወጥሯል። የድል አጥቢያ አርበኞች፣የቀበሌ ጀግኖች፣የኢሰፓ ጀሌዎች የት እንደገቡ አይታወቅም። አምቦ ከተያዘች ወዲህ...

እለቱ ማክሰኞ ግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም. ነው። በስድስት ሰአቱ ዜና ቆራጡና ብልሁ መሪያችን፣ ጓድ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ሀይለማርያም፡-«ለኢትዮጵያ ደህንነት ሲባል ከስልጣን ወርደው ወደ ውጭ አገር ሄደዋል።» ባንድ የመንግስት ቃል አቀባይ ተገለፀ።

አብዮታዊ መሪያችን፡- «ከመሳሪያና ከሰው አንድ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ!» እንዳላሉ ሁሉ ዛሬ ፈረጠጡ!!

ይህን ዜና ስሰማ አንድ ነገር ትዝ አለኝና ወዝ የሌለው ሳቅ ሳኩኝ። ከሶስት አመት በፊት ዘመዶቼን ለመጠየቅ ወደ ትውልድ ቀበሌዩ ሄጄ ነበር። ታዲያ ኑሮ ከመረራቸው አዛውንት እንደ ዘበት እንዲት ግጥም ሰምቼ ነበር። ዛሬ እውን ሲሆን በጣም ገረመኝ፡-

«ፈረሱም ጓመረ፣ በሬውም አገሳ
ሊሮጥ ነው መሰለኝ ይኸ አህያ ፈሳ!»

በመንግስቱ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ሌ/ጀኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ሆነው እንደሚሰሩ ተነገረ። እርሳቸውም ከምሽቱ ሁለት ሰአት ለኢትዮጵያ ህዝብ የመማፀን ጥሪ አስተላለፉ። እንዳልካቸው መኮንን፣ "ፋታ!" ብሎ እንደነበረ ሁሉ እኚህም በሰፈሩት ቁና የመሰፈር አይነት «...ታሪክ በትናንትናው እለት ሀላፊነት ስለጣለብኝ እንጂ ስልጣን ፈላጊ ሆኜ አይደለም። ጊዜ ለመሻማትም አይደለም...» በማለት ወተወቱ። በዚሁ እለት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ማሰልጠኛ ጣቢያ እንዳሉ ላምስቱ ሀያላን መንግሥታት የመማፀን ጥሪ አስተላለፉ። በእጅጉ አሳዘኑኝ። ቆራጥ መሪ አለን ብለው ትምህርታቸውን አቋርጠው አገርን ከደጋ ለማዳን ፈጥነው ለመድረስ ነበር ጥሪታቸው ። ታዲያ ምን ይሆናል አብዮታዊ መሪያችን የውሃ ላይ ኩበት አድርገዋቸው ሄዱ። ደግሞኮ እነሱን ላነጋግር ብለው ነው የሄዱት!

ግንቦት 15 ቀን ሀሙስ የሌኒን ሀውልት ተገነደሰ! በዚሁ እለት ባዲስ አበባ አናት ካራት ሰአት ጀምሮ ቀስተ ዳመና ቀለበት ሰርቶ ታየ።

ብዙ አባውንቶች የየግል ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል:: አንዳንዶቹ "ቀለበት
ሰርቶ በባንዲራችን ተመስሎ የታየን አምላካችን ሲታረቀን ነው" ሲሉ
ሌሎች ደግሞ "የጦርነት ምልክት ነው:: ባንዲራ ቀዳጅ ወራሪ
መምጣቱን ማሳየቱ ነው" በማለት ተንበየዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሞት
ባዲስ አበባ አናት ላይ ክንፉን ዘርግቶ ያዛጋል፤ ዋጥ ስልቅጥ
ለማድረግ:: የሲኦል በሮችም ተከፍተዋል:: በሀጢአት የጎደፉ ነፍሳትን
ለማስተናገድ!

አርብ፣ ግንቦት 16 ቀን አዲስ አበባ አርሁብ በጎዳቸው፣ ውሃ
ተጥለቀለቀች::
ጥም ባቃጠላቸው፣ መሪ ባጡ ቅጠልያ ለባሾች
ወታደሮቹ አዲስ አበባ እንደ ዝጡ ዘረፉ አላካሄዱም:: በስርአት እንዱ
በሄደበት ሌላው በመከተል መስመር ይዘው ነው የሚጓዙት፣ የጦር
ትጥቃቸውን ክርችም አድርገው እንደ ታጠቁ ናቸው:: መሪ ግን
የላቸውም:: እስበሳቸው እየተማሩ ወደ ምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያና
ወደ ማስተናገጃ ዋና ክፍል ይተማሉ፤ ምግብና ማረፊያ እንዲሰጣቸው
ለመጠየቅ:: ተቀባይ ግን አላገኙም:: እነ ጓድ ጄኔራል የሉም::
በየሸርንቁላው አድፍጠዋል:: ለካም አገሬን እወዳለሁ ማለት በቀን ላይ
ኖሯል:: ከዚያ ሁሉ የደርግ ጄኔራል አንድ እንኳን ቆራጥ አስተባባሪ
ጠፋ:: ከዚህ በኋላ ወታደሮቹ የትም ተበተኑ::

ሰራዊቱ ፈቃጅ አጥቶ የትም ሲባዝን ለከፋ ችግር እየተጋለጠ
መጣ:: ሌላ ምርጫ አልነበረውም፤ የጦር መሳሪያውን ቸበቸበው::
ቢኬሎም መትረየሶች እስከነ እንግታቸው በቀላል ገንዘብ በነጋዴዎች እጅ
ገቡ:: ክላሽ ጠመንጃዎች ባሮጌ ልብሶችና በእለት እንጀራ ተለወጡ::
ፕላስቲክ ቦምቦች እንደ ከረሚላ በህፃናት እጅ ተበተኑ::

ግንቦት 19 ቀን ሰኞ የክተት ጥሪው ተነሳ:: ይህ ሁሉ ሲሆን
አዲስ አበባ ከተማ የሞት ጥላ እንደጣለባት ነበረች::

## 2

"አብዮታዊ" መሪያችን ወደ ውጭ አገር ከፈረጠጡበት እለት
ጀምሮ አዲስ አበባ የመረጋጋት ሁኔታ አይታይባትም:: በተለይም ካስራ
ሁለት ሰአት በኋላ አውራ ጎዳናዎች ጭር ይላሉ:: ተባራሪ አግሬኞች
ብቻ እየተገላመጡ ወደ ላይ ወደ ታች ይጣደፋሉ::

ከሀሙስ ወዲህ ተኩስ እንደ ቀለጠ ያድራል:: መትረየስ
እንዳጓራ፣የክላሽ ጥይት እንደ ፈንድሻ እንደተንጣጣ ይነጋል::
የሚገርመው ግን ጧት ሁሉም ያገኘውን ቀምሶ ወደየእለት ተግባሩ
ይሰማራል:: ከነጋ በኋላ የተኩስ ድምፅ ሳይሰማ አረጭ ብሎ ይውላል::
ተኳሾቹ እነማን እንደ ሆኑ በውል ባይታወቅም ሁለት አይነት ግምቶች
አሉ::

1ኛ. የጦሩ መሳሪያ በግለሰቦች እጅ ስለገባ ለመሞከር
ነው የሚሉ ነበሩ::
2ኛ. ወያኔዎች ከጦሩ ጋር ተቀላቅለው በመግባት
ሽብር ለመፍጠር ነው የሚሉም አልጠፉም::



ፀውጭው አለም ደግሞ አዲስ አበባ ደም ባህር ልትዋኝ ነው
እየተባለ ይሟረትባታል:: እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱትም ሞቃዲሾና
ሞናሮቢያ ናቸው:: ያዲስ አበባ ህዝብ ግን ሲነጋ ቁርሱን በልቶ ወደ
መደበኛ ስራው ደፋ ቀና ይላል::

ሰኞን በምጥ ውለን ማታ በሁለት ሰአት ሌ/ጄኔራል ተስፋዬ
ገ/ኪዳን ጦሩ ትጥቁን እንዲፈታ ጥሪ ካስተላለፉ በኋላ ሌ/ጄኔራል ሀዲስ
ተድላን፣ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህንና አቶ ሀይሉ ይመኑን አስከትለው
ጣሊያን ኤምባሲ የሙጥኝ አሉ:: ጦሩ ግን አመራር አጥቶ እረኛ እንደ
ሌለው መንጋ የትም ተበትኖ ቀረ::

# ምእራፍ ሁለት

«እንኳን አሁንና ሙሉ ትጥቅ እያለን፣
በጦር በጎራዴ ታንክ እንማርካለን!»

## 3

ሰኞ ሌሊት እንደ መሰንበቻው ሁሉ አዲስ አበባ በተኩስ
ስትናወጥ ነው ያደረችው:: እንዳይነጋ የለም ጨለማው ተገፎ በብርሃን
ተተካ:: እለቱም ማክሰኞ ቀኑ ግንቦት 20 ነው:: የማማ ልኬ ድምፅ
እንደ ተኛሁ ይሰማኛል:: ከቤት አደጅ ወጣ ገባ እያሉ ነው
የሚነጋገሩት::

"ኧረ አባክህ አምላኬ ሰላሙን ላክልን" እያሉ ይማፀናሉ::
የሰሞኑ ፀሎታቸው ይኸው ነው:: ከግንቦት 13 ቀን ወዲህ ክፉኛ
ተሸብረዋል:: በርግጥ እሳቸው ብቻ አይደሉም፤ ጠቅላላ ያዲስ አበባ
ህዝብ በሽብር ተውጧል::

እማማ ልኬ እኔ ተጠግቼ የምኖርባቸው አባውንት ናቸው::
ከርሳቸው ቤት ተከራይቼ ጣሊያን ሰፈር መኖር ከጀመርኩ ድፍን አራት
አመታት አስቆጥሬአለሁ:: ተግባብተን እናትና ልጅ ሆነን እንኖራለን::

ከመኝታዬ ሳልነሳ ከራስጌዬ ያለውን ሬዲዮ ስከፍተው መደበኛ
ፕሮግራሙን በማስተላለፍ ላይ ነው:: ከዜና በኋላም ከፕሮፌሰር መስፍን
ወ/ማርያም ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ ማስተላለፍ ቀጠለ::
ተረጋጋሁኝ:: ወያኔዎች ገብተው ያድራሉ የሚል ግምት ነበረኝ:: አቃቂ፣
ሰበታ፣ ሰንዳፋ፣ ጫንጮ፣ ሆለታ በአጠቃላይ ባዲስ አበባ ዙሪያ ባሉት
ትንንሽ ከተሞች መግባታቸውን ገና በግዜ ሰምቼ ነበር:: ታዲያ እንዴት
ዘገዩ? የሚያደናቅፋቸው ነገር እንኳን የለም:: ሁሉም ነገር
ተመቻችቶላቸዋል:: ጦሩም ትጥቁን ፈቷል:: በዚህ ሀሳብ ላይ
እየዋለልኩ እንዳለሁ:-

«የዘመናት ህዝባችን ብሶት የወለደው ጀግናው የኢህአዲግ ሰራዊት ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን ያዲስ አበባን ሬዲዮ ጣቢያ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል! ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም.» እየደጋገመ አስተጋባ:: በመገረም አይነት እንደ ተጋደምኩ ፈገግ አልኩኝ!

ልብሴን ለባብሼ ከመኝታ ቤቴ ብቅ ስል፡- "የት ትሄድ ጎርፉ? ኧረ እርፊህ ተቀመጥ ልጅ" አሉኝ እማማ ልኬ:: ቀይ ድርፍዋጫ ፊታቸው ተከፍቶ::

"ወጣ ብዬ አካባቢውን ልቃኘው እንጅ፤ መቸስ ተኝቼ አልውል" አልኳቸው::

"ምን የሚቃኝ ነገር አለ? ወያኔዎች ገብተዋል:: ሬዲዮ ጣቢያውን ሁሉ ይዘውታል" አሉኝ:: መልስ ሳልሰጣቸው ፊቴን ተጣጥባቤ፤ ፀጉሬን እንደ ነገሩ አበጣጥሬ ከቤት ወጣ ስል ፀሀይዋ ሞቅ ብላለች:: እማማ ልኬ ከቤታቸው በር ቆመው እግድም ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሳልፍ አትኩረው ያዩኝ ነበር::

ወደ ዋናው ጎዳና የሚያዘልቀውን መንገድ ይዤ ብቅ ስል ከታች በኩል ህፃናት፣ወጣቶች፣ ሴቶች ሽቅብ ወደ ሬዲዮ ጣቢያው ይጎርፋሉ:: ቤተመንግስት አካባቢ የቀለጠ ተኩስ ይሰማኛል እንጅ በተረፈ አዲስ አበባ በመጠኑ እረጭ ብላለች::

አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት አካባቢ፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ያጥሩ ዙሪያና ማዘጋጃ ቤት በህዝብ ተከቧል:: ይኸ ሁሉ ግርግርና ትርምስ ወያኔዎችን ለማየት ነው:: አንዳንዶቹ በትግርኛ ያነጋግሯቸዋል:: የቀረው ደግሞ ከቦ ለጉድ ያያቸዋል:: እነሱ ያለምንም ስጋት ግማሾቹ ቁጭ ብለዋል:: ግማሾቹ ደግሞ ጋደም ብለው በኩራት በአይናቻቸው ወዲህና ወዲያ ይማትራሉ:: እየተዘዋወርኩ ደህና አድርጌ አጤንኳቸው:: መቅረፀ ድምፅና ፎቶ ማንሻ አለመያዜ እንጅ ጉብኝቴስ ልክ እንደ አንድ ጋዜጠኛ ነበር::

ፊታቸው በፀሀይና በቁር ተፍረግርጓል:: እንደ ማገኛውም የስሚን ህዝብ መጣጣ ናቸው:: አብዛኞቹ ከሰውነታቸው ጥብቅ ያለች ቁምጣ ሱሪ ነው የታጠቁት:: ጎፈሪያቸው እውነትም ፋና አስመስሏቸዋል:: ጫማቸው በዘልማድ ኮንጎ ወይንም ሰንደል ጫማ እያልን የምንጠራው ነው:: ፎጣ ከራሳቸው ጠምጥመዋል:: ሌላ ቅራቅንቦ የላቸውም:: የነፍስ ወከፍ በምቦች በወገባቸው በክረጀ ነገር ከተው ታጥቀዋል:: ካንዳንዶቹ በስተቀር ጉርድ ክላሽ ጠመንጃ ነው የያዙት::

የሴት ወታደሮችም አሉ:: መልክ የሚባል የላቸውም:: የወንድን ልጅ ቀልብ አይስቡም:: የሴት ወታደሮቹን ላይ ግን አንድ አይነት እልህ ተናነቀኝ:: አንደኛዋንማ ስጉድ ነበር አትኩሬ ያየኋት:: ብቻዋን ፈንጠር ብላ ተቀምጣለች:: እንደኔው ከበው በመቆም የሚያይዋት ብዙ ናቸው:: የድካም ምልክት ይታይባታል:: ክላሿን ትራስ አድርጋ በጀርባዋ ተጋደመች:: ከዚያ አገርግሬን የቆምነው ሳቅን::

"ምነው?" አለችን ፈገግ ብላ::

"ምንም" አልናት:: ከዚህ በኋላ ከዚያ ግድም አልተገኘሁም:: ሁኔታዎችን ሁሉ መለስ ብዬ ሳስባቸው ወደ ቤቴ ተመለስኩ:: ብቻየን እየተንከተከትኩ እስቃለሁ:: ያንዘበዝቡኝ ጀመር::



ሴቷ አንኳን ቆጭቷት ቀሚሷን አውልቃ ሱሪ ስትታጠቅ፣
የደርግ ጀኔራሎች ሱሪያቸውን ጥለው አደፈጡ እንደ ቆቅ!

አንጆቴ እርር ሲል የቋጨሁት ግጥም ነበር::
«በመራራው ትግላችን እናሸንፋለን!!» እንዲህ አድርጎም መራራ ትግል የለ!
አሁን በቅርቡ በኑዛዜ ቃላቸው «ህዝቡ ሲደማ እደማለሁ፤ ህዝቡ ሲቆስል እቆስላለሁ፤...» ብለው ነበር! ምን አይነት አታላይ ኖረዋል?

ላመል ያህል በሩን አንኳኩቼ ሹክክ ብዬ ስገባ እማማ ልኬ ከድብዳባቸው ላይ ቁጭ ብለው አቦል ቡና ብቻቸውን ይጠጣሉ:: ይኸው ናቸው:: ቡና ከጎረቤት ሴቶች ጋር መጠጣት አይወዱም:: «ትርፉ ሰው ማማት ነው» ይላሉ::

"የት ደርሰህ መጣህ?" አሉኝ፡- ቡናቸውን ፉት እያሉ::

"ወያኔዎቹን አይቻቸው መጣሁ" አልኳቸው::

"ምን ይመስላሉ?" አሉኝ፡-ወደኔ አንጋጠው እያዩ::

"ለነገሩማ የኛው ሰዎች ናቸው" ስላቸው፡-

"እሰይ! እስቲ የኛው ሰዎች ያድርጋቸው" አሉ::

ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁና ጫማዬን አውልቄ ካልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተንጋለልኩኝ:: በቃ ወደ ደጅ ሳልወጣ እንደ ተጋደምኩ ዋልኩ::

ሌሊት ደግሞ ያን አሮጌ ቤት ነፋሱ ያንቋቋው ጀመር:: የግንቦት ነፋስ ይኸው ነው:: እማማ ልኬ ግን የነፋሱ ብርታት ክፉኛ አስፈርቷቸዋል:: መብራቱን አስርዬ እያበሩ፡-

"ኧረ ምንድን ነው መቶ አለቃ ጎርፉ?"

"ነፋስ ነው እማማ ልኬ! እርፊው ይተኙ::"

"የምን ነፋስ? ጣራ የሚደረምስ! ኧረ የሰው ኮቴ ይሰማኛል!"

"አይዞዎት ነፋስ ነው::"

"አይዞዎት ትለኛለህ እንዴ!" አጉተመተሙ:: ወዲያው ደግሞ ድመቶች በጣራው ላይ ድድድ...! ብለው እየተዛለሉ ሮጡ:: ተኩሱም ልክ እንደመስንበቻው ይቀደዳል::

"ኧረው!" አሉ::

"ምነካዎ! እማማ ልኬ? ድመቶችኮ ናቸው!"

"ምነው ልኬ! 'ድመቶች' ትለኛለህ እንዴ! " ተቆጡ:: ድመቶቹ እንደገና በጣራው ላይ እየተሯሯጡ መጥተው 'ሚያው!' ብለው ድምፃቸውን ባያሰሙ ኖሮ እማማ ልኬ ኡኡታቸውን ይለቁት ነበር:: ዝም ብለው አዳመጧቸውና፡-

"ቀልብ ገፋፊዎች!" አሉአቸው::

ለትንሽ ጊዜ ዝም ብለው ቆይተው፣ "መቶ አለቃ ጎርፉ! እንቅልፍ ወሰደህ እንዴ?" አሉኝ:: ደግሞኮ እስከ ዛሬ ድረስ በማእረጌ ጠርተውኝ አያውቁም:: በጭራሽ ሊያስተኙኝ አልቻሉም::

"ኧረ አልወሰደኝም" አልኳቸው::

"ተኩሱ ይሰማሃል?"

"ይሰማኛል::"

"ተገቡ በኋላ ደግሞ ምን አድርጉ ነው የሚሉን?" አሉኝ። ዝም አልኳቸው። እንቅልፍ ሳይወስዳቸው እንዲሁ አነጉ።

# 4

"አንተ ጎርፉ፤ምንድን ነው የቤቱን ጣሪያ ሲነቀንቀው ያደረው?" አሉኝ ጧት ከመኝታ ቤቴ ስወጣ።

"ነፋስ ነው እማማ ልኬ።"

"ነፋስ እንኳን አይደለም። ደግሞስ ተገቡ በኋላ የምን ተኩስ ነው? እንደ ዶፍ ነው ሲወርድ ያደረው።"

ቁርሴን በልቼ እንዳበቃሁ አክስቴን ለመጠየቅ ተነሳሁ። አይኗን ካየሁት ሰንበት ብያለሁ። ደግሞ ዘመድም የሚጠየቀው በእንዲህ ያለ ወቅት ነው።

"ወዴት ልትሄድ ነው ልጄ አርፋችሁ ተቀመጡ እየተባለ።"

"በቅሎ ቤት ሄጄ አክስቴን እስቲ ልጠይቃት።"

"ወዳክስትህ ከሆነስ ደግ" አሉኝ።

ከሰፈሬ ወጥቼ ወደ ዋናው መንገድ ስገሰግስ አክስቴ ባለፈው "አብዮታዊ መሪያችን" የፈረጠጡ እለት ስልክ ደውላ እየሳቀች ያነጋገረችኝ ትዝ አለኝ።

"ሀሎ! አንተ፣ ጎርፉ..." እኔ መልስ እስከምሰጣት ድረስ እንኳን አልጠበቀችም። እየተጣደፈች፣ "ሳልሳዊ ቴዎድሮስ ጉድ አድርጎን ፈረጠጠ አይደል!" የቁጭት ሳቅ ሳቀች።

"ምን ታደርጊዋለሽ። እኔን ያሳዘኑኝ አሽቃባጮቹ ናቸው። 'ብልሁ፣ አስተዋዩ፣ ቆራጡ መሪያችን!' እያሉ ሲወሸክቱ የነበሩት" አልኳት።

"ማሽቃበጥማ በዘመኑ ደርግ ማን ያላሽቃበጠ አለ ብለህ ነው። ሌላው ቢቀር ህይወትን ለማቆየት ሲባል፤ እንዲያው ግን አይገርምህም? እነጎሹን፣ እነዳዊትን ...ኧረ ስንቶቹን 'ከሀዲዎች! የኢፔሪያሊዝም ቅጥረኞች!' እያለ እንዳልወሸከተ ሁሉ ዛሬ እንዳህያ ውርንጭላ ጭራውን ሰቅሎ ይፈርጥጥ! ቅሌት! " ስትለኝ አንድ ተረት ትዝ አለኝና፡-

"እትዬ ሰናይት፤ አንድ ተረት ልንገርሽ። ይቅርታ ግን በስልክ ብዙ ቆየን" አልኳት ተረቱን መፈለግ አለመፈለጓን ለማረጋገጥ።

"ቁም ነገርም አይደል የምናወራው? በል ንገረኝ።"

"እይውልሽ፤ እንስሳት ሁሉ ተሰብስበው አለቃ እንምረጥ አሉና በድምፁ ማማር ተማርከው አህያን 'አንተ አለቃ ሁነን' ብለው መረጡት" ስላት፡-

"እሽ" አለችኝ ለመስማት በመጓጓት።

"ቡላ ሆዬ ባለቅነቱ እየተኩራራ ለጥቂት ጊዜ ደህና የሚያገለግል ሲመስልልሽ ጊዜ እንዴት እንዴት ያለው ኮርማ በሬ ያሸረግድለት ጀመር። በይህ ጊዜ ቡላ የልብ ልብ ተሰማውና ኮርማውንም፣



ወይፈኑንም፣ ጥጃውንም፣ ጊደሩንም... እንዲያው ያገኘውን ሁሉ ትንሽ ትልቅ ሳይለይ በርግጫ እያፈረጠ ይጥለው ጀመር። እንስሳቱ ሁሉ የሚያደርጉት ቢያጡ ከርግጫው ለመሸሽ ወደ ጫካ ገቡ። ግማሾቹ ደግሞ እየተሰባበሩ ወደቁ። የዚህ ጡር የተራበ ጅብ ከጫካ ብቅ ይልልሻል።"

"እሰይ! በዘረገፈው!" አለች።

"ቡላ ሆዬ የጅቡን ድምፅ ሲሰማ ፈሱን እንዝርጦ እግሬ አውጭኝ ይላል!" ስላት ሳታቋርጥ ሳቅ ፍንቅል አደረጋት። ፀጥ ብዬ ሳቋን እስክትጨርስ ድረስ የስልኩን እጀታ ከጆሮዮ ለግቼ ጠበኳት።

"ሀሎ! አንተ! ይዝጋህና! ምነው ይህን የመሰለ ተረት እስከዛሬ ሳታጫውተኝ?" አለችኝ።

"በምን አስታውሽ ልንገርሽ? መንስኤ መኖር አለበት። 'ቴዎድሮስ ነኝ፤ ያንበሳው ክፍለ ጦር አባል ነኝ' እያለ ይደነፋል! አሽቃባጮች ተቀብለው 'ቆራጡ መሪያችን' እያሉ ሰማይ ላይ ሲሰቅሉት ልቡ በእብሪት አብጦ፡- 'አድሃሪያንን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም በቁጥጥራችን ስር እናደርጋለን!' እያለ ሌት ከቀን ደነፋ። ተፈጥሮም በድርቅ አንበርግባ በቁጥጥሯ ስር አደረገችን። አድሃሪያን የሚላቸውም ይኸውና አስፈረጠጡት!"

"አፈር ይብላና! ምናለ ጀኔራሎቹን ይዞ አልሆንለት ቢል እንኳን እንደ ሲያድባሬ ባገሩ ጫካ ገብቶ ትንሽ ቢያደፍጥ? ወይንም እንደ ሳሙኤል ዶ ከታማኝ ወታደሮቹ ጋር ሆኖ የክብር ሞት ቢሞት። ብስብስ!" አለችው።

"ይህን ሁሉ ማድረግ የሚቻለው አእምሮ ሲኖር ነው። ደርጎች ደግሞ ለዚህ የታደሉ አይደሉም። አነሳሳቸው አስገራሚ እንደ ሆነ ሁሉ አወዳደቃቸውም አስቂኝ ነው። 'ጀኔራሎቹን ይዞ' ብትይኝ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። እየውልሽ፤ እኔ ምክትል መቶ አለቃ ሳለሁ አስር አለቃ የነበሩ ሁለት የደርግ አባላት ዛሬ ለጀኔራልነት ማእረግ በቅተዋል። የሚገርምሽ ደግሞ ሁለቱም በአዋሳ በኩል ሲፈረጥጡ አንዱ ተገደለ፤ ሁለተኛው በፀና ቆስሎ ተያዘ። ታዲያ ከነዚህ ጋር ቢሸፍት ምን ሊፈይድ? ያው የገበሬ ቤት ያቃጥሉና ይዘርፉ እንደሆን እንጅ።"

"እሱስ እውነትክን ነው፤ የገበሬ ቤት ከመዝረፍ አያልፉም። ለነገሩማ ከትግራይ ተነስተው ከዚህ እስከሚደርሱ ድረስ እሱ ሚኒስትሮቹን ይዞ በምእራብ ኢትዮጵያ ወርቅ ይሰበስብ አልነበረም?"

"በይ እትዬ ሰናይት! ሲመችኝ ብቅ እላለሁ" ብያት ነበር በስልክ የተለያየነው።

አክስቴ ያኔ በስልክ ያለችኝን እያሰላሰልኩ ቸርችል ጎዳና በመግባት ቁልቁል ተዳፋሁ። መኪና የሚባል ነገር ጨርሶ የለም። ለካም አዲስ አበባን የሚያደምቃት መኪና ኖሯል። ጎዳናው ጭር ብሏል። እግረኞች ብቻ ወደላይ ወደታች በርጋታ ይንቀሳቀሳሉ።

ቴዎድሮስ አደባባይ ስደርስ ከኋላዬ መንጋ በቅሎ እየተንጋጋ ደረሰብኝ። ህፃናት፣ ወጣቶች ከኋላ እየተከተሉ እንደ ብርቅና ድንቅ ያዩዋቸዋል። ወደ ዳር ወጣ ብዬ አስቀደምኳቸው። ባልቆጥራቸውም ወደ ሰባና ሰማኒያ ይጠጋሉ።

"ወይ ቸርችል ጎዳና! ዲኤክስና ማርቸዲስ መኪና እንዳልተርመሰመሰብሽ ሁሉ ዛሬ በቅሎ ፋንድያውን እያንጠባጠበ ይንጋጋብሽ ጀመር" አልኩኝ በመገረም::

ልጆቹ እየተንጫጩ ይከተሏቸዋል:: ሁለት የኢህአዲግ ወታደሮች ይነዷቸዋል:: እነሱም መሳሪያ በመያዛቸው እንጂ እረኞች ናቸው:: በመንገድና በጭነት ስለተንገላቱ የብዙዎቹ ጀርባ ተገጥቧል:: ግራና ቀኝ በጎዳናው ዳር ዳር ያለው ህዝብ እነሱን እያየ ይስቃል:: ያንዳንዶቹ ሳቅ ግን «ማሽላ ሲያር ይስቃል» የሚባለው አይነት ነው:: አንድ አዛውንት ያሉት ግን ምንጊዜም አይረሳኝም:-

"እነዚህ ናቸው የመንግሥቱ ሀይለማርያምን ታንክና መድፍ አንጋግተው ካገር ያስፈረጠጡት? ትፍ! " ብለው በቁጣ እየተፈናጠሩ አቆልቁለው ሄዱ:: እኔም እየተወራጨሁ ተከተልኳቸው::

ለካም ጨዋታም የሚጥመው አገር ሰላም ሲሆን ነው:: ካክስቴ ጋር ይህን ያህል የጣመ ጨዋታ አልተጫወትንም:: ብናነሳው፣ ብንጥለው ያው ስለ ጦሩ መፈረካከስና ስለ "አብዮታዊ መሪያችን" መፈርጠጥ ነው::

"ይገርምሀል! ለካ ደርግ ውስጡ ባዶ ኖሯል? ያለነገር ምላስ አላበዛም" አለችኝ::

"ለባዶነቱማ ምን አንድና ሁለት አለው:: እውቅ ጀኔራሎችን አርዶ ጨርሶ ጦሩን ያለመሪ አስቀርቶ የንቧይ ካብ ሲክብ ኖሮ ባንድ ጊዜ ሲናድ እግሬ አውጭኝ አለ::"

"ኧረ አንዳንድ ጊዜስ እነዚህ ወያኔዎች ደግ አደረጉ:: ይህ ቅርንጫፍ! ጥግብ ብሎብን ነበር::"

"እረስቼ ሳልነግርሽ፤ ቅድም ወዳንቾ ስመጣ መንጋ በቅሎዎች አይቼ ስስቅ ነበር::"

"የምን በቅሎዎች ናቸው?"

"የወያኔ በቅሎዎች ናቸው:: ስንቃቸውንና መሳሪያቸውን ጭነው ያመጡባቸው::"

"አንተ ሆየ፤ ታንኩን፣ መድፉን፣ ጀቱን ይዛችሁ በበቅሎ በተጫነ መሳሪያ ነው የተሸነፋችሁት? ወታደሮቹንም አየኋቸው፤ ከዚህ ታች ከባንኩ ሲጠብቁ:: ጭብጥ ያሉና ርሃብ የጎዳቸው ናቸው:: ፀጉራቸው ብቻ የተንጨፈረረ:: እንዲያው ያ-ዘብጣጣ ዘብጣጣ የደርግ ወታደር ሁሉ የት ደረሰ?" ስትል በመገረም ጠየቀችኝ::

"አሁንኮ ተናግረሽዋል እትየ ሰናይት:: ደርግ ባዶ ጉራ ወናፍ ነው! ጦሩን ማን ይምራው? ሰውኮ የለም:: ስዎቹን ቀደም አድርገው ጨርሰዋቸዋል::"

"አዎን ልጄ፤ አርደው ጨርሰዋቸዋል" አለችኝ:- አንገቷን በሀዘን ዘንበል አድርጋ::"

የሚጥመን ባናገኝም ካክስቴ ጋር ስንጫወት ውለን ወደ ማታ ቤቴ ተመለስኩ:: አሁንም መኪና አልነበረም:: ጥሩ እስፖርት ነው:: ከበቅሎ ቤት ጣሊያን ሰፈር ድረስ በግር ደርሶ መልስ፤ እቀበቱን ተጋተርኩት...



# 5

«ግርም ያደርገኛል የኢትዮጵያ ሁኔታ፣
አሳሪ ሲታሰር ታሳሪው ሲፈታ፣
ከትከት ብላ ሳቀች አለም ጥርስ አውጥታ!»

ብሎ ነበር አንድ አቅራሪ በ66 ዓ.ም. የሀይለስላሴ ባለስልጣኖች ተጋፈው ሲታሰሩና ያላግባብ የታሰሩት ደግሞ ሲፈቱ:: ባስራ ሰባተኛ አመቷ ደግሞ ታሪክ እራሷን ደገመች:: የደርግ ባለስልጣኖችም እየተለቀሙ ይታሰሩ ጀመር::

የኢሰፓ የፖሊት ቢሮ አባልና የትግራይ እራስ ገዝ አስተዳዳሪ የነበረው ጓድ ሻምበል ለገሰ አስፋው ለሁለተኛ ጊዜ ተያዘ:: ሻምበል ለገሰ አስፋው ለብዙ ንፁሀን ደም መፍሰስና ለበርካታ ምሁራን መሰደድ ምክንያት የሆነ ግለሰብ ነበር:: ለኢትዮጵያ ውድቀትም አንዱና ዋናው ተጠያቂ ሰው ነው:: ሌላው ቢቀር እንኳን ትግራይን ባይሾምና ፈርጥጦ ባይመጣ ኖሮ የዛሬው መፈረካከስ ባልደረሰ ነበር:: የውሻ ደም የማያስቀረው እምላክ ወገቡን እንደ ተመታ እባብ አጥመልምሎ አጥመልምሎ ከወያኔዎች እጅ ላይ ጣለው::

«ጓድ ሻምበል ለገሰ አስፋው» በመጀመሪያ ኢህአዲግ አዲስ አበባ ከመግባቱ በፊት በሰበታ በኩል ሊሾልክ ሲል የ14ኛ ክፍለ ጦር ባልደረቦች ናቸው የያዙት:: ከዚያ ወደ ማእከላዊ እስር ቤት ተወስዶ ይታጎራል:: ኢህአዲግ አዲስ አበባ ሲገባ ደግሞ እንደማንኛውም እስረኛ ይለቀቃል:: ለጌ ሆዬ ወደ ዮሃንስ አካባቢ እንደ ሰባራ አህያ ሲጥመለመል ከወያኔዎች እጅ ይገባል:: እያጣደፉ በመውሰድ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ከበሩ ላይ ገትረውት ዋሉ፤ ህዝቡ እንዲያየው:: በርግጥም መሳለቂያ ሆኖ ዋለ:: 'የሞተ ሰው ምንፈቀደኝ!' ያሰኛል:: በፍዋለለባት አገር፣በፈነጨባት ከተማ እንደዝንጀሮ ቡጫሌ ተቆጥሮ የህፃናት መጫወቻ፣ያዛውንቶች መዘባበቻ ሆነ::

ጓድ ለገሰ አስፋው ትግራይን የተሿመ እለት ህዝቡ ጉድ ብሎ ስለነበር እኔም አንዱ ጉድ ባይ ነበርኩና በወቅቱ አንዲት ግጥም ቋጥሬለት ነበር:-

ቢፈለግ ቢፈለግ ሰው ጠፍቶ ካገር፣
ለገሰ ተሾመ በትግራይ ምድር፣
አየ ትህትና አየ ቁምነገር፣
አስረክቦ መጣ ሳይውል ሳያድር::
ምን ጊዜ አርጦ ምን ጊዜ ደረሰ?
ለጌ ባይሆን ኖሮ ልቡ በፈረሰ::

ማታ ደግሞ በሬዲዮ ጀኔራሎችና ሚኒስትሮች ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ድረስ እየሄዱ እጃቸውን እንዲሰጡ ጥሪ ተላለፈ:: ጧት ቁርሴን በልቶ እየገሰገስኩ የሄድኩት ወደ ተጠቀሰው ቦታ ነበር:: እጃቸውን እንዴት እንደሚሰጡ ለማየት::

አምባሳደር ቲያትር ግንቡን ተደግፌ በመቆም ትኩረቴን ወደ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ግቢ አደረኩኝ:: ያ ሁሉ ጀኔራል ከያደፈጠበት በመውጣት እጁን ይሰጥ ጀመር:: ደግሞኮ ፈገግ ለማለት ይሞክራሉ::

ኧረ እንዳንዶቹስ ይስቃሉ:: ኢህአዲጎቹን ለማግባባት ይሁን ወይንም ጠላትን ደስ እይበለው፣ ወዳጅን እይከፋው ብለው ከቶ አልገባኝም::

ዝግባ ዝግባ የሚያክል ጀኔራል፣ እንደ ጠጅ በርሚል የተንዘረጠጠ የሰቪል ሚኒስቴር ቂጥ ለቂጥ ተጋፋ:: ህዝቡ ከቦ እያየ ይስቃል:: እኔም በዋናው በር በኩል ጠጋ ብዬ አያቸው ጀመር:: እንደ ገለባ ቀለሉብኝ:: ጨርሰው ላይኔ ሚዛን አልሞላ አሉ:: ኢህአዲጎቹም በንቀት ነበር የሚያዩዋቸው::

በ66 ዓ.ም. አብዮቱ የፈነዳ ጊዜ:-

«ጥይት ሳይተኮስ ቦምብ ሳይፈነዳ፣
ያ ሁሉ መኳንንት እንደ በግ ተነዳ!»

ተብሎ ነበር:: ዛሬ ያ ቂና ተደገመ:-

ኢህአዲግ ቢመጣ ባምቦ በኩል ቆርጦ፣
መንግስቱ እሮጠ በኬንያ እቋርጦ::
የደርግ ጀኔራሎች እነ አውሉ ነፉሱ፣
እጅ ስጡ ሲባል ከያደፈጡበት ተንጋግተው ደረሱ::
ለካ ለዚህ ኖሯል ያ ሁሉ ድንፋታ ያ ሁሉ ጩኸት፣
እንዲህ ሆኖ ቀረ የደርግ ወንድነት::
ደህና ደህናው ሱሪ የትም ተጣለና፣
ገመናችን ታየ ቀዳዳው ቀረና::

ከዚያ ቁሜ እነሱን መመልከቱ ሲያስጠላኝ ጊዜ ሽቅብ በፖስታ ቤት ሳቀና ከኋላዬ:-

"መቶ አለቃ ጎርፋ" የሚል የጥሪ ድምፅ ስማሁና ዘወር ብዬ ሳይ የመስሪያ ቤቴ ባልደረባ አምሳ አለቃ እንዳለው ነው:: የፖለቲካ ሰራተኛ ነበር:: ዛሬን እያድርገውና መሬቷን ለመርገጥ ይጠየፋት ነበር:: ቆም ብዬ ጠበኩት::

"ታዲያስ፤ ደህና ነህ" አልኩት ካጠገቤ ደርሶ እጅ ለጅ ስንጨባበጥ::

"ምን ደህንነት አለ በቁማችን ሙተን:: አየሃቸው አይደል የኛን ጀኔራሎች?" አለኝ:- እንደ መብሸቅ ብሎ::

"አየኋቸው:: እድሜ ለናንተ" አልኩት ኮስተር ብዬ::

"እንዴት ማለት? እኛ እነማነን?" ሲል ጠየቀኝ::

"ኢሰፓዎች ናችኋ! ምድረ ዱማ ተሰብስባችሁ ለሽንፈት ያበቃችሁን! ያለ ሆድ ተዝካር በስተቀር ሌላ ነገር አታውቁ! በየቀኑ ስብሰባ እያላችሁ እጃችንን አስጨበጣችሁን!" አልኩት::

"ታዲያ ይህንን ሀሳብህን ለምን ቀደም ብለህ አታቀርብም ነበር?" አለኝ፣ እንደመየቀም ብሎ::

"ያኔማ ባቀርብ ቆራርጣችሁ ትበሉኝ ነበር:: ያቀረቡትስ የታሉና:: እኔም ብሆን የስርን ፅዋ ቀምሽ ነው የወጣሁት:: ለመሆኑ ዛሬን እያድርገውና ደርጎችና ኢሰፓዎች የሰው ምክር ትቀበሉ ነበር? በእብሪት ተወጥራችሁ!" የጀኔራሎቹን ቁጭት ተወጣሁበት::

"ለመሆኑ በምን እንደ ተሸነፍን አውቀሀል?" አለኝ::

"ደግሞ በምን ተሸነፍን ልትሉ ይሆን?"

"ባስማት ነው:: ከሱዳን በመጣ አስማት ነው የተሸነፍነው" ሲለኝ ከት ብዬ ሳኩኝ:: የብሽቀት ሳቅ::

"ምን ያስቅሀል? ህዝቡ እያወራ ያለው ነው::"



ለምን የሊቢያ አስማት ሳይጨመር ቀረ ብዬኮ ነው የሳኩት:: ወናፎች! ደግሞ ብላችሁ በሱዳን አስማት አመካኛችሁ? ሱዳን እንደዚህ ያለ ጥበብ ካላት ለምን የራሷን ችግር አልፈታችም ነበር?"

"እሽ ተወው:: እውነቱን ማወቅ ከፈለክ ግን ሄደህ ማየት ትችላለህ" አለኝ ቀዝቀዝ ብሎ::

"ምኑን ነው የማየው?"

"አስማት የተደረገባቸውን"

"ምንድን ናቸው እነሱ?"

"አንዲት ነጭ ቀበሮና አንዲት ነጭ ድመት ናቸው:: መዘጋጃ ቤት አስቀምጠዋቸው እየተጠበቁ ህዝቡ ለጉድ ያያቸዋል" ሲለኝ ምራቄን በብሽቀት ተፋሁና:-

"ይልቅ ቀበሮዎቹና ድመቶቹ እኛ ነን ብትለኝ አምንህ ነበር!" አልኩትና እንደ እልህ ስለተናነቀኝ፣ "በል ያየኸውን ውሰድና አሳየኝ" ስለው:-

"በቻህንም ቢሆን ማየት ትችላለህ:: እኔ ከዚህ ተረት ሰፈር ከጓደኛየ ጋ ቀጠሮ ስላለብኝ አትከተለኝ" አለኝ:- ቆም ብሎ ሰአቱን እያየ:: በዚህ ወቅት ቴዎድሮስ አደባባይ ከፌርማታው አጠገብ ደርሰን ነበር::

"ከጓደኛህ ቀጠሮ ስትመለስ ትደርስበታለህ:: ሳታሳየኝ አትሄድም:: አለበለዚያ ለኢህአዲጎች ነው ጠቁሜ የማሲዝህ" ስል አስቦካሁት:: ካደባባዩ አጠገብ ዙ23 እየር መቃወሚያ አጥምደው ይጠብቃሉ:: ከመቅዐቡት ላብ በግንባሩ ችፍፍ አለ::

"እንዴ! ምን ማለትህ ነው መቶ አለቃ ጎርፋ፤ ምን አደረኩህ? ከምርህ ነው እንዴ?" አለኝ:- እንደ መማፀን እያለ::

"ከምሬ ነው:: ዛሬ ዋሽተህብኝ አትሄድም! እስከ ዛሬ የተቀደዳችሁት ይበቃል!" አልኩት አሁንም ኮስተር ብዬ::

"ዳግመኛ አይለመደኝም:: የዛሬን አውጣኝ" አለኝ ወደ እግሬ ስር እየጎነበሰ:: እንዲህ ሲሆን ደግሞ አሳዘነኝ::

"አስከናኝ:: ሁለተኛ ውሸትን ፈጥሮ ማውራት እንዳይለምድህ:: በል ሂድ" ስለው ፈትለክ አለ::

ከአምሳ አለቃ እንዳለው እንደ ተለየሁ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ማዘጋጃ ቤት ነበር:: በዋናው በር በኩል ስደርስ ህዝቡ ከቦ ወደ ውስጥ ያያል:: ኢህአዲጎቹ በግቢው ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ:: በታች በኩል ደግሞ ካትክልቱ ስር ሁለት ኢህአዲጎች ገልበው ይፀዳዳሉ:: ንቀት ይሁን እውቀት ማነስ እንጃ:: የሚያያቸው ሰው ሁሉ ይስቃል::

ሰው ወደ ውስጥ እንዳይገባ ከበሩ ሁለት ኢህአዲጎች ቁመው ይከላከላሉ:: ነጭዋን ቀበሮና ድመት ለማየት ወደ ውስጥ ባተኩር ከኢህአዲጎቹ በስተቀር የሚታየኝ ነገር የለም:: ምናልባት ነጭ ቀበሮና ድመት ያለኝ አምሳ አለቃ እንዳለው ኢህአዲጎቹን ይሆን እንዴ? እውነትም ሰው ከቦ የሚያየው እነሱኑ ነው:: እየሳኩኝ ወደ ቤቴ ሄድኩ::

አየ ቀበሮና ድመት! የደርግን ሰራዊት ብትንትን አደረጉት!

# 6

በማግስቱ ግንቦት 23 ቀን ነበር፤ ያን እለት የሄድኩት ወደ መርካቶ አቅጣጫ ነበር:: "አብዮታዊ ጦራችን" በየመንገዱ ዳር ፈሶ ይለምናል:: እጃቸውን፣እግራቸውን የተቆረጡ ሁሉ አሉ:: በተለይ አውቶቢስ መናኸሪያ የግር መንቀሳቀሻ የለም:: ደክሟቸው የወደቁ፣ ርሃብ የረታቸው በየጥጋጥጉ ወድቀዋል::ትኩስ ቁስለኞች ተዘርግተው ያቃስታሉ:: መናገር ያቃታቸው አፋቸውን ገጥመው አይኖቻቸው ብቻ ይቅበዘበዛሉ:: ሳንቲም በመሻት:: አንዳንዶቹ ደግሞ ቅራቅንቧቸውን ይዘው እየተማሩ የሚሄዱበትን ሳያውቁት ወደ አገኙበት አቅጣጫ ይንከላወሳሉ:: ሁሉም ግን ደክመዋል:: ጨርሶ ተስፋ የላቸውም:: ሞራላቸው ሙቷል::

"ላገራችን መግቢያ" ልመናቸው ይኸው ነው:: ህዝቡ የተቻለውን ያህል ይሰጣቸዋል:: ደረታቸውን የሚደቁ ብዙዎች ናቸው:: የሚያለቅሱ ሁሉ አሉ:: «ነፃ አውጪው ሰራዊታችን...» እየተባለ ሲነገርለት የነበረው ሰራዊት እራሱን እንኳን ነፃ ሳያወጣ ለልመና ተዳረገ:: እንዲህ ሆኖ ሳየው አእምሮየን ጭንቅ ጭንቅ አለኝ:: ያለኝ ምርጫ ከዚያ ግድም መጥፋት ነው::

በባንኩ በኩል አድርጌ ቁልቁል ባመዴ ገበያ ተዳፋሁ:: እንደ መናኸሪያው አይትረፍረፉ እንጂ በዚያም ተልከስክሰዋል:: ወጭ ወራጁን ደፈር ያሉት "ላገራችን መግቢያ" ይላሉ:: ጥግ ይዘው በመቀመጥ የሚለምኑም አሉ:: እኔምኮ የሚጠብቀኝ የነሱው እድል ነው:: አንጀቴን በሉኝ:: ግን ምን ላድርጋቸው?

ላገር መግቢያ እያለ ሲለምን እያየሁ፣
ዝም ብየው አለፍኩኝ አይቼ እንዳላየሁ፣
እኔምኮ እንደሱ እጃጠር ሁኛለሁ::

ወዴት እንደምሄድ ባላውቅም ስራመድ እየተጣደፍኩ ነው:: በምሄድበት ሁሉ ሰራዊት አላጣም:: የትም ተረጭተዋል:: በራስ ቲያትር አድርጌ ቁልቁል ወደ ሰንጋ ተራ የሚያዘልቀውን ጎዳና ይዤ እፈናጠር ጀመር::

ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስደርስ ወደ ግራዬ አጠፍ ብዬ ቁልቁል ወደ ዋናው ጎዳና የሚያዘልቀውን መንገድ ያዝኩኝ:: አሁንም ስራመድ ልክ ቀጠሮው እንዳለፈበት ሰው ሆኜ ነው:: ወደ ትግላችን ሀውልት ገሰገስኩ:: ህዝቡ ከቦ ያያል:: እረማመዴ ግርምድምድ አድርጌ የማፈርሰው እመስላለሁ:: ፊቴ ተኮሳትሯል:: ደረጃዎቹን ጡብ ጡብ እያልኩ ወጥቼ አይኖቼ በመጀመሪያ ያረፉት 24 ሰአት ከሚነደው እሳት ላይ ነበር:: ጠፍቷል:: እንኳንም እልም አለ! አብረተኞቹም እልም ብለዋል! በንዴት የተቀጣጠለ ሰውነቴ በረድ ሲልልኝ ታወቀኝ:: ቀዝቀዝ አልኩ:: "ሰደድ" ነበር:: እርጥብ ከደረቅ የማይለይ የኢሰፓዎች ምድጃ!

ወደ ሀውልቱ ብዙም ሳልጠጋ ልክ ከዚያ በፊት እንደ ማላውቀው ሁሉ ከቂጡ እስከራሱ ማስተዋል ጀመርኩኝ:: በርግጥም



ከዚያ በፊት መኖሩን እንጅ አስተውየ አይቸው አላውቅም ነበር:: ያዲስ አበባ ህዝብ ባንድ ወቅት ያለው ትዝ አለኝ::

"የደርጉ ጀላ!" እያለ ነበር የሚጠራው:: እውነትም "አብዮታዊ መሪያችን" እንደዚት ያለ ስራ ሰርተው ሄዱ!!

"እርግጠኛ ነኝ፤ ይህን ሀውልት ያለዛሬ አይተኸው አታውቅም" የሚል የሴት ድምፅ ሰማሁ:: መለስ ስል የኔነሽ አሰፋ ነች:: ፈገግታዋ አስቀድሞ ሰላምታ ሰጠኝ:: እኔም ልክ ከደመና ውስጥ ድንገት ብቅ እንደምትል ፀሀይ ፈገግ አልኩኝ::

"ልክ ነሽ፤ አልተሳሳትሽም" ብያት ለመሳሳም ተቃቀፍን:: የሽቶዋ መአዛ እውድ አደረገኝ:: ባንድ ወቅት የኔነሽ የኔ ነበረች:: በፍቅር አክንፋኛለች::

"ከዚህ ጎላ ሚካኤል አክስቴን ጠይቄ በዚህ ሳልፍ ህዝቡ ተሰብስቦ ሳይ ጊዜ እንደ ሌኒን ሀውልት እየናደው መስሎኝ ቀና ስል አንተን አየሁህ:: የኔ ጎርፍ ለመሆኑ ደህና ነህ?" አለችኝ ተሳስመን ስናበቃ::

"ደህና ነኝ:: እኔማ ምን እሆን ብለሽኝ" አልኳት ልክ የናቱን ሞት የተረዳ ያህል ሆኜ::ፈገግታዬ ጭልም እያለ::

"እረ እንኳን ደህና ሆንክ፡፡ እኔስ አስቤልህ ነበር::"

"እውነት?" አልኳት፣ አታስቢልኝም በሚል አይነት ጥያቄ::

"እንዴት? አታስቢልኝም ማለትህ ነው?"

"ከተያየን ብዙ ጊዜያችን ስለሆነ አታስታውሽኝም ብዬ እንጅ እንደምታስቢልኝ እንኳን አውቃለሁ::"

"ምንስ ቢሆን የጨረፉ ጉዞው ይረሳል" ስትል የሩቅ ጊዜ ትዝታ ቀሰቀሰችብኝ::

"ምላጭ!" አልኳት እኔም ፈገግ ብዬ::

"ምን ትሰራለህ? እንሂድ፤ ይህን ሀውልት ተገትረህ ብታየው መንግስቱን አይወልድልህ" አለችኝ::

"ያውስ በጀግንነቱ የሚፈለግ ሰው አይደል::"

"ኤዲያ! 'አብዮታዊ መሪያችን! ቆራጡ! ብልሁ!' ስትሉ የነበራችሁት እናንተው መለዮ ለባሾቹ ነበራችሁ!"

"ልክ ነሽ! ይህን የሚክድ የለም:: እውነተኛ ባህሪውን ግን እራሱ አስመሰከረ:: ሳይሞት ሀውልቱን ተሸምቶ ያሰራው የቁም ሙት መሆኑን አውቆ ኖሯል::"

"ኤዲያ! ተወኝ እባክህ" ብላኝ ተያይዘን ወረድን::

አምሳ ኪሎ ጤፍ የሚቋጥር አፍና ቂጡ በቀይ ቆዳ የተለጎመ ዘንቢል መሰል ቦርሳ አንግታለች:: ከውስጡ ምን እንዳለበት እንጃ ከብዷት ነው መሰል አስር ጊዜ ወደ ትከሻዋ ከፍ ታደርገዋለች:: ራንግለር ጃኬትና ሱሪ ነው የለበሰችው:: ከስር ደግሞ ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች፤ የላይኞቹን ሁለቱን ቁልፎች አልቆለፈቻቸውም:: እርግጠኛ ነኝ ሆን ብላ ነው:: ከጡቶቿ መሀል ያንገቷ ሀብል ተዘለግልጎ ይታያል:: እቅል እልም ነው የምታደርገው:: ስትራመድ ነጠር ነጠር ስለምትል ሽንጧ ያረግዳል:: ፀጉሯን ምንጊዜም ቢሆን ከልክ በላይ ማሳደግ አትወድም:: አጠር አድርጋ ነው የምታበጥረው:: ውሸት ምን ያደርጋል

ነፍሴ እስክምትወጣ ድረስ እወዳት ነበር። ታዲያ ምን ይሆናል። እጥማጇ በዛ፤ እሷም ቅንዝንዝ ሆነች። ስለዚህ በቅናት ከማር ብዬ ከሷ መራቅን መረጥኩኝ። ሲበዛ ጭልፊት ነች። የፈቀደችውን ወንድ የማጥመድ ችሎታዋ የተለየ ነው። ጥሩ ጥርሶች አሏት። በፈገግታዋ ነው ጠብ የምታደርገው። እኔንም ጠብ ያደረገችኝ በጥርሶቿ ነበር። ትዝ ይለኛል፤ከየኔነሽ አሰፋ ጋር የተዋወቅነው ድሬደዋ ነው። እኔ ያኔ ዘጠነኛ ክፍለ ጦር፤ የ25ኛ አየር መቃወሚያ ባትሪ ባልደረባ ነበርኩኝ። የሰፈሩ ስም "ነምበር ዋን" ይባላል። የጦሩ ካምፕ ከሰፈሩ አጠገብ ስለሆነ ሰኩት መኮንኖች ሆነን ከወይዘሮ ዘውድነሽ ምግብ ቤት ኮንትራት ይዘን እንመገብ ነበር። ያኔ ድሬደዋ ገና ከጦርነት በማገገም ላይ ነበረች። እኔም ከመሃል ኢትዮጵያ ወደዚያው የሄድኩት በዚሁ በጦርነቱ ወቅት ነበር።

የኔነሽ አሰፋ ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ነው። ወይዘሮ ዘውድነሽ ያባቷ ትንሽ እህት ስለሆኑ የረፍት ጊዜዋን የምታሳልፈው ድሬዳዋ አክስቷ ዘንዳ ነበር። እንደ ነገረችኝ ከሆነ አባቷ የሞቱባት በልጅነቷ ነው። አክስቷ ናቸው በከፊል ያሳደጓት። በዚህ የተነሳም ወደ ድሬዳዋ ትመጣለች። ያን ጊዜ ደግሞ 12ኛ ክፍል ጨርሳ ስራ ፈላጊ ነበረች።

ካክስቷ ቤት ወጣ ገባ ስንል ባይኖቿ ትቃኘን ነበር። አንዳንድ ጊዜም ምግብ ታቀርብልናለች። ሁለቱ ጓደኞቼ ውስጥ ውስጡን አብስለዋት ኖሯል። እኔ ግን ያን ጊዜ ለፍቅር ግድ አልነበረኝም። "እንዴት ሶማሊያ ትደፍረናለች" ብዬ ትኩረቴ ሁሉ ወደ ጦርነቱ ነበር። ምንላድርግ፦ «ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር!» እየተባለ ጧት ማታ በዜና ማሰራጫ ይስተጋባል። አእምሮየ ተሰልቧል፤ የፍቅር ስሜቴ ሞቷል ማለት እችላለሁ። በዚህ ላይ ደግሞ አይነ አፋር ነኝ። ጓደኞቼ ግን መቀራረቡ ጠበቅ ሲል ከሷ ጋር ጫት አብረው መቃም ጀምረው ኖሯል። የየኔነሽ ምርጫ ግን ወደኔ ይሆናል። ታዲያ ምን ይሆናል እኔ ዳፍንት ሆንኩባት። ሰረቅ አድርጌ ካልሆነ በስተቀር ባይኖቼ ሞልቼ አላያትም ነበር። ሴትን ልጅ ትክ ብሎ ማየት እፈራለሁ። ዛሬም ቢሆን ይኸው ነኝ። ቅልስልስ።

አንድ ቀን ምሳየን በልቼ ካበቃሁ በኋላ ከሰአት እረፍት ስለነበርኩ ዝም ብዬ ተቀመጥኩ። በዚህ ጊዜ ወይዘሮ ዘውድነሽ ብቸኛ መሆኔ ተሰማቸውና፦

"ጓደኞችህኮ ጓዳ ውስጥ ናቸው። ግባና ተጫወት። አንተ ጫት አትቅም" አሉኝ። ተነስቼ ስገባ የኔነሽን ከጎናቸው አድርገው ይህን ለምለም ጫት ይሉታል። የሰንደሉ ጭስ ይተናል። ፊታቸው ሁሉ በላብ ወርዝቶ ይብለጨለጫል። ጓደኞቼ ቀና ብለው አፈጠጡብኝ። "ምን ልታደርግ መጣህ?" በሚል እይነት። እኔም በመጠኑ ደነገጥኩ። የኔነሽንም በማየቴ እንደ ማፈር አልኩኝ። ልመለስ ስል፦

"የት ትሄዳለህ? ና ተቀመጥ" ስትል ቀልጠፍ ብላ ከሷ ጎን እንድቀመጥ አመቻቸችልኝ። በምንተፍረት ሄጄ ከጎኗ ተቀመጥኩ። ድሪያ ነበር የለበሰችው። ሰረቅ አድርጌ ሳያት ደረቷ ልትጠልቅ ያለች ፀሀይ ይመስላል።

"ጫት እንካ" ብላ ቀንጠብ ጫት ዘረጋችልኝ።

"አይ" ብዬ በመቃወም ራሴን ነቀነቅሁ።



"አትወድም?" አለችኝ።

"አልወድም" አልኳት።

"ካልቃምክ ውጣልን። አትደብረን" አሉኝ ጓደኞቼ።

"እሽ ብዬ ብድግ ስል"፦

"ለምን? እማየ ትሙት ልክ አይደላችሁም" ብላ ሸሚዜን ጨምድዳ በመያዝ አስቀረችኝ። ከዚያ ኮከላ ከፍታ ሰጠችኝ።

ለስላሳየን እየጠጣሁ ከመቅለስለስ ወደ መጫወት ተሸጋገርኩ። አይነ ሞራየ ከተገፈፈ በኋላ ደግሞ ጨዋታየ ከማር ይጣፍጣል። አፍነከንካት ጀመር። እነእጅሬ ግን ፈገግም አላሉ።

ያንለት እንዲሁ በተራ ጨዋታ ተለያየንና ከሶስት ቀናት በኋላ ጨረቃ ጉዞ ሆቴል በፍቅር አበድነው።

"ለምን ከጓደኞችህ መካከል አንተን እንደ መረጥኩህ ታውቃለህ?" ነበር ያለችኝ የመጀመሪያው ቀን።

"አላውቅም" አልኳት።

"ቅልስልስ ስለሆንክ ነው። እማየ ትሙት፤ ለምን እንደሆነ እንጃ ቅልስልስ ወንዶች ደስ ይሉኛል።" ገና ፍቅርን ያልጠገበች እሳት ነበረች። ዛሬም ያው ናት። ቋያ! ጨረቃ ጉዞ ሆቴል ዛሬም ትዝ ይለኛል።

"አሁን ወደ ቤትሽ ነው የምትሄጅው ወይንስ ወደ ሌላ" አልኳት ከቀድሞ ትዝታችን ስመለስ። ሽቶዋ አሁንም አትልቀቃት እያለኝ ነው።

"ወደ ቤቴ ነው የምሄደው። አንተስ ወዴት ነው የምትሄደው?" አለችኝ፦ ቦርሳዋን ወደ ትከሻዋ ከፍ እያደረገች።

"እኔ እንኳን ለጊዜው ወዴት እንደምሄድ አልወሰንኩም።"

"ከቤትህ ስትነሳ ምንም ፕሮግራም አልነበረህም?"

"አልነበረኝም። ዝም ብዬ ነው በመርካቶ ዙሬ ከሀውልቱ የደረስኩት። ወደ ቤትሽ ከሆነ ትደርሻለሽ፤ ምሳ ልጋብዝሽ?"

"በቀር ይህን ያህል ጊዜ ሳንተያይ ቆይተን ሳትጋብዝ ልትሰደኝ ኖሯል?" ስትል ቀለደችኝ። ተያይዘን ወደ ቋራ ምግብ ቤት ሄድን።

"አሁን ቋራ ምግብ ቤት ይዘኸኝ የመጣኸው ቴምድሮስን አታገኘው" አለችኝ። ዝም አልኳት። ምን መልስ ልስጣት? እንዳለችው ቋረኛው ካሳ እንደ ገና አይወለድ።

ሁሉም በየቤቱ መሸጎ ነው መሰል የምግብ አዳራሹም ሆነ ውጭ መናፈሻው ጭር ብሏል። አንደኛው ተባራሪ ሰዎች ናቸው አልፎው አልፎው የተቀመጡት።

ምሳችንን በልተን ለስላሳ ይዘን ረጋ ያለ ጨዋታ ያዝን። ጧት ለማኝ ጦር እየሁ ብዬ እንደ ትኩስ እብድ ወፈፍ ወፈፍ እንዳላልኩ ሁሉ አሁን በፈገግታ ተውጬ ከየኔነሽ ጋር በመሆን እኔን አታለልኩት።

ከምግብ ቤቱ ለቀን ወደታች ስንወርድ እንደ ዋዛ አድርጌ ልክ በፊት እንደ ምጠራት፣ "የኔ የተረሳ ፍቅር ማደስ አይቻልም እንዴ? ለምን የዛሬን እንኳን አብረን አናሳልፍም?" አልኳት በተለሳለሰ አንደበት።

"ወጭው ካልከበደህ" አለችኝ።

"እረ ለወጭውስ ግዴለሽም" አልኳት ቀልጠፍ ብዬ:: ከሁሉ ደስ የምትለኝ ለፍቅር ደጅ አለማስጠናቷ ነው:: አይጣል ግን ወዷት ለጠላችው:: ዞራክ አታየውም::

"በል እንግዲያው ለማየ ስልክ ልደውልላት" አለችኝና የህዝብ ስልክ ወዳለበት ስንሄድ:-

"ከሆን አይቀር ለሶስት ቀናት የምትቆዪ መሆንሽን ንገሪያቸው" ስላት:-

"እማየ ትሙት ከኔ ጉያ ተደብቀህ መቆየት ትፈልጋለህ መሰል?" ቆም ብላ በሽሙጥ ፈገግታ አየችኝ::

"ብስጭት ብስጭት ስላለኝ ካንች ጋር ስሆን እረሳዋለሁ:: ለዚያውም የቀድሞዋ የኔነሽ ከሆንሽ ነው::"

"ድንቄም ብስጭት:: ምን ለመሆን?" ብላ የስልክ እጀታውን አንስታ ወደ ጆሮዋ ካስጠጋች በኋላ ሳንቲሞች ጨመረችና ቁጥሮች ታሽከረክር ጀመር:: እኔ ካጠገቧ ቁሜአለሁ:: ወዲያው ሳንቲሙን ስልቅጥ ሲያደርገው:-

"ሀሎ! እማየ ነሽ?... እንደምን ዋልሽ... እየውልሽ ለሶስት ቀናት ያህል እንዲት ጓደኛዬ ታማ ከሷ ቤት ነኝ:: ብቻዋን ስለሆነች እነጋገሪኝ ስላለችኝ ነው:: እንዳታስቢ ብዬ ነው የደወልኩልሽ..." አለቻቸው:: ወዲያው ደግሞ ምን እንዳሏት እንጃ ፊቷን ከስክሳ፣ "የራሱ ጉዳይ ነው፤ ጓደኛዋ ታማ ሄዳለች በይው!" ብላ በቁጣ ስልኩን ዘጋችው:: "የምን ሰው ነው? " ብዬ ልጠይቃት አልኩና መልሽ ተውኩት::

እኔም እማማ ልኬ እንዳያስቡ ለሶስት ቀናት ከክስቴጋ የምቆይ መሆኔን በጎረቤት ስልክ ገልጩላቸው ጎን ለጎን ሆነን ወደታች ወረድን:: የትኛው ሆቴል እንደሚሻል ማማረጥ ያዘን:: ለፀጥታውም ሆነ ለማንኛውም ነገር የተሻለ ሆቴል መምረጥ ነበረብን:: ለሶስት ቀናትም ቢሆን ሰላማችን መደፍረስ የለበትም::

ከየኔነሽ እሰፋ ጋር እርብለት የመሸግን ሰዋለት ተለያየን:: ቁሜ መሄዶ ብርቱ ነኝ:: እራሴ ሁሉ በፍቅር ዞሯል:: አይኖቼም ቀልተዋል:: ሰውነቴ በጠቅላላው ደቋል:: የኔነሽ መቼም እያደር ጥንቅሽ ነው የምትሆነው:: የተረሳ ፍቅርን እንደ ገና መቀስቀስ ደግሞ አይጣል ነው:: የተዳፈነው እየተጫረ ይቀጣጠልና መላ አካላት መጋየት ነው:: ሁሉን ነገር አስረሳችኝ:: ከሷ ጉያ ተሸጉጬ ዋልኩ፤ አደርኩ፤ ተረጋጋሁ::

ከሷ እንደተለየሁ ወደ ቤቴ ነበር የሄድኩት:: ታክሲዎች ስራቸውን ጀምረው ስለነበር በታክሲ ነበር የሄድኩት:: በግሬ ቢሆን ኖሮ እርግጠኛ ነኝ ከመንገድ አዙሮኝ እወድቅ ነበር::

ከቤቴ እንደደረስኩ ካልጋዬ ላይ ተዘረርኩኝ:: ሙሉ ቀን ድብን ያለ እንቅልፍ ተኝቼ ዋልኩኝ:: የሶስት ቀናቱን እንቅልፍ ተወጣሁት:: የኔነሽ እንዴት ሆና ይሆን? አጅሬት ወይ ይሄኔ አንዱን ጠምዳው ይሆናል:: ፍቅር የማትጠግብ ፍጥረት::

እራቴን በልቼ እንደገና ተጠቅልየ ተኛሁ:: እስከ ሌሊቱ አስር ሰአት ድረስ ከንቅልፌ አልነቃሁም ነበር:: አስደንጋጩ ፍንዳታ ነው ከንቅልፌ ያባነነኝ::



# ምእራፍ ሰስት

የዘር መፈጠሪያው ዋዜማው ግንቦት፣
ምነው እሳት ሆነ ዛሬና ትናንት::

## 7

እለቱ ማክሰኞ ግንቦት 27 ቀን 1983 ዓ.ም. ነው:: ይህ እለትና ወር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሲታሰብ የሚኖር ይመስላል:: ብዙ ክንዋኔዎች በተከታታይ ተከናውነውበታል::

ግንቦት 8 ቀን 1981 እለቱ ማክሰኞ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሮ በመክሸፉ ሜ/ጀነራል መርእድ ንጉሴ የጦር ሀይሎች ኢታማጆር ሹም፣ ሜ/ጀኔራል አምሀ ደስታ፣ ያየር ሀይል አዛዥ በእለቱ ራሳቸውን ገደሉ::

ግንቦት 10 ቀን 1981 የሰሜኑ የጦር አዛዥ ሜ/ጀኔራል ደምሴ ቡልቱና ጥቂት ጀኔራሎችና በርካታ ኮለኔሎች በ102 አየር ወለድ ክፍለ ጦር ተገደሉ:: እሳዛኝ ውድቀት:: ኢትዮጵያ በየቀኑ ጀግና እያጣችና እየተራቆተች መጣች፤ ባንፃሩ ምንቸቶች ጋን ሆኑ::

ግንቦት 13 ቀን 1982 ዓ.ም. "አብዮታዊ መሪያችን" 12 ጀኔራሎችን ረሸኑ፤ በአንፃሩ ቱልቱላዎች ብቻ ቀሩ::

ግንቦት 11 ቀን 1983 መፈንቅለ መንግስቱ የከሸፈበትን ሁለተኛ አመት ምክንያት በማድረግ ቤተ መንግስት፣ "ካብዮታዊ መሪያችን" ቤት ቅልጥ ያለ ግብዣ ነበር:: በውስጥ ግን "ቆራጡ መሪያችን" የወጭ ያደረጉት ግብዣ ነበር:: በዚህ እለት ደሴ ተያዘች::

ግንቦት 13 ቀን 1983 እለተ ማክሰኞ፤ "ቆራጡና ብልሁ መሪያችን፣ ውድ ጓድ መንግስቱ ሀይለማርያም፣ የኢሰፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሀፊ፣ የኢህድሪ ፕሬዚዳንት፣ያብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ" በዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን ወደ ዝምባብዌ ፈረጠጡ!!

ግንቦት 20 ቀን 1983 አዲስ አበባ በኢህአዲግ ተያዘች::

ግንቦት 27 ቀን እለተ ማክሰኞ በሳምንቱ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ጀምሮ አዲስ አበባ በከባድ ፍንዳታና ቃጠሎ ተናወጠች::

ቃጠሎው የተነሳው ወደ ነፋስ ስልክ አቅጣጫ፣ ጎተራ አጠገብ፣ በቅሎ ቤት እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ያለው የጦር ሰራዊት የመሳሪያ ዲፖ በእሳት በመያያዙ ነው:: ከእንቅልፌ የባነንኩት በከባድ ፍንዳታው ሳቢያ ካልጋየ ላይ ስናጥ ነበር:: እማማ ልኬ ቀድመው በመነሳት:-

"እግዚኦ! እግዚኦ! ምኑን ማት አመጣህብን ጌታዬ!" እያሉ ይብረከረኩሉ:: ልብሴን ለባብሼ ፈጥኘ ከቤት ስወጣ የሰፈሩ ሰው ሁሉ በየቤቱ በር እገርግሮ በመቆም ይንጫጫል:: ደቡብ አዲስ አበባ እየጋየች ነው:: የከባድ መሳሪያ ፍንዳታ ከተማዋን በሞላ ያናውጣታል:: የሁላችንም ግምት አድፍጦ የነበረ ጦር ገብቶ ከኢህአዲግ ጋር ውጊያ ገጥሟል የሚል ነበር:: ንጋት ቀደደና ሁሉም ነገር ሲታይ ያደፈጠ ጀግና ጦር ሳይሆን እሳት ነው:: የግንቦት ወር እሳት::

ጥቀርሻ የመሰለ ጭስ በመጠኑ ወደ መናገሻ ጋራ ረገብ ብሎ ሰማዩን ደግፎት የቆመ ይመስላል:: ከሰማዩ ላይ ሌሊቱን ወጥቶ የተከመረው ጭስ ጥቀርሻ መስሎ ሊዘንብ የተቃረበ ይመስላል:: ከስር ደግሞ ነበልባል ሽቅብ ሽቅብ ይተፋል:: ከባድ ፍንዳታ በፈነዳ ቁጥር ብራማ መልክ ያለው፣ የተድቦለቦለ ነገር እንደተወርዋሪ ኮከብ በጭሱ መሀል ሰንጥቆ ለረጅም ጊዜ ላይን ሳይጠፋ ይቆይና ያርጋል:: ሌላ ብርቱካንማ መልክ ከስር ይነሳና ተብለጭልጮ ይሄዳል:: መካከለኛ ተኩስ ደግሞ እንደ በረዶ ይንዷዷል:: ቃጠሎው ደግሞ ካንዱ ህንፃ ወደ ሌላው ህንፃ ባፋጣኝ እየተሸጋገረ አዲስ አበባን ብርክ ውስጥ አስገባት:: የእግዚአብሄር ቁጣ፣ ያላህ ሰይፍ የተሰነዘረባት አደረጋት::

ንጋት ከቀደደ በኋላ ህዝቡ ከያለበት በመውጣት ወደ ቃጠሎው መጉረፍ ያዘ:: ወገኑን፣ ዘመዱን፣ ወዳጁን... ከመቅሰፍት ለማዳን:: እኔም ወዳክስቴ ቤት እሩጫየን ቀጠልኩ:: ደግሞ ቤቷ ከዚያው ከቃጠሎው አካባቢ ነው::

ቸርችል ጎዳና ብቅ ስል ከወደታች በኩል ሽቅብ የሚያቀናው ህዝብ ለጉድ ነው:: ቢጠይቁት መልስ አይሰጥም:: ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም:: በፍርሃትና በጭንቀት ብቻ ይቃትታል:: አብዛኞቹ አሮጊቶችና ህፃናት ናቸው:: ውስጥ ልብስ ብቻ የለበሱ አሉ:: ብርድ ልብስ ጠቅልለው የያዙ ብዙዎች ናቸው:: እጅና እግራቸውን ብቻ ይዘው የሚቅበዘበዙት ደግሞ ከሁሉም ይበልጣሉ:: ሁሉም ግን አሳዳጅ የተከተላቸው ይመስል እየዞሩ እያዩ በዚያ አቀበት ይቧችቻሉ::

እናቶቻቸው የጠፍዋቸው ህፃናት «እናቴ» እያሉ ይጮሀሉ:: ልጆቻቸው የጠእፍዋቸው እናቶች «ልጆቼ» እያሉ ይንጦዘጦዛሉ:: ምስቅልቅል ያለ ሁኔታ ነው:: ጋራው ከመጣው ቁጣ የሚያድን ይመስል ሁሉም ወደ እንጦጦ አቅጣጫ ነፍሴ አውጭኝ ይላል... ቃጠሎውም የጥፋት አድማሱን በማስፋት ደቡብ አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ በጭስ ጋርዷታል:: ጥቀርሻ መስሎ ይጥመለመላል:: ነበልባሉም ብጫ መልክ እንዳንድ ጊዜም ቀይ ላንቃ እየመሰለ ሽቅብ ሽቅብ ይጎናል::

ሶስት አራቱ በአንድ ጊዜ ሲፈነዳ ምድሯ ትናወጣለች:: በነውጡ ምክንያት ያዲስ አበባ ረጃጅም ፎቆች መስተዋታቸው እንዳለ ወርዶ መሬት ላይ እንደ በረዶ ሆጭ ብሎ ተከምሯል::

ቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ስደርስ ከላይ የመጣውን ህዝብ እንዳያልፍ ኢህአዲጎች አጥር ሰርተው አግደውታል:: ሕዝቡ ጥቅልል ብሎ አግድም ወደ መስቀል አደባባይ አለፈ:: እኔም ተቀላቅየ ነጎድኩ...

የቦሌን መስመር እንደ ያዘን ሁሉም አቋራጭ መንገድ እየፈለገ ወደ ቃጠሎው ለመድረስ በያቅጣጫው ተሰራጨ:: እኔም ተሹለክልኬ ካክስቴ ቤት ደረስኩ:: በሌሊት ልብሷ ብቻ ደንብራ እንደ ወጣች አገኘኋት:: ተነፈስኩ::

"ይህ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው" አለችኝ፡- ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ::

"ለምን ልብስ አለበስሽም?" አልኳት::

"ምኑን እለብሰዋለሁ? የቤቱ በር በፍንዳታው ምክንያት በራፉ ተቀልፎ አልከፈትም አለ" አለችኝ:: እውነትም ተከርችሟል:: ቤቷም ባላንድ ፎቅ ስለነበረ ባንድ በኩል መስተዋቱ በመጠኑ እረግፍዋል::



ወዲያው ተሯሩጠን አናፂዎች አምጥተን ከፈቱልን:: አግዜር ይስጣቸው::

አሁንም አካባቢው በጭስ ደመና እንደ ጨለመ ነው:: በርግጥ የጧቷ ፀሀይ ፈንጥቃለች:: ያዲስ አበባ ህዝብ ግና ገና ተስፋ አልፈነጠቀበትም:: ፍንዳታው አሁን በመጠኑ ተግ ብሏል:: የቀላል መሳሪያ ተኩስ ግን እንደ ዶፍ ይወርዳል:: የቃጠሎው ድምፅ ልክ እንደ ወገቦ ሲንጃጃ ይሰማል::

አክስቴን ካረጋጋኋት በኋላ እልቂቱን ለማየት ወጣሁ:: ከታች ከጎዳናው ብደርስ ግን ለማለፍ አልቻልኩም:: አሁንም ኢህአዲጎቹ በየቦታው ግድግዳ ሆነው አላሳለፉም:: ከቃጠሎው ቦታ ደርሼ የጠፋውን ጥፋት የማየት እድል ሳይገጥመኝ ቀረ:: ያው ማታ እንደ ማንኛውም ሰው በሬዲዮ ሰማሁት:: እሱም ቢሆን ቁጥብ ነበር:: "... ወደ ፊት የወደመውን ንብረትና የሞተውን የሰው ብዛት እንደ ተረጋገጠ እንገልፃለን" የሚል ነበር:: ሁለት የውጭ ጋዜጠኞች ግን አንደኛው ወዲያው ሲሞት ሁለተኛው ደግሞ በፀና መቁሰሉ ተገልፀዋል::

ማታ በሬዲዮ እንደ ተገለፀው ከሆነ የቃጠሎው መንስኤ የተሳበበው በደርግ ሰራዊትና በኢስፓዎች ነው:: ይኸ ሰበብ በጣም አስገረመኝ:: ደርግም ይኸው ነበር:: አንድ ነገር የተፈጠረ እንደ ሆነ «የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች ደባ! አድሃሪያን አሻጥር ሰርተው...» እያለ ይለፈልፍ ነበር:: ከጥቂት አመታት ወዲህ ደግሞ የጦር ሜዳው ድል እየከዳው ሲመጣ እራሱ በፈጠረው ጭፍን አመራር ኢኮኖሚው ሲንኮታኮት «ያረብ ቅጥረኞች ሴራ! የወያኔዎች ደባ!...» በማለት ይወተውት ነበር:: የሚገርመው ግን እንዳንዶቹንማ ድርጊቶች እራሱ ይፈፅማቸውና ለመቀስቀሻነት ይጠቀምባቸዋል:: የነዚህም አዝማሚያ አላማረኝም:: ካንድ ወንዝ የተቀዱ አስመሰሏቸዋል::

ጀኔራሎቹ በጦር ሜዳ ማዋጋት አቅቷቸው ጦሩን እየመሩ አዲስ አበባ ገብተው፣ አዲስ አበባ የቆዩትም በየሽርንቁላው እንደ ጥንቸል አድፍጠው ቆይተው እጅ ስጡ ሲባል እጃቸውን ለመስጠት ሲሽቀዳደሙ እያየናቸው፡- «የደርግ ሰራዊት ሴራ ነው» መባሉ መልሶ የኢህአዲግ ሴራ ነው ያሰኛል::

ጦሩም የትም ተበትኖ የሚበላው አጥቶ ልመና ተሰማርቷል:: ለዚያውስ የትኛው አመራር ሰጭ ተገኝቶ ነው እንዲህ ያለው ስውር ደባ የሚፈፀመው? በርግጥ ለተንኮል ስራ ደርጎችና ከነሱ የተጠጉ ሁሉ ይሰንፋሉ አይባልም:: ጥያቄው በዚህን ወቅት አሞቱ አላቸወይ? የሚስዩቻቸውን ቀሚስ አጥልቀው በማድፈጥ፡- «ምን ይመጣ ይሆን?» እያሉ እየባነኑ እንዲህ ያለ ሙያ ሊሰሩ! ድንቄም!

በዚህ ቃጠሎ ሌሎቹ ታሚተኞች ኢስፓዎች ናቸው::

እነሱም ቢሆን እንደዚህ ያለ ተግባር ይፈፅማሉ ብዬ አላስብም:: ሰውን ያለስራው ማማት ሀጢአት ነው:: ለነገሩስ ቀላል ነው:: ህፃን ልጅም ቢሆን ካሳዩት ያደርገዋል:: ክብሪት ጭሮ መለኮስ ነው:: ከዚያ በኋላ ቆስቋሹኝ አይልም:: በራሱ ይቀጣጠላል:: አቀጣጣይ ከቤንዚን የበለጠ ባሩድ አለ:: ቁምነገሩ ከበር ያሉትን ዘቦች ሰብሮ ከመግባቱ ላይ ነው:: አጥፍቼ ልጥፋ የሚል የኢስፓ አባል ደግሞ ካለፍናቸው የትንቅንቅ አመታት ውስጥ አላጋጠመኝም:: ኢስፓዎችን እናውቃቸዋለን፤ሁሉም ናቸው ባይባልም አብዛኞቹ የድል አጥቢያ አርበኞች ናቸው:: ወይንም

ደግሞ የሰላም ጊዜ ጀግኖች ናቸው:: ባይሆን በግልፅ የሚነገርላቸው ውስኪ ለመጠጣት፣ ጮማ ለመጮምጮም የማይቀደሙ፣ የሴት ዳሌ የማያማርጡ መሆናቸውን ነው፤ በተረፈ ግን ቁርጥማታሞች ናቸው::

የናት አገር ጥሪ በመጣ ቁጥር በተግባር አይተናቸዋል:: የበሽታቸው ብዛት ተነግሮ አያልቅም:: ጉበት፣ ሳንባ፣ ጨጓራ፣ ኩላሊት፣ ጣፊያ፣ ትርፍ አንጀት፣ ስኳር፣ ደም ብዛት፣ ደም ማነስ... እረ ምኑ ቅጡ? በሽታቸው ጠቅላላ የሆድ እቃ በሽታ ነው:: ያን ሰሞን ሆስፒታሎች በኢስፓዎች ይጣበባሉ:: ሚስቶች ይደገፋሉ፣ ልጆች ጃንጥላ ይዘው ይከተላሉ፤ እነሱ ያቃስታሉ፤ በዚህ በዚያ ብለው ቅርት ይሏታል:: ሀኪሞቹም በነሱ ላይ አይጨክኑም:: መከረኛ ዘበኞች ከየድርጅቱ ይለቀሙና ወደ ጦርነት ይላካሉ:: ያልገባኝ ግን የደርጎችና የኢስፓዎች በሽታ ለምን የሆድ እቃ ብቻ እንደሆነ ነው? የድሎት በሽታ ይሆን እንዴ? ደግሞ፤ የሚነሳው ጦርነት ሲቀሰቀስ ነው:: ቁንጮ የደርግ አባላትም በሆድ እቃ በሽታ ጡረታ ወጥተዋል:: እረ ስለ ኢስፓዎች ብዙ የተባለ አለ:: አሁን በቅርቡ እንኳን ኢህአዲግ ከጎንደር እያሳደደ ወደ ጎጃም ሲያሻግራቸው ሩጫቸው የገረመው የጎንደር ህዝብ፡-

«እነ እንቁላል ቁርሱ እነ ብር ትራሱ፣
ሀሙሲት ቢተኩስ ባህርዳርን አልፈው ዳንግላ ደረሱ::
ደህንነት ባህያ ኢስፓ በፈረስ፣
አሸቅድድም ያዙ ማርቆስ ለመድረስ!» ብሏቸዋል::

ከማርቆስ ደግሞ ፈርጥጠው አዲስ አበባ ሲገቡ የጎጃም ህዝብ፡-

«የወያኔ ጥይት ጨሞጋ ቢያንራ፣
ማርቆስ ላይ ቀረ ድሃና ባንዲራ!» ብሏቸዋል::

እኛ ደርጎችንና ኢስፓዎችን የምናውቃቸው ከሞላ ጎደል በዚህ ተግባራቸው ነው::

አሁን በመጨረሻው በሚያዝያው የክተት ጥሪ ደርግ «ራሳችሁን ተከላከሉ» ብሎ መሳሪያ አስታጥቋቸው ነበር:: ጥቂቶችም ሰንዳፉ ገብተው ለጥቂት ቀናት ለመሰልጠን ሞክረዋል:: «አዙጥ» በሚል መጠሪያ ስምም ተሰባስበው ነበር:: «አዲስ አበባ ዙሪያ ጥበቃ» ማለት ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን የተፈየደ ነገር የለም:: ያው ዙጥ ብለው ቀሩ እንጅ:: እና የተሰነዘረው ምክንያት አጥጋቢ አይደለም ባይ ነኝ:: «ሲበሏት የፈለጓትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል» እንደ ሚባለው እንዳይሆን:: ይልቅየ በቃጠሎው የተጎዱት ህዝቦች በጅጉ ያሳዝናሉ::

እኔም በየኔነሽ ፍቅር ተቃጥያለሁ:: ማታ ስልክ ደውየላት ነበር:: እናቷ "የለችም" አሉኝ:: የት ሄዳ ይሆን? እየቆየሁ ቅናት ሰረሰረኝ:: ይህን ጊዜ ካንዱ ጋር በፍቅር እየተምነሸነሸች ይሆናል:: ትጥል አልኩ::ያለፉት ሶስት ሌሊቶች ትዝ አሉኝ:: እንደ እንዝርትክ ነው ሹራ የምታሽረው:: ተስማ አትጠገብ፤ ሁለመናዋ የማር ወለላ:: ታዲያ ምን ይሆናል! እሷን የብቻው አድርጎ ያስቀረ ወንድ የለ:: አይኖቿ፣ ጥርሶቿ፣ እርምጃዋ ሁሉ ወንድ ይጠራሉ:: አሁን ምን ነበር ድምፅዋን ብሰማው:: እንቅልፍ ወስዶኝ ያድር ነበር:: ከማን ጋር እየከነፈችው ይሆን? እሷ



መቼም በፍቅር ልግመት አታውቅም:: እኔን እንዳበጠረችኝ ሁሉ አንዱን የታደለ እያበጠረችው ይሆናል:: ያለኝ ምርጫ ተጠቅልየ መተኛት ነው:: ተኛሁ:: እንቅልፍ ግን ሊወስደኝ አልቻለም::

ቀደም ሲል ያልሰማሁት ጥሪ፣ «በድጋሚ ጥሪ» ብሎ በሬዲዮ "ከነገ ጀምሮ በ48 ሰአት ውስጥ ከም/መቶ አለቃ እስከ ኮለኔል ማእረግ ድረስ ያላችሁ መኮንኖች ጃንሜዳ በሚገኘው የቀድሞው 1ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ::"

"ይቺ ጥሪ የዚህ ቃጠሎ መንስኤ ነች" አልኩኝ:: ይህንኑ ሳሰላስል ለጊዜው የኔነሽን አረሳኋት::

## 8

በልማዱ የግንቦት ወር የበልግ ወቅት ነበር:: በዚህ አመት ግን ደርቋል:: ነፋስ ብቻ፤ አቀጣጣይ ነፋስ...

ማታ በሬዲዮ በተላለፈው ጥሪ መሰረት በጧት ቁርሴን በልቼ ደፋ ደፋ እያልኩኝ በጊዮርጊስ አቅንቼ ወደ ጃንሜዳ ገሰገስኩ:: ሲቪሉ ህዝብ ሌሎ ስለጀመረ በያቅጣጫው ይጣደፋል:: ሰውም ከያደፈጠበት ወጥቶ መተረማመስ ይዟል:: በመጠኑ የመረጋጋት ሁኔታ ይታያል::

እየገሰገስኩ ከቀድሞው 1ኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ስደርስ ከበሩ ውጭ መኮንኖች ፈስዋል:: ሁሉም አፍ ላፍ ገጥመው ያንሾካሽካሉ:: ወደ ውስጥ ስገባ ደግሞ የእግር መቋሚያ የለም:: ሁሉም የጦር መኮንን የሲቪል ልብስ ነው የለበሰው:: ሽማግሌ ኮሎኔሎች ሳይቀሩ የዘመኑን ራንግለር ጃኬትና ሱሪ ነው የለበሱት:: ያንዳንዶቹ ነተብ ብሏል:: ሁሉም ማለት ይቻላል ከራሳቸው የሌኒን ቆብ አይነት ደፍተዋል:: የፀሐይ መነፅርም የስኩ በርካታ ናቸው:: ብቻ ሁሉም ተዋናይ መስሏል::

ለመመዝገብ፣ «ተሰለፉ» ተባልንና መሰለፍ ስንጀምር መቆሚያ የት ተገኝቶ:: ደግሞ ቀድሞ ለመሰለፍ መስገብገብ የጀመርነው ከዚህ በኋላ ነበር:: የት ለመድረስ እንደ ተጣደፍን አልገባኝም:: ግብግቡ የዋዛ አልነበረም:: ይህም ሆኖ አልተሳካልንም:: ቦታው በመጥበቡ፡-«ወደ ጃንሜዳ ውጡ» ተባልን:: ቀድሞ ሰልፍ ለመያዝ እንደ ግሪሳ ወፍ ግርር አልን:: ወላ ኮለኔል ወላ ሻለቃ ትናንት ከተመረቀው ምክትል መቶ አለቃ ጋር እኩል እግርን ነቅሎ መፈትለክ ሆነ::

አንድ ቁመቱ የስልክ ምሰሶ የሚያክል ሰውነቱ ጭርንቅ ያለ መኮንን ሲሮጥ ጥቅልል ብሎ ወደቀና እንደግንዲላ ተንከባለለ:: ሁለት ጊዜ አቃሰተና ተነስቶ አቧራውን እንኳን ሳያራግፈው እሩጫውን ቀጠለ:: ፈንደስ ፈንደስ እያለ:: ነፍሴ እስክምትወጣ ድረስ ሳኩኝ::

ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት፡- «ተሰብሰቡ» ተባልንና ስላላማው በድምፅ ማጉሊያ ተገለፀልን:: ቀደም ሲል የፖሊስ መኮንን ነበሩ አሉ:: ጥቁር ናቸው:: የማእረግ ምልክት ባያደርጉም ሌ/ኮለኔል እንደ ነበሩ የሚያውቋቸው ነግረውኛል:: ወደ ጦሩ ተዛውረው ያንድ ብርጌድ የጦር አዛዥ ነበሩ:: ሲቀናቸው ትግራይ ላይ ተማረኩ:: ፊኛቸው ከፊታቸው

አይለይም። ተፈጥሮአቸው ይሆን ወይንም በድል አድራጊነታቸው ኮርተውና ተደስተው አይታወቅም ሲናገሩም ፈንደቅደቅ እያሉ ነው። ብቻ እንደ ጥቁረታቸው ፈገግታቸው ባይኖር ኖሮ ያስደነብሩን ነበር።

"ምዝገባውን እንደ ጨረሳችሁ ለተሃድሶ፣ ደርጋዊ አመለካከታችሁ በመጠኑ እንዲለወጥ፣ ለሶስት ቀናት ካዲስ አበባ ወጣ ትላላችሁ። ደግሞ እስራችው እንዳታስችን ለቤተሰቦቻችሁ አስረዷቸው" ሲሉ በመግባቢያ አነጋገር ተናገሩ። እኛ በመጠራጠር ተተራመስን።

"የሌሊት ልብስ አልያዝንም" ሲል አንድ መኮንን ጠየቀ።

"ችግር የለም፤ ልብስም፣ ምግብም ዝግጁ ነው። አታስቡ። ባይሆን እንደ ደርግ ጮማ አናቀርብላችሁም" በማለት ሁላችንንም አሳቁን። ከዚህ በኋላ ማንም ቅር አልተሰኘም። ሁላችንም የሶስቱን ቀን የተሃድሶ ሴሚናር ተካፍለን ለመምጣትና የግንቦትን ወር ደመወዝ ለመውሰድ ቸኮልን። ከዚያ ደግሞ እንዳቅማችን ስራ መያዝ... ወዲያው ስድስት አይፋ መኪናዎች ቀረቡና የተመዘገቡትን ማሳፈር ያዙ። እኔ አሳፈር እኔ አሳፈር ጦርነት ሆነ።

«የደርጉ መኪና ሸራ የለበሰው፣
ያን ሁሉ መኳንንት ወዴት አደረሰው?»

እንዳልተባለ ሁሉ ዛሬ ያ-ፅዋ ሞልቶ በመፍሰሱ በራሽን መጫኛ ባሮጌ አይፋ እንደ ሰርዲን እየታጨቅን እንጫን ጀመር። ንጉሱም ባሮጌ ቮልስዋጎን ነበር ወደ እስር የተወሰዱት። ያ-ሁሉ በጥራን ኮለኔል ቂጡ እየተገፋ ይሳፈር ጀመር። ማእረግና ስልጣንም የምትከብደው ለካ በጊዜ ላይ ኖሯል። እንደ ጌሾ ቀለነው አረፍነ። ግፊያው፣ ትርምሱ፣ ጩኸቱ እራሱን የቻለ ትርኢት ነው።

ያን እለት ፈፅሞ ወረፋ ሳይደርሰኝ በመቅረቱ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። እርም የለኝም፤ ማታ ለየኔነሽ ስልክ ደወልኩላት፡- «የለችም» ተባልኩ። ንድድ እንዳልኩ ተጠቅልየ ተኛሁ።

# 9

በማግስቱ ቀደም ብዬ በመነሳት ቁረሴን እንደ ነገሩ ቀማምሼ ቀድሜ ስልፍ ለመ ጋዝ እየገሰገስኩ ስደርስ ሌሊቱን ሲጓዙ ይደሩ ወይንም እንደኔው ይማልዱ ጃንሜዳ ጠጠር ቢጣል መሬት ላይ አታርፍም። አብዛኞቹ ግን ከዚያው ጃንሜዳ ተኝተው ያደሩ ናቸው። እኔ ስደርስ እንኳን ውርጭ ያገረራቸው ገና አልተነሱም ነበር። ልክ እንደ ስደተኛ ተኮራምተዋል።

የዛሬውማ ለጉድ ነው። ሚስቶች፣ ልጆች፣ ጎረቤቶች፣ ወዳጆች አልቀሩም። ተነቅንቀው መጥተዋል። «ሴሚናር ሊሄዱ ነው» ስለተባለ ለመሸኘት ነው። ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ ጠቅልለው በፌስታል፣ በትንሽ ቦርሳ አንጠልጥለው የያዙ ጥቂቶች አይደሉም። ከዚህ ላይስ እኔም ብልጥ ሆኛለሁ። ለክፋም ለደጉም ብዬ አንድ ፎጣ፣ አንድ ጋቢ፣ ካናቴራና መለወጫ የውስጥ ሱሪ በቦርሳ ከትቼ አንጠልጥዬ ይዣለሁ።



በኪሴ ደግሞ አምሳ ብር ብቻ አለችኝ። ለምናልባት እንጂ ምግብም ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል ተብሏል።

እኩለ ቀን ላይ ከኛው መካከል መንጃ ፈቃድ ያላቸው ሹፌሮችም ተመርጠው ተመደቡ። ምዝገባውም ከዚያው እንዲሆን ተወስኖ ቆመ። ከዚህ በኋላ የትንቅንቁ ነገር አይነሳ። ለካም ከዚህ በፊት ትንቅንቁ መጠነኛ የነበረው ግማሹ ስለሚመዘገብ ኖሯል። አሁንማ አንድ አይፋ እንደ አፈር ገልባጭ ገልብጦ በመጣ ቁጥር ሺ መኮንን ይሰፍርበታል። ኋላማ ኢህአዲጎቹም ማስተባበሩን ተውት። ሹፌሮቹ እኛ፤ ተሚኞቹ እኛ፤ ምን ችግር አለው?

ሚስቱ ከኋላው ቂጡን እየገፋችው የሚሳፈር አለ። እንሳፈራለን ሲሉ እንደ ኑግ ጆንያ ተንደባለው የሚወድቁ አሉ። አውክተን እንስቃለን። ከወደቁበት ተነስተው ተፍገምግመው ለመሳፈር ይታገላሉ። ደግነቱ የሞተ ሰው የለም።

"እረ ጎበዝ፤ እረ ተዋረድን፤ እረ ይሽ ቀን ያልፍና ያስተዛዝበናል። እረ እረጋ በሉ። የት ለመድረስ ነው?" አሉ አንድ በድሜ ጠና ያሉ መኮንን። ሌላው ቀበል አድርገው፡-

"ለካ እንደዚህ ኖረናል? እኛን ያላሸነፉስ ማንን ሊያሸንፉ ኖሯል! የጀኔራሎቹ እጅ አሰጣጥ ሲያስቀን የኛው ብሶ ቁጭ አለ" አሉ ክፉኛ አገዝነው።

አይፋዎቹ አንዱ ሲሄድ ሌላው ይመጣል። መኮንኑ ግን ጉደልም አላለ። ደርግ በየወሩ ያስመረቀው ቢዝቁት ቢዝቁት ንቅንቅ አልል አለ። እኔም ወረፋ ሳይደርሰኝ የምሳ ሰአት ደረሰ።

ባካባቢው ካሉት ምግብ ቤቶች በልቼ ለመምጣት በታችኛው በር በኩል ወጣ ስል ከውጭ በግንቡ አጥር ዙሪያ ጥቁር ጥቁር መነፅራቸውን ደንቅረው ተኮልኩለው የቆሙ መኮንናችን አየሁ። ከወደ ውስጥ የሚወጡትን ጠቀስ እያደረጉ ስለሁኔታው ይጠይቃሉ። ሳያቸው ከትናንት ጀምረው ወደ ውስጥ አልገቡም። የፍርሃትና የጥርጣሬ ሁኔታ ይታይባቸዋል። አብዛኞቹን አውቃቸዋለሁ። ከዚሁ አዲስ አበባ በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ገንዘብ ሲመዘብሩ የነበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በቀይ ሽብር ጊዜ የህዝብ ልጅ እንደ ጎመን የቀረደዱ ናቸው። በዚህም ስምና ማእረግ አግኝተውበታል። ከተራ ወታደርነት ባንድ ጊዜ ሻለቃ የደረሱ አሉ። የደርግ ማእረግኮ አንዳንድ ጊዜ የቃቃ ማእረግ ነው። መፈክር ሲያሰማ ድምፁ መረዋ ነው ተብሎ ምክትል አስር አለቃ የተሾመ ወታደር አውቃለሁ። ከዚህ በኋላ ጉረሯቸው እስኪነቃ መፈክር የሚያሰሙ ወታደሮች ነበሩ። ማእረግ ለማግኘት።

ባንድ ወቅት «አብዮታዊ መሪያችን» በምስራቅ ጦር ግንባር ጉብኝት ሲያደርጉ አገራችን በሶማሌ ጦር በተወረረችበት ወቅት ሞፈር ቀንበሩን ሰቅሎ የመጣ ሚሊሺያ መመለሻ አጥቶ ስጥሞ በመቅረቱ የቀድሞ ስራው ትዝ ስላለው በሬዎችን ጠምዶ ሲያርስ ቢያገኙት ባንድ ጊዜ የሻምበልነት ማእረግ አሸከሙት። ዶሮዎችን ሲያረባ የተገኘ ሙቶ አለቃም የሻለቃነት ማእረግ አግኝቷል። እነዚህ ሁሉ «መኮንኖች» ናቸው።

ከውጭ ቆመው ወሬ የሚያነፈንፉትን ላፍታ ያህል ገልመጥ ብዬ አይቻቸው አለፍኩና ካንድ ቀበሌ ምግብ ቤት በመግባት ከያዝኳት አምሳ

ብር ሶስት ብር እንደልኩላት:: ቶሎ ደመወዝ ካልተከፈለን በስተቀር ከችግር ላይ መውደቃችን የማይቀር ነው::

ምሳየን በልቼ እንዳበቃሁ ወጣ ብዬ የህዝብ ስልክ ፈልጌ ለየኔነሽ ደወልኩላት:: ልሰናበታት ፈልጌ ነበር:: ግን «የለችም» አሉኝ::

"ሀሎ! ማታም ደውዬ ነበር:: ላገኛት አልቻልኩም:: በጤናዋ አይደለችም እንዴ?... ታዲያ በጤናዋ ከሆነች ወዴት ደረሰች?... 'ከጓደኛዋ ቤት?' ... እም ...! እሺ::" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ከኔም ጋር ለሶስት ቀናት የተፍነሸነሸችው "ጓደኛዬን እሚቷል" ብላ እመካኝታ ነው:: እንዱ የታደለ ለሳምንት ይዟት መሽጓል ማለት ነው:: ሁሉ የሚቀጥፋት::

ተመልሽ ወደ ግቢው ስገባ አሁንም መኪና ላይ ለመውጣት የሚደረገው እርኩቻ እንደ ቀጠለ ነው:: ማየቱ እንኳ ያስጠላል:: መኮንኑ ሁሉ ቂጡን ጥሎ አብዷል:: እይፋ በመጣ ቁጥር ግርር ብሎ መሰፈር ነው:: ወዲህ ወዲያ የሚቅበዘበዙ መኮንኖችም አሉ:: ኢህአዲጎቹን ለማማከርም ይቃጣቸዋል:: ቶሎ ለመለጠፍ::

አንድ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ የነበረ ሻምበል በኔ አጠገብ ያልፍ የነበረ የኢህአዲግ አባልን እሮጥ ብሎ አስቆመና:-

"ጓድ" አለው ሊያማክረው በመፈለግ::

"ይቅርታ ጓድ አይደለሁም" አለው ኮስተር ብሎ::

"እሺ፣ ጓድ ታጋይ" አለው እንደ ማፈርም እንደ መደንገጥም ብሎ:: ሁለት ማእረግ ባንድ ጊዜ ስላስታቀፈው ነው መሰል ኢህአዲጉ አሁን ፈገግ ብሎ ነበር:: ፈገግታው ግን የንቀት ነበር::

"እንደዚህ እየተንጋጉ መኪና ላይ ሲወጡ ሊጎዱ ይችላሉ:: ተሰልፈው በስርአት ቢሳፈሩ አይሻልም?" ሲለው:-

"ጥሩ ሀሳብ ነው:: በል ሂድና አንተ አሰልፋቸው" ብሎት እብስ:: ጓድ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ እንደ ቆመ ቀረ...

እንዲሁ አይን አይን በማየት ብቻ የጉዞ ወረፋ ሳይደርሰኝ ከ12 ሰአት ደረስኩ:: ሰአት እላፊ አንድ ሰአት ላይ ስለሆነ አንዳንድ መኮንኖች እየተጣደፉ ወደየቤታቸው መሄድ ይዘዋል:: እኔም እየተጣደፍኩ ከግቢው ስወጣ ከበሩ ላይ የክፍሌን ባልደረባ ሻምበል አዱኛ ደቻሳን አገኘሁት:: ከወደ ውጭ ሊገባ ሲል ነው ግጥምጥም ያልነው::

"እንዴ! ጎርፉ!" አለኝና ተቃቀፍን:: ከግንቦት 19 ቀን ወዲህ ስንገናኝ የመጀመሪያችን ነው::

"አንተ ደህና ነህ? ተጠፋፋን አይደል" አለኝ ትከሻ ለትከሻ ከተሳሳምን በኋላ:-

"ደህና ነኝ:: አሁን ነው እንዴ የምትመጣው?" አልኩት::

"እረ ከዚሁ ነው የዋልኩት:: ለባለቤቴ ስልክ ለመደወል አሁን ነው የወጣሁት::"

"ምን አደዋወለህ:: መሽቷል እንሂድ እንጅ" ስለው:-

"መኪና ላይ ለመሳፈር ያለውን ስቃይ አይተኸዋል? ስለዚህ አንተም ተመለስና ከዚሁ አምሽተን ቅልል ሲልልን መሳፈር ነው:: አለበለዚያ በሳምንትም አይደርሰን" አለኝ::

"ልቅር ብለህ?" አልኩት እንደ ማመንታት እያልኩ::



"ቅር አባክህ" ብሎ ጎተት አደረገኝና ወደ ግቢ ተመለስን:: ጎን ለጎን ሆነን ስንሄድ የሱ ሰውነት ጭርንቅ ብሎ ኮቴው ሳይቀር ይከብደኛል:: በቁመትም ከኔ ዘለግ ብሎ ይታያል::

እኔና ሻምበል አዱኛ እንዳሰብነው በቶሎ ሳንሳፈር ቀረን:: ለካም ሁሉም እንደኛ ልባም ኖሯል:: የተነቃነቀም የለ:: ሄዱ ያልኳቸውም እራታቸውን እየበሉ ተመለሱ:: ምን አይነት ስነስርአት አክባሪ ኖረናል?

ግማሽ ሌሊት የጃንሜዳ ውርጭ መጥቶ ፈሰሰ:: ቆዳ ያኮማትራል፤ አጥንት ይቆረጥማል፤ ጆሮየ ሳይቀር የተነቀለ መስሎኝ ነበር:: ከስር መሬቱ ሲወረዛ ከላይ ያየሩ ቅዝቃዜ እንደ በረዶ ይጠብሳል:: መኪናዎቹ አሁንም ያንጉዛሉ:: ወሰል ያለች ጨረቃ ነበረች:: ልክ እንደ ቀኑ ሁሉ ሌሊትም መኪና ላይ ለመውጣት ግብግብ ነበር:: እኔ እንኳን መኪና ላይ ታግየ ልወጣ ይቅርና ጋደም ካልኩበትም መንቀሳቀስ አልቻልኩም:: እጆቼም፣ እግሮቼም ኩርትምትም ብለው ደንዝዘዋል:: እግዚኦ ነው! እኔ እሳት ብቻ መስሎኝ ነበር የሚጠብሰው፤ ለካም ውርጭም ይሞሽልቃል:: እንዳይነጋ የለም ባይናችን እንቅልፍ ሳይዞር ነጋ::

"እግዚአብሄር ይይልህ አዱኛ! እንዲህ አድርገህ ትጫወትብኝ!" አልኩት::

"ካሁኑ ችግሩን መላመድ አለብህ:: ሄደህኮ ሜዳ ላይ ነው የምትወድቀው" አለኝ::

"ለምን ሜዳ ላይ እወድቃለሁ?"

"ታዲያ ይህን ሁሉ መኮንን የሚችል ቤት ይገኛል ብለህ ታስባለህ?" ሲለኝ ትንሽ ድንጋጤ ተሰማኝና:-

"ለሶስት ቀናት መቼስ የሆነውን ሁሉ መቀበል ነው እንጅ" አልኩት::

"አካና! 'ለሶስት ቀናት?' እንዲህ ከሆነማ ትናንት የሄዱት ነገ ሊመለሱ ነዋ!" በማለት የምፀት ፈገግታ አሳየኝ::

"ታዲያ ለስንት ቀናት ልንቆይ ነው? እራሳቸው ናቸው 'ለሶስት ቀናት ነው የምትቆዩት' ያሉን" ስለው:-

"ጅል! ታዲያ ለወር ለሁለት ወር ወይንም ላመት ሊሉን ኖሯል?" ሲለኝ ቆጣ ብዬ:-

"ምንድን ነው የምታወራው? የሰማኸው ነገር ካለ ንገረኝ::"

"ምንም የሰማሁት ነገር የለም:: ሁኔታውን ስገመግመው ግን ለበጎ ነገር አይመስለኝም:: ቀና ነገር ቢያስቡ ኖሮ እኛን ለሶስት ቀናት ሴሚናር ብለው ካዲስ አበባ ውጭ ማጓጓዝ ባላስፈለጋቸው ነበር" የገዛ ጭንቅላቱ ከብዶኝ አንገቴን አቀርቅሬ ፀጥ አልኩኝ::

ሻምበል አዱኛ ደቻሳ በሰራዊቱ ውስጥ የረጅም ጊዜ አገልግሎት አለው:: የቀድሞ የክብር ዘበኛ አባል ነበር:: ከረጅም ጊዜ አገልግሎት ካገኘው ልምድ የተነሳ ምን ጊዜም ተጠራጣሪ ነው:: ጥሩ ተጠራጥሯል::

ወጣ ብለን ቁርሳችንን በልተን ተመለስን:: ዛሬ ደግሞ የመጨረሻ እለት ስለሆነ እድፍጦ የነበረው ሁሉ በመምጣቱ ጃንሜዳ ተጨነቀች:: ከረፋዱ ላይ እንደምንም ታግለን ተሳፈርን:: ለሶስት ቀናት የተሃድሶ ሴሚናር ወደ ሆለታ ተወሰድን::

# ምእራፍ አራት

ደርግ ሲያቃጥለኝ ሲያንገበግበኝ፣
ልፀድቅ ነው መስል በኢህአዴግ ጊዜ ገነት ገባሁኝ።

## 10

ለስራ ጉዳይ ወደ ወለጋ ክፍለ ሀገር ወይንም ወደ አምቦ የሚሄድ ሰው ካዲስ አበባ ሲነሳ የምእራብን አቅጣጫ መያዝ አለበት። ገፈርሳን አልፎ ከመናገሻ ጋራ ጎን ያሉትን የወልመራን ኮረብታዎች ሲዳፋ መንገዱ ወገብ ለወገብ ሆኖ ጠመዝማዛና በደን የተሸፈነ ነው። ቢሆንም ከታች ከረባዳው ላይ የተንጣለለውን ሜዳ ተንተርሳ የከተመችውን የሆለታ ከተማን ከማየት አያግድም።

የወልመራን ጠመዝማዛ መንገድ እያሽቆለቆሉ ሄዶ ከዙበጡ እንደ ደረሱ በሽንጣም አውቶቢስ አለዚያም ባነስተኛ መኪና ፍጥሉ ሆለታ መግባት ነው።

ለመዝናኛ የሚሆን አውቅ ሆቴሎች ባይኖሩም ካሉት መጠነኛ ሆቴሎች ውስጥ ካንዱ አረፍ ብሎ በተለይም በረንዳ ላይ ወንበር ይዞ በመቀመጥ ንፁህ አየር እየተመገቡ በርቀትም፣ በቅርበትም ሲቃኙት ስሜትን ይማርካል። እቴ ምኒልክ ተሳስተዋል፤ ዋና ከተማቸውን ከዚህ ነበር መመስረት የነበረባቸው ያሰኛል።

በስተምስራቅ የመናገሻ ጋራ እንደ ጋሻ ጃግሬ ተገትሮ ካደጋ የሚጠብቃት ይመስላል። ከንጣጠ ጀምሬው እንደ ሰንሰለት ተቀጣጠሬው የሰሜንን አቅጣጫ በመያዝ ወደ ሙገር የሚያልፉት የወልመራ ኮረብታዎች ጎርፍ ገድበው የሚያስቀሩላት ይመስላሉ። በደን ተጀቡነው በመኮፈስ።

ወደ ምእራብ አቅጣጫ ደግሞ ከትንንሽ ጉብታዎችና ሸለቆዎች በስተቀር በቾ ድረስ ያለው መሬት ለጥ ያለ እረባዳ ነው። ወደ ደቡብ በኩል ግን አይን እስከሚታክት ድረስ መመልከት ይቻላል።

ገነት ጦር ትምህርት ቤት የሚገኘው ከከተማዋ በስተደቡብ በኩል ከዳር ላይ ነው። ገነት ጦር ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት የጦር ትምህርት ቤቶች ባንጋፋነቱ ቀደምትነትን ይይዛል። ከምሳ አመት በላይ እድሜ አለው። የመጀመሪያዎቹን እጩ መኮንኖች ለማይጨው ጦርነት አውሏል።

ከትምህርት ቤቱ ግቢ እንደ ተገባ ከፊትለፊት እረጅም ሀውልት ተገትሮ ይታያል። በርቀት ሲያዩት «እንኳን ደህና መጣችሁ» የሚል ይመስላል። እየቀረቡት ሲመጡ ግን ተወርውሮ የሚከመር ነው የሚመስለው። ጣሊያን የዚሁ ትምህርት ቤት አባል የነበረውን ካዋር ላይ ባይሮፕላን ወርውሮ ስለገደለው ለዚያ መታሰቢያ የቆመ ሀውልት ነው። ካናቱ ላይ የብረት ቆብ የደፋ እግረኛ ወታደር እረጅም ጠመንጃ ይዞ አንድ እግሩን ነቅሎ ለመሮጥ ሲወረወር የሚያሳይ ምስል ነው።

ሀውልቱ ያለበት አካባቢ መሬቱ በመጠኑ ኮራ ያለ ስለሆነ ከዚያ ሆነው ወደ ፊትለፊት ባዘቅዛቂ ሲመለከቱት እመሀል ለጥ ያለ አስፋልት



አለ። ግራና ቀኝ ከላይ እስከታች የመማሪያ ክፍሎቹና የቢሮ ህንፃዎቹ በረድፍ በረድፍ ተከፋፍለው አሉ። ከበስተጀርባው ደግሞ ትንሽ ራቅቅ ብለው የእጩ መኮንኖች የመኝታ ክፍሎች ይገኛሉ።

ከአስፋልቱ መጨረሻ ላይ አንድ ትልቅ አዳራሽ አለ። ግማሹ የእጩ መኮንኖች የመመገቢያ አዳራሽ ሲሆን ግማሹ ደግሞ ቤተ መፃሕፍት ነው። ከዚሁ አዳራሽ ከወዳናቱ በኩል ያንድ ሀፃን ስእል ይታያል። የብረት ቆብ ደፍቶ በሁለት እጆቹ የብረት ቆቡን አንቆ ይዟል። ሲሮጥ እንዳይወድቅበት የያዘው ነው የሚመስለው። ሁለት እግሮቹን ከቋንጃው ሽብረክ አድርጎ ፊቱ የፈካ ቢመስልም ልብ ብሎ ላስተዋለው ግን የበረገገ ፊት ነው። ያጠለቀው ቦት ጫማ ደግሞ ከቋንጃው ደርሶ ከልጁ በልጧል። ከስእሉ እጠገብ የተፃፈው መፈክር «እኔም እንዳባባ!» ይላል። እንደ ገባኝ ከሆነ «እኔም እንዳባባ ወታደር ሆኜ አገሬን እጠብቃለሁ ወይንም ጀግና እሆናለሁ» ማለት ነው። ነገር ግን የራሱን ቆብ በሁለት እጆቹ ጨምድዶ ይዞ ቋንጃውን ሽብረክ አድርጎ ሳየው «እኔም እንዳባባ ልፈትለክ» ያለ ነው የሚመስለኝ።

«ያብዮታዊ መሪያችን» አባባልም ካዳራሹ እናት ላይ በጉልህ ተፅፎ ይታያል። እጩ መኮንኖችና አሰልጣኝ መምህራን በጧት በማታ እንጋጠው እያዩ በምሳሌነቱ እንዲጠቀሙበት ታስቦ ነው።

«ማየት ማመንን ያጠናክርልናል። በምሳሌነትም መታየትን የመሰለ ዋናና ውጤታማ የማስተማር ዘዴ የለም!» ጓድ መንግስቱ ሀይለማሪያም። እኛም አይተን፣ አስተውለን አርአያነታቸውን ተከትለናል። በምሳሌነትም ተጠቅመንበታል...

ትምህርት ቤቱ የተገነባው አዳዲስ ከተጨመሩት ህንፃዎች በስተቀር በጥርብ ድንጋይ ነው። ይህም ጥንታዊነቱን ያስመሰክርለታል።

ግቢው በጠቅላላ በአበቦችና በጥድ ተክሎች ተውቧል። በተለይ የጥድ ተክሎቹ ባጭሩ ተከርክመው ሲታዩ የጥንቱን ነፍጠኛ ያስታውሱናል። ባጠቃላይ ግቢው ከላይ እስከታች በልምላሜ የከበረ ነው። ተመልካችን ያማልላል። እውነትም ገነት ሊባል ይገባዋል።

ከጦር ትምህርት ቤቱ በስተምእራብ በኩል አንዲት ክብ ኮረብታ አለች። ከሷ እናት ላይ ያፄ ምኒልክ ቤተ መንግስት አለ። ኮረብታዋ በሆለታ ዙሪያ ያለውን በሙሉ ቁልጭ አድርጋ ታሳያለች። ለመመልከቻነት ይሆነኝ ተብላ የተሰራች ነው የምትመስለው። ለዚህም ይመስላል እቴ ምኒልክ ቤተመንግስታቸውን ካናቷ ላይ ያሰሩት።

ህንፃው ባላንድ ፎቅ ሆኖ ግዙፍ ነው። እንዱም ግዝፈት የሰጠችው ኮረብታዋ ነች። ልክ ከሞሶብ ላይ የተከደነ ወስከንቢያ ነው የሚመስለው። የህንፃው አሰራር ቤተ ንጉስ የሚባለው አይነት ሆኖ ከስፋቱ የተነሳ ብዙ ክፍሎች አሉት።

ይህ ቤተመንግስት ይዞት የነበረው ቤተ መዘክር፣ የመኮንኖች የግል ማህደር፤ የትምህርት ቤቱ የህትመት ክፍል፣ ሙዚየም፣ የትምህርት ቤቱ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱም የታሪክ ቅርሶች... ባጠቃላይ ብዙ ነገሮችን አቅፎ ነበር። እነዚህ ሁሉ ዛሬ ወድመዋል! አንዳችም የታሪክ ቅርስ አልተረፈም።

ዛሬ ቤተመንግስቱ ከሚችለው በላይ መኮንኖች እንደ ንብ ሰፍረውበታል:: ባብዛኛው መኮንን ፎቁ ይደረመሳል የሚል ስጋት አለ::

ወደፊት ገነት ጦር ትምህርት ቤትን መልሶ ለመገንባት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይጠይቃል:: ይህም ሆኖ በፅሁፍ የሰፈሩ፣ በስእል የተደገፉ ታሪኮችን ማግኘት አይቻልም:: ያውምኮ የወደመው የታሪክ ቅርስ ከመቶ አመት ወዲህ የተከማቸው ነበር:: የታሪክ ነገር ታሪክ በላው!

ይልቅየ ከዚህ ሁሉ መአት ተርፋ ያብዮታዊ መሪያችን የግል ማህደር ተበጫጭቃ አገኘኋት:: ጨርሳ ሳትወድም መቅረቷ ያስደንቃል! እሳቸውስ ከዚያ ግንዲላ ባለስልጣን መሀል ሾልከው ሄደው የል:: ከፍላት የወጣ ባቄላ ይሏል እንዲህ ነው!! እንደ ጲላጦስ «ከፈሰሰው ደም ንፁህ» ቢሆኑ አይደል!

የግል ማህደራቸው የያዘችው ቁምነገር:-

1ኛ «እጩ መኮንን መንግስቱ ሀይለማርያም» በጠቅላላው የተሰጠውን ትምህርት ተቀብሏል::

- የመሳሪያዎች
- ጠቅላላ ትምህርት
- የጦር ስልትን ተምሮ የሶስቱ ውጤት ተደምሮ ለሶስት ተካፍሎ 67.2 አምጥቶ ከ115 ተወዳዳሪዎች መካከል 80ኛ ሆኖ አልፍዋል::

2ኛ «ይህ እጩ መኮንን የሚሰጠውን ትምህርት የመቀበል ችሎታ ያለውና አስፋፍቶ ለማስተማር የሚችል ሲሆን ስነስርአት አክባሪነቱ ግን አጥጋቢ አይደለም:: የበላዩን የሚቃወምና ትቢተኛ ነው:: ነውሩን ለመሸፈን ሲል ብዙዎቹን ነገሮች በማስመሰል ይናገራል:: ተንኮል ስራ ውስጥ ለመግባት የመጀመሪያ ሰው ነው:: ነባር እውቀቱ 7ኛ ክፍልን የጨረሰ ስለሆነ ደህና ነው:: በጥብቅ አዛዥነት ስር በማንኛውም ቦታ ቢደለደል ሊሰራ ይችላል::»

ፊርማ የትምህርት መሪ መኮንን የተማሪዎች የሻምበል አዛዥ::

«አብዮታዊ መሪያችን» ገና ከማለዳው የተነገረላቸውን ትንቢት አሟልተዋል ማለት ነው:: «በማንኛውም ቦታ በጥብቅ አዛዥነት ስር ቢደለደል ሊሰራ ይችላል» ተብሎ የተነገረላቸው «አስተዋዩ መሪያችን» ያለጠባቂ ተለቀው ኢትዮጵያን ሰው አልባ አስቀርተው እሳቸው ፈረጠጡ!

# 11

አካባቢያችን ሙቀታማና ነፋሻማ ነው:: ሰምኑን ደግሞ ሳይዘንብ አይቀርም:: ደመናው ይጉለመለማል:: ከውጭ የፈሰሱት መኮንኖች ተፈጥሮን እንዴት አድርገው በቁጥጥራቸው ስር እንደሚያደርጓት እንጃላቸው::

ምን አይነት የታሪክ አጋጣሚ ነው? ይህ አንጋፋ የጦር ትምህርት ቤት በየጊዜው ያሰለጠናቸውን በህይወት ያሉትን ባሁኑ



ወቅት ካንድ ላይ አሰባስቦ እያሳሳመ ነው:: በ20 አመታቸው ተመልሰው ትምህርት ቤቱን የረገጡት አሉ:: በዚህ ላይ «አብዮታዊ መሪያችን» በየጦር ሜዳው ማእረግ የለጠፉላቸው ዛሬ "ኮርሰኞች" ሆነዋል:: እንደገና ደግሞ ያየር ሀይል፣ የባህር ሀይል፣ የፖሊስ ሰራዊት መኮንኖች አብረው ተቀላቅለዋል:: ወያኔዎችን፣ "በታኞች!" ይሏቸዋል እንጂ እኛንስ ሰብስበውናል:: ምናልባት ከሁብረተሰቡ ተነጥለን እንጂ ሆነ እንጅ እኛስ አዲስ ታሪክ ከፍተናል::

ገሚሱ መኮንን የሰፈረው ከላይ ታንከኛ ማሰልጠኛ ከነበረው ነው:: ሙሉጌታ ቡሊ የቴክኒክ ትምህርት ቤትን ሁሉ ይጠቀልላል:: ይኸም 2ኛ ክፍለ ጦር ተብሎ ተሰይሟል:: ግማሹ ደግሞ ከዋናው ትምህርት ቤት ነው የሰፈረው:: ይኸ ደግሞ 1ኛ ክፍለ ጦር ተብሏል:: እኔ ያለሁት ከሁለት ጓደኞቼ ጋር 1ኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ነው:: አንደኛው ከጃንሜዳ ጀምሮ አብሮኝ የመጣው ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሻምበል በድሉ ጫኔ ይባላል:: ጥሩ ክፍል አግኝተናል::

ከውጭ በየጥጉ፣ በየበረንዳው የፈሰሰው መኮንን ለጉድ ነው:: አዳራሾች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቢሮዎች ጢቅ ብለው ሞልተው ከዚህ የተረፈው ነው እንግዲህ ውጭ የፈሰሰው:: ትንሽ እርሾ ያላቸው ከቤታቸው ድንኳን አስመጥተው ወጣጥረዋል:: በዚህ ሰባያ ታዲያ ብዙ ጥፋቶች ጠፍተዋል::

እነዚያ የሚያማምሩ የጥድ ተክሎች ወድመዋል:: አበቦች ጨርሰው የሉም:: የሰውም እግር እንደ እሳት ነው መሰል በጥቅጣቆ ከስለዋል:: ትምህርት ቤቱ ተዘርፎ የጠበቀን ቢሆንም እኛም ድርሻችንን አበርክተናል::

መፃሕፍት እየተቀደዱ ለመጓታ ጉዝጓዝነት ውለዋል:: ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካና አሜሪካ ግንጥልጥል ብለው ድራሻቸው ጠፍቷል:: ወታደራዊ ካርታዎች እየተገነጠሉ ለምንጣፍ ውለዋል:: ጥቁር ሰሌዳዎች ከየተሰቀሉበት እየወረዱ በየጥጋጥጉ ለመኝታ ከለላ ውለዋል:: ወንበሮችና ጠረጴዛዎች ከየክፍሉ እየወጡ ባመቻው ቅርፅ በፋስ እየተፈለጡ የለት ጎጆ ተቀልሶባቸዋል:: የሶስት ቀናት የተሃድሶ ሰሚናር ንብረቶችንም እያደሰ ነው:: እኛን ብቻ አልሰባበረም::

የሚገርመው ግን ተቀዳደው ለምንጣፍ የዋሉትም ሆነ የተጣሉት የምእራባውያን መፃህፍትና የኛዎቹ ናቸው:: የምስራቃውያን ግን ከተደረደሩበት እንኳን ተንሸራተው አልወደቁም:: ክርችም ብለው እንደ ተደረደሩ ናቸው:: ከዚያው ቤተ መፃህፍት ከሚገኙት ውስጥ አንዱን መኮንን:-

"ምናለ ካድ ጠቃሚ የሆኑትን መፃህፍት ባትቀዳድዷቸው:: ይልቅ እነዚህን ብትቀዳድዷቸው ይሻል ነበር" ስለው:-

"የነዚህን ውሾች መፅሀፍ መንካትም አያስፈልግ!" አለኝ:: ቢጨንቀኝ ሳኩኝ፣ ለካም መጣላትም ያስከብራል::

አንድ የፈረደበት መኮንን ታዲያ ከዚህ ሁሉ ዘረፋ የተረፈ አንድ ፓኬት ደስጣ ወረቀት አግኝቶ ከተማ ወስዶ ሊሸጥ ሲል ተይዞ ዛሬ ጧት በኛ ፊት ተሸክሞ ዞሯል:: እኛ እንኳን መታወቂያው ከኪሱ ተገኘበት እንጅ "የከተማ ዱርየ አምጥታችሁ አትስደቡን" ብለን ነበር:: ይኸም ሆኖ አልተረታንም:: "መንግስቱ ሀይለማርያም ከየበረንዳው

እያፈሰ ማእረግ የለጠፈለትን ሁሉ ሰብስባችሁ አትስደቡን!" ብለናቸው ስብሰባውን ጥለን ተበተን::

ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን መጥተን ሁለተኛ ሳምንታችንን ይዘናል:: እስካሁን ምንም አይነት ወሬ የለም:: ሻምበል አዱኛ ደቻሳ አስቀድሞ አውቆታል:: አስር ጊዜ የሚሉን:-«ተመዝገቡ» ነው፤ እስካሁን ወደ አምስት ጊዜ ተመዝግበናል:: ቁምነገር ያለው አይደለም:: ዝም ብለው አስቀመጧቸው እንዳይባሉ ነው:: ስም ከነ ማእረግ፣ ያባትና ያያት ስም፣ የትምህርት ደረጃ፣ ያገልግሎት ዘመን፣ የጦር ክፍል፣ ልዩ ሙያ የሚል ይኖኝበታል:: አንድ ጊዜ ብቻ የተመዘገብነው ይበቃ ነበር::

ግን ደርግ እንዴት አድርጎ ባምሳሉ ቀርፆን ኖሯል? ዛሬ ነው በውል ያጤንኩት:: የሚገርም ነው፤ ሙቶ አለቃው ሻምበል፣ ሻምበሉ ሻለቃ ነኝ እያሉ ማእረግና ደመወዝ እየጨመሩ የተመዘገቡ ብዙ ናቸው:: እኔ እንኳን ሁለት የማውቃቸውን መኮንኖች ባይኔ አይቼ ታዝቤያለሁ:: አንደኛውንማ ሻምበል አላስችል ብሎኝ::

"ከመቼ ጀምረህ ነው ሻለቃ የሆንከው ጓድ ሻለቃ?" ብዬ ጠየኩት:: እንደ ማፈር ብሎ:-

"በሚያዝያ ወር ተሰጥቶኝ ነበር:: ሳልበላበት ጉድ ሆንኩኝ እንጂ" አለኝ:: እኔ ግን ከግንቦት ሀያ በፊት የሻምበል ማእረጉን አድርጎ አይቼዋለሁኝ::

የኢሰፓ አባል የነበሩትም፣ «አይደለንም» እያሉ ተመዝግበዋል:: ይኸ ሁሉ ቀላል ነው:: እኔን የከበደኝ ኢህአዴግ ለተማሩ መኮንኖች ልዩ ቦታ ይሰጣል የሚል ወሬ ስለተናፈሰ ጥቂት ብልጦች ዲግሪ አለን እያሉ መመዝገባቸው ነው:: ማስረጃ አቅርቡ የተባሉ እንደ ሆነ መቅለላቸው ነው:: አንዱን ሙቶ አለቃማ ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚማር መሆኑን ደህና አድርጌ አውቃለሁኝ:: መቼም ኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር ነው ያለባት ብሎ ነው መሰል፤ «በፖለቲካል ሳይንስ ምሩቅ ነኝ» ብሎ ምዝግብ:: ቀና ሲል እኔን ከጀርባው ቆሜ ወረቀቱ ስጠብቅ አየኝ፤ ቢሞት በወደደው:: "አይዞህ" አልኩት:: እውነቴን ነው:: መመኘት ወንጀል አይደለም:: ባይሆን ትንሽ በዛ እንጂ::

በስነ ምግባር ብልሹነት ከሰራዊቱ የተባረሩም ተገልለው የቆዩባቸውን አመቶች ሁሉ ደማምረው፣ ደመወዛቸውንም ጨምረው ተመዝግበዋል:: መቼም ነገረኛ ነኝ አንዱን ሙቶ አለቃ ጠጋ ብዬ:-

"ጓድ ሙቶ አለቃ! ከሰራዊቱ ተሰናብተህ አልነበረም እንዴ? መቼ ተመለስክ? ነው ጥሪው አንተንም ይመለከታል?" አልኩት:: ይኸስ የዋዛ አይደለም::

"አንተንስ ከምንየው ኢህአዴግ መለመለህ?" ብሎ ቀንዶን አለኝ::

በርካታ ወታደሮችም፣ «መኮንኖች ነን» እያሉ ተመዝግበዋል:: ይህ ሁሉ ሲሆን ኢህአዴጎች ዝም ብለው መመዝገብ ነው:: ማስረጃ አይጠይቁም:: ነገረ ስራቸውም አያምር::

ተመዝግቤ ስመለስ የቀድሞ አለቃየን፣ ኮሎኔል ዘርጋውን አገኘኋቸው:: እሳቸውም ተመዝግበው መመለሳቸው ነበር::



"ደህና አርፍደሃል ጎርፉ" አሉኝ:: እኔን ሲያዩ ፊታቸው በመጠኑ ፈታ አለ እንጅ ተከፍቶ ነበር::

"ደህና ነኝ ጌታዬ፤ እስዎስ በርትተዋል?"

"ምኑን እበረታዋለሁ ብለህ፣ ተለዋውጬ" አሉ ፊታቸው መልሶ እየጨፈገገ:: ጊዜ ጥላቸው እንጅ እንዴት ያሉ ጀግና ነበሩ:: የሶማሌ ሰራዊት የሳቸው ስም ሲጠራ መድረሻ ነበር የሚያጣው::

"አይዞዎት ጌታዬ! ሁሉም ነገር ያልፋል::"

"በርግጥ ያልፋል:: ግን ደግሞ እስከሚያልፍ ያለፋል" ፊታቸው እየቀደመ ይጨማደድ ጀመር::

"ቢሆንም መበርታት ነው::"

"በልስቲ" አሉኝና "ለመሆኑ በየቀኑ ተመዝገቡ የሚሉን ለምንድን ነው? የዛሬውም ከመሰንበቻው የተለየ ነገር አላየሁበትም" አሉኝ::

"ጊዜ ለመውሰድ ካልሆነ በስተቀር ምንም አይነት ልዩነት የለበትም::" እያወራን ሄደን ከሀውልቱ ስር ተቀመጥን::

ኮለኔል ዘርጋው በረጅሙ ተነፈሱና ፊታቸውን ቅጭም አድርገው:-"አንድ አባባል አለኮ ጎርፉ" ሲሉኝ:-

"ምን?" አልኳቸው ቀልጠፍ ብዬ::

'ትንሽ ሰው ትንሽ ነው ከትንሽ አትዋሉ!
አጥፍቶ ጠፊ ነው አገርን በሙሉ' የሚል::

"እየውልህ! ደርግ እሱም ጠፋ፤ አገሪቱንም አጠፋ:: እኛም ከሱ ተጠግተን ጨኽን ጨኽን በመጨረሻ መፈክር ብቻ ታቅፈን ቀረን:: አስበውስቲ ግራ እጃችንን ወጥረን፣ 'ይውደም! እናወድማለን!' ብለን እኛ ወደምነው:: አባቶቻችን 'እረጋሚ ተረጋሚ ነው' ይላሉ:: 'ስር ነቀል አብዮት!' እያልን ተነቅለነው ቀረን::" አገሪቱንም እስከ ወዲያኛው ድረስ እንዳትነሳ አድርገን ነቀልናት::

"እየህ፤ ህዝብ ያልተቀበለው መሪ ምን አዋቂ፣ ምን ብልህ ቢሆን አገር ሊመራና ሊያስተዳድር አይችልም:: የመንግስቱ ችግርም ይኸው ነበር:: ጀኔራሎቹ ከፊት ለፊቱ፣ 'አብዮታዊ መሪያችን! ቆራጡ!' ይሉታል:: ዘወር ሲል ግን 'ይህ ቅርንጫፍ! እንዴት በሱ እንመራለን?' እያሉ ይዶልቱበታል:: እሱም እንደሚዶሉቱበት ደህና አድርጎ ያውቃል:: ለዚህም ነው በየምክንያቱ አንድ ባንድ እየገደለ የጨረሳቸው:: የቀሩትም መፈንቅለ መንግስት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ:: ያው እነሱም አለቁ:: በመጨረሻም ጠሩ ያለ መሪ ቀረና ተበታተነ:: የኔ ስጋት ታዲያ ዛሬ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" አሉኝ ወደኔ መለስ ብለው::

"ምንድን ነው?" አልኳቸው እኔም ወደሳቸው አትኩሬ እየተመለከትኩ::

"መቼም ለመሪ አልታደልንም:: መሪ የምናገኝ አይመስለኝም:: ሰውኮ የለም:: ተመትሯል!"

"ልክነዎት ጌታዬ! የኔም ስጋት ይኸው ነው:: እንዳሉት መንግስቱ ሀይለማርያም በህብረተሰቡ ዘንዳ ተቀባይነትን ባለማግኘቱና

በግል በተጠናወተው ባህሪው በጭፍጨፋ ለመግዛት ሞከር አልተሳካለትም። እንፀባራቂ ታሪክ እመሰርታለሁ ሲልም አሳፋሪ ታሪክ መሰረተ።"

"የመሪ ነገር ባፍሪካ ምድር እንደ እርግማን ተቆጥሮ በየጊዜው ጡንቸኛ እየተነሳ ያለውን ይዘርፋል፤ የተረፈውን ያወድማል። ልክ እንደ ባእድ ወራሪ። ይህም ለመሪ አለመታደል ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ትናንት በጦርነት፣ ትናንት በርሃብ የተንገረገብነው ይበቃን ነበር። ያለም መሳቂያና መሳለቂያ ሆነናል። ሌላው ቢቀር ካለፈው ውድቀታችን እንኳን ልንማር በተገባን ነበር።

"መንግስቱ ሀይለማርያም ሶሻሊዝምን ከሶቭየት ህብረት እንደ ሸቀጥ ባንቴናቭ ጭና በማምጣት፣ 'ለሰላም፣ ለእኩልነት፣ ለብልፅግና፣ ለዲሞክራሲ...' እያለ ኢትዮጵያን 'የዳቦ ቅርጫት አደርጋታለሁ' በማለት አስራ ሰባት አመታት አናፍቶ አናፍቶ ሰውም ንብረትም አውድሞ ሲጨርስ ጥሎ ፈረጠጠ!

"አፄ ቴዎድሮስ ላገራቸው ክብር ሲሉ ሽጉጣቸውን በመጠጣት ህይወታቸውን አሳልፈዋል። መንግስቱ ግን ክብር የሌለው ሀሊና ቢስ በመሆኑ ያገሪቱን ክብር ባለም ፊት አስገፍፍዋታል። ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት መሪ በታሪኳ ውስጥ አጋጥሟት አያውቅም! ይኸ ሁሉ ውርደት የደረሰባት እንግዲህ ከመጀመሪያው አእምሮው የበሰለ መሪ በማጣታችን ነው። ያለፈውስ አለፈ፤ ዛሬ ምን ይበጀን?"

"እምን አስገፍፍዋታል። ክብር አሳጥቷታል።"

"የዛሬው የበለጠ ያሳስባል። ሶቭየት ውስጥ አሜሪካ ገብታለች። ያጣቻትን ኢትዮጵያን እንደገና ጨብጣለች። መመሪያችን ማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝም መሆኑ ቀርቶ 'ካፕኒዝም' ወይንም 'ዲሞክራሲ' ሆኗል። እጣ ፈንታችን ሆና የመጣውን መቀበል እንጅ የመቃወም ወይንም የማስተካከል እድሉ ተሰጥቶን አያውቅም። የማርክሲዝም የሌኒኒዝም ፍልስፍና ያጎናፀፈን ፀጋ ረሃብ፣ ጦርነት፣ ስደት እንደሆነ ሁሉ ዲሞክራሲም ዘረኛነትን፣ ጎሰኝነተን ይዞልን መጥቷል። ተበታትነነው እናርፈዋለን። ይኸ ሁሉ የመሪዎች ገፀ በረከት ነው።

"በመሰረቱ ዲሞክራሲ በራሱ ሰላም አያመጣም። ሶቭየት ህብረት ኢትዮጵያን በአፍሪካ የሶሻሊዝም ሞዴል እንዳደረገቻት ሁሉ ዛሬ ደግሞ አሜሪካ የዲሞክራሲ ሞዴል ልታደርጋት ሽርጉድ እያለች ነው። ይህን ሴራ ማክሸፍ ያለበት ህዝቡ ነው።"

"እምን፤ ህዝቡ ነው ከንግዲህ የድሉ ወሳኝ መሆን ያለበት፤ አለበለዚያማ ምኑን ዲሞክራሲ ሆነው? ያሜሪካን ህዝብ ራሱም አይደል መሪውን የሚመርጠው? የኛም ህዝብ መሪውን መምረጥ መቻል አለበት" አሉኝ።

"አንድ ቁም ነገር ግን አለ ጌታዬ! ደርግ ሶሻሊዝምን አራምዳለሁ ብሎ በፈጠረው ጭፍን አመራር ራሱ ባጠመደው ወጥመድ ገብቶ እንደ ተሽመቀቀ ሁሉ እነዚህም ዲሞክሲን እናራምዳለን ብለው ጀምረው ከመርሁ ካፈነገጡ ያው የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል። በዲሞክራሲ የተሸፈነ የጎሳ መርህ ጎስ ሆነው እንዳይቀሩ እሰጋለሁ።"



"እህ፤ እኛንም ጎስ አድርገው እንዳያስቀሩን እንጅ ጎርፉ" አሉ፡- እንደ መሳቅ ብለው።

ለትንሽ ጊዜ ወጭ ወራጁን እያየን ዝም ብለን ቆየንና "እንዲያው ግን ይኸ ሁሉ መኮንን ነው ብለህ ታስባለህ? እኔማ የመርካቶ ዱርዬ ሁሉ አብሮን መጥቷል እያልኩ አስባለሁ።"

"ግምትዎ ልክ ነው። ቦርድ የወጡና በስነምግባር ብልሹነት ከሰራዊቱ የተባረሩ ሁሉ መጥተዋል። የማውቃቸውን አግኝቻለሁ። የመኮንንነት ክብር ከቀረ ቆይቷል ጌታዬ።"

"ልክ ነህ። የሞትነው ለክብራችን መሞት ሲያቅተን ነው። ለዚህ ደግሞ ስምና ክብር የሌላቸው ግፋፎዎች መሩን! ስማልባ ሆነን ቀረነው" አሉና በፀፀት ራሳቸውን ነቀነቁ። እውነታቸውን ነው። ጥሩ ስም ነበራቸው። ዛሬ ግን ስም የላቸውም። እናታቸው ያወጡላቸው ስም ዘርጋው ብቻ። ማእረግ ይጨመር ከተባለም፡- «የደርግ ኮለኔል» ተብለዋል። የምስራቁ ጀግና ለዚህ በቅተዋል።

ከኮለኔል ዘርጋው ጋር ጨዋታ ይዘን ሳይታወቀን ከምሳ ሰአት ደረስን። መኮንኖች ሲሰለፉ ይታየኛል።

"ጌታዬ፣ የምሳ ሰአት ደርሷል፣ እንሂድ" ስላቸው፡-

"ትንሽ ያገልግል እንጀራ አለችኝ፣ እንሂድና እሷን እንካፈላት" አሉኝ፣ ከተቀመጡበት እየተነሱ።

"እንግዲያው እሷን እርስዎ ይጉረሷት። እኔ ልሂድና ከብዙሃኑ ጋር ልጋፋ" አልኳቸውና ቀደም አልኩኝ።

"ተው ግዴለህም" አሉኝ ከተል እያሉኝ።

"ግዴለም ጌታዬ፣ በሌላ ቀን ይጋብዙኛል" ብያቸው ነጠቅ ነጠቅ እያልኩ ተራመድኩ።

የምግብ ቤት ሰልፍ በመጠኑ ተሻሽሏል። ችግሩ ሊቃለል የቻለውም ሁለቱም ክፍለ ጦሮች ለየራሳቸው ምግብ ቤቶች በመክፈታቸው ነው። ምግብ ቤት ተከፍቶ ስል ግን ሳላወቀ እንጀራ ተጋግሮ፣ ወጥ ተሰርቶ የሚሰጠን ሊመስል ይችላል። ደረቅ ኮቸሮና ሻሂ ነው። አልፎ አልፎ በአራት ሰአት መኮረኒ ይቀቀልልናል።

ይልቅየ ይህን ሰሞን አንድ በላስቲክ የታሸገ ምግብ ታድሎናል። አንዱ እሽግ ለሁለት ለሁለት ነው የተሰጠን። በፈረንጅኛው ፅሁፍ ግን «አንድ ላንድ» ይላል። ምናልባት አንዱ የፈረንጅ ሆድ ሁለት ያበሻ ሆድ ይወጣው ይሆን እንጃ? በርግጥም ውቅያኖስ አቋርጦ፣ አየር ሰንጥቆ መጥቶ እንኳን የበሰለውን ጥሬውንም ቁርጥምጥም ነው የሚያደርገው። ይህም ሆኖ የፈረንጅን ሆድ የሚያጠግብ ነገር የለም።

መቼም የምእራቡ አለም ደግ ነው። ቀለምና ነገር የበላው ነው። ጦርነት ቢያስነሳም መድሃኒት ይልካል፤ ጥሬ እቃ ቢመዘብርም መልሶ እርዳታ ይሰጣል። ለኛም ይህን ሰሞን ከምግቡ ሌላ አንድ የምእራብ በጎ አድራጊ ድርጅት ብርድ እንዳይበርደን በማሰብ ብርድ ልብስ ልኮልን ነበር። የት እንደገባ አጣነው እንጂ። ብርድ ልብሱ ግን ቢሰወርም ተገቢ ነው። ቡስቅ ያለ ነው። ይኸ ሁሉ እያቆሰለን ነው። የሚያቆስለንስ ሞልቷል። ገና ምን ተይዞ...

# 12

ገነት ጦር ትምህርት ቤት ከገባን ጀምሮ በትምህርት ቤቱ አጥር ዙሪያና በግቢው ውስጥ ለውስጥ ሻሂና ቡና አፍሊዎች እንደ አሸን ፈልተዋል:: እኛ ደግሞ እየገዛን መጠጣት ነው:: በተለይ ኮረዳ ቢጤ ከሆነች አስር ሀያው መኮንን ከቦ ዝንብ ሲከላከልላት ይውላል:: ጭሱ ተጥመልምሎ ወደ ሰማይ ሲወጣ ሀዳር ሚካኤል የታጠነ ይመስላል:: ካጥሩ ወጣ ሲሉ ደግሞ አረቂው ለጉድ ነው:: ያን እየለጉ የሚደነፉ መኮንኖች ብቅ ብቅ ማለት ይዘዋል::

ዛሬ ተረፋዱ ላይ ካንዱ መኝታ ክፍል ስገባ ስድስት መኮንኖች ውስኪ አቅርበው ይጠጣሉ:: ሁለቱ ገንዘብ ቤቶች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ ደመወዝ ከፋዮች ናቸው:: እንዴት ተጠቃቅሰው እንደ ተገናኙ ደግሞ ገረመኝ:: ድፍረታቸውስ:: ሰው ለካ ተስፋ ሲቆርጥ እንደዚህ ነው:: ሞቅ ስላላቸው አስተውለው እንኳን አላዩኝም:: እኔ ግን ባይኖቼ ፎቶ አንስቻቸው ወጣሁና ወደ ሀውልቱ ሳቀና ኮለኔል ዘርጋውንና በድሉን ቁመው ሲያወሩ አየኋቸው:: ሄጄ በመጨመር:-

"እግር ጥሎኝ ካንድ ክፍል ገብቼ አይኔ ጉድ አየ" አልኳቸው::

"ምን አየህ?"አሉኝ ኮለኔል::

"ደመወዝ ከፋዮችና ገንዘብ ቤቶች ከመኝታ ክፍላቸው ውስኪ አስመጥተው ይጠጣሉ::"

"ዛሬ ነው እንዴ ያየሃቸው? ከመጡ ጀምረው ውስኪ መቼ ተለይቷቸው ያውቃል:: ታዝበን ታዝበን ትተናቸዋል" አለኝ ሻምበል በድሉ::

"ይሉኝታ ማጣት ነው ወይንስ ንቀት? ለምን ከተማ ሄደው አይጠጡም!" አልኩኝ ቆጣ ብዬ::

"እስቲ ለሁሉም እንቀመጥ?" አሉ ኮለኔል ትክት ባለ አነጋገር:: ወደ ላይ ወጣ ብለን ከዛፉ ስር ተቀመጥን::

"ታሪካችን ተበላሸኮ ጌታዬ" አላቸው በድሉ::

"አየ በድሉ፤ ምን ታሪክ አለን ብለህ? ያለፈው ውርደት አልበቃን ብሎ ተግዘን እንኳን ከውስኪ መለኪያ መላቀቅ ሲያቅተን ምን ይባላል:: ወይኔ ዘርጋው!" አይኖቻቸው ደም ለበሱ:: እሳቸው ስላመረሩ የኛም ፊት ተከሳተረ::

"ክብራችንን አጥተን የተዋረድነው ከላይም፣ ከታችም በክብረ ቢሶች ስለተከበብን ነው:: ሆዳም ሰው ድሮም ቢሆን ክብርና እምነት የለውም:: አስቡትስቲ ጎበዝ! ዛሬ ሎሚ የምንቆርጥበት፣ ውስኪ የምንጠጣበት ወቅት ነው? እንደ መንጋ ከብት ተነድተን መምጣታችን ሊያንገበግበን ሲገባ ከመኝታ ክፍላቸው ውስኪ አምጥተው መጠጣት ምን ማለት ነው? ወያኔዎችኮ በነዚህ እንገዛም ብለው ቢወይኑ አግባብ አላቸው:: የሰው ልጅ ክብር ከሌለው ይሉኝታም የለውም:: ይሉኝታ ከሌለውም አዙሮ የሚያይበት አንገትም የለውም፤ አንገት ከሌለውም እንስሳ ነው፤ ቢጭኑት አህያ ቢያርዱት የሚታረድ ከብት!" በተናገሩ ቁጥር ደማቸው ይፈላ ጀመር:: ዘወርወር ብለው አዩና:-



"ሌላው ቢቀር 'ተመልካች ምን ይላል?' ማለት ነበረባቸው:: እንዴ! አብረንኮ ነው የምንሰደበው ምነው ጎበዝ" ሲሉ እኛ ያጠፋን ይመስል ገላመጡን:: እውነታቸውን ነው፤ ትናንት ኢህአዲጎች ሰብስበው ጥንብርኩሳችንን ነው ያወጡን::

የኢህአዲጎቹ ተወካይ ነበሩ የሰበሰቡን:: ፊታቸው ምጥጥ ያለና የቀይ ዳማ ናቸው:: ማእረጋቸው ኮለኔል ነው:: «ማእረግ አነሰኝ» ብለው ነው ወደ ኢህአዲግ የገቡት:: የጎሳ ልጓም ጎትቷቸው እንጅ ዛሬም ቢሆን ያው ኮለኔል ናቸው::

"ዛሬ የምንነጋገረው ስለ ስርአት አልበኞች ጉዳይ ነው" አሉ፣ ንግግራቸውን ሲጀምሩ:: ሁለቱንም ክፍለ ጦሮች ነበር ለጥ ካለው አስፋልት ላይ የሰበሰቡን:: "በርግጥ ባጠቃላይ መኮንኖችን ለመውቀስ ያስቸግራል:: ጥሩ ስነምግባር ያላቸው መኮንኖች አሉና:: ግን ደግሞ አንዳንድ ከስነስርአት ውጭ እንሁን የሚሉ መኮንኖችን ዝም ብለን አናያቸውም:: የስነስርአት እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን:: እኛ መጠጥ አትጠጡ አንልም፤ ጠጥታችሁ ግን አትስደቡን! ትናንት ማታ ሁለት መኮንኖች ከመጠን በላይ ጠጥተው ይሰክሩ ይመጡና የበር ዘቦችን 'ቅማላም ሁሉ! እናንተ ናችሁ እኛን የምታሸንፉን? አውቀን ተሸነፍንላችሁ እንጅ' እያሉ ደነፉ:: በፈጠራችሁ! አረቂ ስትጠጡ ነው እንዴ ወንድነታችሁ የሚነሳው? ጀቱን፣ ታንኩን፣ መድፉን ይዛችሁ ያልተሳካላችሁ ዛሬ ባረቂ ጥይት ድል ለመቀዳጀት ትመኛላችሁ!" ሲሉን ቢጨንቀን አቋርጠናቸው ሳቅን::

"እባካችሁ አትስደቡን:: ተከበሩ! እናክብራችሁ:: አለበለዚያ በዚህ መልኩ የምትቀፅሉ ከሆናችሁ የስነስርአት እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን እንድታውቁት" በማለት ነበር ንግግራቸውን የጨረሱት::

ስለመጠጥና ጠጭዎች አንስተን ስናወራ ከወደላይ በኩል ሶስት መኮንኖች የቆጥ የባጡን እየቀባጠሩ መጡ:: በተራመዱ ቁጥር እግሮቻቸው ወዲያና ወዲህ ወልከምከም ይላሉ:: ጨዋታችንን አቁመን ወደነሱ አተኮርን::

"ቅ... ቅ... ቅማላም ሁሉ! በ... በ... በነሱ እንሸነፋለን!!" አለ አንደኛው መኮንን

"ባ... ባ ... ባሪያው ነው ጉድ የሰራን" ሲል ሁለተኛው መለሰ::

"ባሪያው! ባሪያው! ትላላችሁ! እሱ ምን ያድርግ? ጉድ የሰሩንስ ጀኔራሎቹ! ዝምበሉ አሁን! ሰካራም ሁሉ!" አላቸው ሶስተኛው:: ይኽ በመጠኑ ሚዛኑን እንደጠበቀ ነው::

"ተ... ተው እባክህ! እናግረን ይውጣልን! እ... እስከዛሬ የታፈነው አይበቃም!" በማለት የመጀመሪያው ተናጋሪ እንደ መወራጨት ሲል ሊወድቅ ነበር፤ ሳደኛው ደግፎ አስቀረው::

ኮለኔል ዝም ብለው ሲያዩ ቆዩና "እኔ እምለው ተስፋ መቁረጥ ይሆን እንዲህ የሚያደርጋቸው?" አሉ::

"በርግጥ አንዳንዶቹ የሶስት ቀናቱ ሴሚናር ስለቀረ ተስፋ ቆርጠው ሊሆን ይችላል:: አንዳንዶቹ ግን የቆየ ልማድ ስላላቸው ነው" ስላቸው:-

"እረ ወዲያ!" ብለው እጃቸውን አወራጭተው ከተቀመጡበት ተነስተው ሲሄዱ በድሉ ተከተላቸው:: እኔ ግን እንደ ተቀመጥኩ ቀረሁ:: ፍዝዝ ብዬ ነበር ወጭ ወራጁን የማየው:: እረ የስካር ነገር ቅጥ እያጣ መጣ:: ከዛፍ ስር ሳይቀር ወድቀው የሚያነጉ አሉ:: ሲደጋገም የራበው ጅብ እንዳይዘረክታቸው እንጅ፤ ሰሞኑን ደግሞ ሲጮህ ነው የሚያድረው:: አንዳንድ መኮንኖች «የረሃብ ምልክት ነው» ሲሉ ሌሎች ደግሞ «የለም! የጦርነት ምልክት ነው» ይላሉ:: ከንቱ ትንበያ ነው:: ሁለቱንም ይዘናቸዋል:: ርሃብንም፣ ጦርነትንም:: አንዱ መኮንን ያለው ይልቅ እውነትነት አለው::

"ጅብስ ደርግ ነው! ኢህአዴግ ደግሞ አሳማ ነው!" አለ በሽቆ::

እኔ ከምተኛበት ጎን ነው የሚተኛው:: እንዳጫወተኝ ከሆነ ያምስት ልጆች አባት ነው:: ደመወዝ ቶሎ ባለማግኘቱ ይበሳጫል:: ከአስራ ሁለት ሰአት በኋላ ተጠቅልሎ ነው የሚተኛው:: ጧትም ቶሎ አይነሳም:: ፊቱም ግጥጥ ያለና ርሃብ የጎዳው ነው:: ሚስቱንም ባለፈው እሁድ ልትጠይቀው መጥታ አይቻታለሁ:: ክስት ያለች ነች::

ወደ ሰው ብሶት ገባሁ እንጅኮ እኔም ብሶት አለብኝ:: በርግጥ እንደሱ ሚስትና ልጆች የሉኝም:: ለምን እንደ ሆነ እንጃ የኢትዮጵያ ሁኔታ እያሳሰበኝ መጥቷል:: ለነገሩማ አገር ሚስት ነች፤ አገር ልጆች ነች፤ አገር ሀብት ነች፤ ሲያገኙ መደሰቻ! ሲያጡም መለመኛ ወይንም መተከዣ:: ያለ አገር ምንም ነገር የለም:: አገር ከጠፋች ሁሉም ነገር ይጠፋል:: ዛሬና ትናንት ኢትዮጵያ የሚደሰቱባት ሳትሆን የሚያለቅሱባት፤ የሚኖሩባት ሳትሆን የሚሰደዱባት ሆናለች::

# ምእራፍ አምስት

ጥንት በልማዱ የኢትዮጵያ ገበሬ ነጭ ጤፍ ነበረ
ያመርት የነበረው!
ጊዜው ተለውጦ እንበጣው ደርግ ወጥቶ ቡቃያውን በላው!

## 13

ትናንት ማታ ግማሾቹ ከርታ ይጫወቱ ነበር:: ግማሾቹ ደግሞ በየመኝታቸው ላይ ጋደም ጋደም ብለው በሀሳብ ተደምመዋል:: ሬዲዮ ድንገት ጢርርር... ጢርርር... ማድረግ ጀመረ:: አዲሱ የኢህአዴግ ማርሽ መሆኑ ነው:: ሁላችንም ጆሮዎቻችንን አቀናን::

«የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢሰፓ መዋቅርና ድርጅቶች ከዛሬ ጀምረው ፈርሰዋል:: ሰራተኞቹም ተበትነዋል::» ከጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተገለፀ:: ሁላችንም



ተመስጠን ነበር ያዳመጥነው:: እኛ የተሰባሰብን መስሎን ነበር፤ ለካ ተበትነናል...

"መከላከያ ሚኒስቴር ፈረሰ ማለት ነው?!" አለ ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ወደ በድሉ ዞሮ:: ቀስ ብሎ መናገር አይሆንለትም:: ጮክ ብሎ ነበር የተናገረው::

"አትጩህ! ይፍረስ!" አለው በድሉ ቆጣ ብሎ:: ከሱ ቀና መልስ ሲያጣ ጊዜ ወደኔ መለስ አለና አይኖቹን አፈጠጠ::

"ምን እንደ ጉማሬ ትገላበጣለህ? አርፈህ አትተኛም" አልኩት:: ከዚህ በኋላ ትንፍሽ አላለም::

ስለወቅቱ ሁኔታ አንስቶ መወያየት አይቻልም:: ችግር ነው:: ወጥመድ ውስጥ እንገባለን እያልን እንሰጋለን:: ትግሬ መኮንኖችን የኢህአዴግ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ እያልን መፍራት ጀምረናል:: አብረው እንደኛው እየተሰቃዩ የጎሳ ጉዳይ በመሆኑ ልናምናቸው አልቻልንም:: በዚህ ላይ በደርግ ጊዜ ሲቋሰል የከበረው ሁሉ የጎሪጥ ይተያያል:: አብዛኛው ደግሞ ማን ምን እንደሆነ በውል አይተዋወቅም:: ውስጥ ለውስጥ የሆነ ያልሆነውን እሳብቀው ለመሾም፣ ለመሸለም የሚቅነዘነዙ መኮንኖች መታየት ይዘዋል:: ለገፀ በረከት እንዳያቀርቡን መጠራጠር ይዘናል::

ጧት ቁርሳችንን በልተን ከመነቃቀል ከተረፉት ቁጥቋጦዎች ስር ሄደን ተቀመጥን::

"ማታ እረ እንደዚያ ቀንዶን ያላችሁኝ ለምንድን ነው?" ሲል አዱኛ ጭውውታችንን በጥያቄ ጀመረው::

"ቀስ ብለህ መናገር አይሆንልህም፤ ኢህአዴግ በየመኝታ ክፍሉች የመለመላቸው መኮንኖች አሉ ይባላል:: እረ እባካችሁ ተጠንቀቁ" አለ በድሉ::

"ደርግ ትናንት የተፈጠረ ነው:: ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ግን ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው:: በርግጥ ኢሰፓና ሌሎች ድርጅቶች መፍረስ ይገባቸዋል:: የደርግ መጠቀሚያዎች ነበሩ:: የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርም ይፍረስ፤ አፋኝ መስሪያ ቤት ነበር:: የመከላከያ ሚኒስቴር ግን ከኢትዮጵያ መፍረስ ጋር ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: በመሰረቱ ጥፋተኞችን ለፍርድ ማቅረብና ለውትድርና አገልግሎት ብቁ ያልሆኑትን ማገለል ሲገባ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መዘጋት አልነበረበትም" አለ አዱኛ በመቆርቆር አይነት አነጋገር:: እኔም ሆንኩ በድሉ ፈጥነን መልስ አልሰጠነውም:: እራሱ መናገሩን ቀጠለ:-

"አላማቸው ግልፅ ነው:: ኢትዮጵያን በጎሳ ከፋፍሎ ለማፈራረስ ነው:: ፖሊስንም ያፈረሱት በከተሞች አካባቢ ሁከት እንዲፈጠር ነው:: በዚህ ግርግርም ንብረት ወደ ትግራይ ያጉዛሉ፤ ፋብሪካዎችን እየነቀሉ ይወስዳሉ፤ ኦሮሞንና አማራን ደም እንዲቃቡ ሳቸው ቅስቀሳ ያደርጋሉ፤ ይህ ደግሞ ለነሱ ምቹ ነው:: ከቻሉ አረግጠው ይገዛሉ:: ካልቻሉ የሚፈልጉትን አጉዘው ሲጨርሱ እስበሳችን እናክሰው ወደ ትግራያቸው ሙልቅ ይላሉ:: ከዚያ ከኤርትራ ጋር ተዋህደው አምባገነን ገዥዎች ይሆናሉ" አለና አሻግሮ ወደ መናገሻ ጋራ አተኮረ:: አስተያየቱ "አንተ ጋራ ፍረድ" የሚል ይመስላል::

ካገነበስኩበት ቀና አልኩና "ሌላውን ተወውና በጎሳ የመከፋፈላችን ጉዳይ ግን አሳሳቢ ነው:: አንድ ሆነንም አልተሳካልን፤ እንኳን ተበታትነን:: ህዝቡ እስካልነቃ ድረስም የገዥ መደቦች የሚያመቻቸውን መንገድ ከመምረጥ ወደኋላ አይሉም:: እኔ እንደሚገባኝ ዛሬ ለዚህ የከፋ ችግር ተፈታኞቹ እነሱ ሳይሆኑ ህዝቡ ነው:: ይህን ደባና ሴራ ማክሸፍ መቻል አለበት:: አለበለዚያ ግን የጎሳ ሆያ ሆየ ልንወጣው ከማንችለው ችግር ውስጥ ይከተናል:: በተረፈ ግን መከላከያ ሚኒስቴርንስ እንኳንም አፈረሱት! ግንብ ነበር:: ባዶ ህንፃ! ሰው የሌለበት!" በስተመጨረሻው በስጨት ብዬ ነበር የተናገርኩት::

"ሰራዊቱ ግን አያሳዝንህም? ላገሩ እንዳልደማ፣ እንዳልቆሰለና ለሀገሩ አንድነት ሲል በረሃ ለበረሃ እንዳልተንከራተተ ተቆጥሮ የትም ተበትኖ በገዛ አገሩ ለማኝ ሆኖ ሲቀር" አለኝ::

"ያሳዝነኛል፤ አንጀቴን ይበላኛል፤ ግን ለዚህ ሁሉ ውርደት ማን አበቃውና? ሰራዊቱን በትኖት የሄደው መንግስቱ ሀይለማርያም፣ ያብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ነው:: እሱ የበተነውን ሰራዊት ደግሞ ጠላት ሰብስቦ ይንከባከባል ማለት የዋህነት ነው::

"ሰራዊቱ እንደ ሆነ ድሮም አልደላው:: ሲንከራተት ነው የኖረው:: ለመንግስቱ ሀይለማርያምና ለጥቂት ደልቃቆች ሲሞት፣ ሲደማ፣ አካሉን ሲያጣ ኖሯል:: ከእንግዲህ ግን ለራሱ መሞት አያቅተውም:: መቼም እድሜውን ሙሉ ለማኝ ሆኖ አይኖር!

"በመሰረቱ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በዘመነ ደርግ ስሙ የጎደፈ፣ ሙያው የቆሸሸ ነበር:: በስመ አንድነት የህዝብ ሃብት እየተዘረፈ ለደርግ ቅምጥሎች ቤት መስሪያ፣ መኪና መግዣና መንደላቀቂያ ውሏል:: የነሱ ልጆች በካናዳ፣ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ ከመዋእለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ተልከው ሲማሩ የድሀው ልጅ እጣ ፈንታ ግን እየታፈነ ብሄራዊ ውትድርና መላክ ነበር:: የሚገርመው ግን ከናቅፋ ተነስቶ አዲስ አበባ እስከሚደርስ ድረስ 'አብዮታዊ ሰራዊታችን ግንባሩን አያጥፍም!' እየተባለ ከግል ወደ ቡድን ከዚያም ለወጥ አድርገው በብርጌድ፣ በክፍለ ጦር፣ በእዝ ደረጃ ቆርቆሮ እየቀጠቀጡ 'የጀግና ሜዳይ' በማለት ለማታለል መሞከራቸው ነው:: የነሱን እስትንፋስ ለማቆየት ይህ ሰራዊት የሱን እስትንፋስ ማጣት ነበረበት::

"የጦሩ ስምና አይነት ቢጠሩት ቢጠሩት አያልቅም:: አበው ሲተርቱ 'ዘጠኝ ሱሪ ከፈስ አያድንም' ይላሉ:: የእዙ፣ የግብረ ሀይሉ፣ የክፍለ ጦ ብዛት በትክክል አይታወቅም:: በየቀኑ አዳዲስ ስም ይሰየማል:: 'ናደው፣ ገረምደው፣ ውቃው፣ ሰንጥቀው፣ በርግደው፣ ተራራው፣ ስፓርታው፣ አየር ወለዱ፣ ፓራኮማንዶው፣ ሜካናይዝዱ፣ ሚሊሻው፣ ወዛደሩ፣ አብዮት ጠባቂው፣ ብሔራዊ ወታደሩ' ይኸ ሁሉ ሰራዊት ነው:: ሳር ቅጠሉ፣ ጎጣጎጡ ሁሉ ሰራዊት ብቻ ነው:: መሪ ግን የለውም...

"እንደ ሰራዊቱ መንጋጋት የልብሱ አይነትም ተቆጥሮ አያልቅም:: ዝብርቅርቅ ያለና ቅጥያጣ አለባበስ ነበር ይታይ የነበረው:: ያለ ምክንያት አይደለም ልብስን ያነሳሁት:: ያንድ ሰራዊት ግርማ ሞገሱ ልብሱ ነው:: አለባበሱ ያላማረ ሰራዊት ተመልካችን አይማርክም:: ተመልካችን ካልማረከ ደግሞ የውትድርና ሙያ አይከበርም:: ይናቃል::



መለዮው እራሱ የረኛ ጥሬ መቋጠሪያ ይመስላል:: ከዚህ ብሶ ደግሞ 'ባጅ' የለውም:: ታዲያ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከፊልም ቤት ዘበኛ በምን ይለያል? ይህ ሁሉ ተዕእኖ አድርጎበታል::

"ይህ ሰራዊት አስራ ሰባት አመታት ሙሉ ካገር አገር እየተንከራተተና ከምሽግ ምሽግ እየተፈራረቀበት፤ የራሱን ፀጉር እንኳን የሚላጭበት ጊዜ አጥቶ ቅማል በላዩ ላይ እየፈላበት የሰውነቱ እድፍ መገረና ሰርቶ የኤሊ ገላ መስሎ ቅርፊት አበጅቶ ከሰው እንዳልተፈጠረ ሲሆን ከጀርባው ግን ኀድ ደርጎች ጮማ እየቆረጡ በውስኪ ይራጩ ነበር:: ይህ ብቻ እልበቃቸው ብሎ ሀውልት ሳይቀር ይገነቡ ነበር:: በሱ ደምና አጥንት:: እየሞተ 'ገሗል መሰለኝ ዝናሩ ጎሗል' እያሉም አዘፍነውበታል:: ሲሮጥም ጥሎት ሲሆን ይችላል::

"እሱ እየተንከራተተ 'ልጄ እንኳን ተምሮ ይደርስልኛል' ሲል በቀበሌ ታፍኖ ካለበት ድረስ ተላከለት:: ታዲያ እንዴት ብሎ ለኢትዮጵያ ይሙትላት? ለዚያውምኮ አለገመም:: ሲያጠቃ 'ይዞታህን ለቀህ ተመለስ' ይሉታል:: ሲማርክ 'ልቀቅ' ይባላል:: 'ጥይት' ሲላቸው ኮቸሮ ይልኩለታል:: 'ኮቸሮ' ሲላቸው ጥይት ይልኩለታል:: በዚህ ላይ ሹመትና ማእረግ ለፈርጣጮች ይሰጣል:: ይህም አንጀቱን ያሳርረዋል::

"አንድ ጊዜ ከደብረታቦር የፈረጠጡ ባህርዳር ይገባሉ:: ቀሪዎቹ የጀግና አሸሻሸት እየሸሹ ከሶስት ቀናት ጉዞ በኋላ ባህርዳር ሲደርሱ ፈርጣጮቹ ሹመት በሹመት ሆነው ቆዩዋቸው:: እንዳይከሱ 'አብዮታዊ ሹመት ነው' ቢጨንቃቸው 'እንደዚህ ከሆነማ ቆይ ለወደፊቱ እኛን ማርቆስ ድረስ የሚቀድመን የለም' አሉ:: ይኸ ሁሉ የሰራዊቱን ሞራል ገሎታል:: ፈሪ መሪዎች ፈሪ አድርገውታል" በማለት ትንሽ ተነፈስኩ::

"ስለዚህ መከላከያ ሚኒስቴር መፍረስ አለበት ነው የምትለኝ?" አለኝ::

"አዎን፤ ሰራዊቱ ባጥፊነት ባይወቀስም በደርግ አምሳል የተቀረፀ ስለሆነ መፍረስ አለበት:: ከላይ እስከታች የተግማማ ነው" አልኩት:: በድሉ የሁለታችንን ክርክር በተመስጦ ያዳምጥ ነበር:: ሲበዛ ከመናገር ቁጥብ ነው::

በዚህ ላይ እንዳለን ኮሎኔል ዘርጋው ከወደፊት ለፊታችን መጡ:: መጠነኛ ፈገግታ ይታይባቸዋል:: ካጠገባችን ሲደርሱ ቁመታችንን ሙሉ ተነሳንላቸው::

"እረ በግዜር፤ እንደምን አረፈዳችሁ" ብለው እጃችንን ተራ በተራ ከጨበጡን በኋላ ከጎናችን ተቀመጡና:-

"ታዲያስ እንዴት ይዟችኋል?" አሉን::

"አለነው:: ሲመሽ ሲነጋ እናያለን" አልኳቸው::

"መኖር መልካም:: ይህን ማን አየበት" አሉ ላላ ባለ አነጋገር::

"ጌታዬ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በመፍረሱ ምን ተሰማዎት?" ሲል አዱኛ ጠየቃቸው::

"እናንተ ምን እንደተሰማችሁ እንጃ እንጅ እኔስ መፍረሱን አምኘበታለሁ::!"

"እንዴ! ጌታዬ አገሪቱኮ ተቆርቋሪ ሀይል ከሌላት ንብረት እየተዘረፈ ወደ ትግራይ መጓዙኮ ነው" ሲላቸው ፈገግ አሉና:-

"ሀገር መከላከያ ሚኒስቴርስ ኖሮ መች ከጥፋት አዳናት አዱኛ" አሉትና "ግዴለም ያጉዙ:: የትግራይ ህዝብ እንደሆነ ወገናችን ነው:: ወደ ሱዳን አያግዙ እንጅ:: ዋናው ነገር መከላከያ ሚኒስቴር እንኳንም ፈረሰ:: ለዚህ ሁሉ ውርደት የበቃነው አመራር ሰጭ በማጣታችን እንጅ ሰራዊት አንሶን ወይንም መሳሪያ አጥተን አልነበረም:: እርግጥ ለሽንፈታችን ብዙ ዘርፍ ሊኖረው ይችላል" አሉና አንገታቸውን ደፋ አድርገው ትንሽ አሰቡና:-

"ለውድቀታችን ተጠያቂው መንግስቱ ሀይለማርያም ብቻ አይደለም:: ጀኔራሎቹም ናቸው:: ወይ ታማኝ ሆነው ከልብ ማገልገል ነበረባቸው:: ወይ እሱን በወቅቱ አገር ሳያጠፋ ማጥፋት ነበረባቸው:: ወይ 'አልቻልንም' ብለው ስልጣን መልቀቅ ነበረባቸው:: አስራ ሰባት አመት ሙሉ በሱና በጀኔራሎቹ መካከል የድብብቆሽ ጨዋታ ይካሄድ ነበር:: በመካከሉ ግን ይኸ ሰራዊት እንደ ቅጠል ይረግፋል::

"ጀኔራሎቹ መንግስቱን ከሰራዊቱ ነጥለው እርቃኑን ለማስቀረት ሲሉ ሰራዊቱን በተለያዩ መንገዶች ይረሽኑት፣ ያስሩት፣ ያሰቃዩት ነበር:: ሰራዊቱ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለመንግስቱ ከፍተኛ አክብሮት ነበረው:: ጀኔራሎቹን ግን በጠላት አይን ነበር የሚያያቸው::

"በዚህ የተነሳም መንግስቱ በጀኔራሎቹ ላይ እምነት ስለሌለው እስከ ብርጌድ ጦር ድረስ እሱ ሳያውቀው ከመከላከል በስተቀር የማጥቃት ዘመቻ ማካሄድ አይቻልም:: የክፍለ ጦር፣ የብርጌድ፣ የሻለቃ አዛዦች የውጊያ እቅድ አውጥተው ጦራቸውን በመረጡት ጊዜና ቦታ ማዝመት አይችሉም:: ሁሉም ነገር ከላይ መጠበቅ አለበት:: ከላይ የሚወጡት የውጊያ እቅዶች ደግሞ ምስጢሮቹ ለባላጋራ ከወገን ቀድመው ስለሚደርሱ ሽንፈትን ያፋጥናሉ::

"የመረጃ ሰራተኞቻችንም 'ስኳር፣ ጨው፣ ካኪ ተሸጠ' እያሉ ከመሯሯጥ በስተቀር ከጠላት ጓዳ ገብተው የጣመ መረጃ አያመጡም:: እንዲያውም በገንዘብ እየተገዙ የኛን የሚያቀብሉ ሞልተዋል::

"የፖለቲካ ሰራተኞቻችንም 'ሌኒን እንዳለው፣ ማርክስ እንዳለው፣ ኤንግልስ እንዳለው፣ አሁን አሁን ደግሞ አብዮታዊ መሪያችን ባንድ ወቅት እንዳስገነዘቡት' ከማለት በስተቀር ሌላ ነገር አያውቁም:: ቢያውቁም ከዚህ ውጭ እንዲሉ አይፈቀድላቸውም:: በዚህ የተነሳ ጦሩ እያደር ደነቆረ፤ ደነዘዘ...

"የጀኔራሎቹ ደባ በዚህም አያበቃ:: ጦሩ በጠላት ጦር እየተመታ ባፈገፈገ ቁጥር እንደገና በማጠናከርና ሞራል በመስጠት ፋንታ ቀድመውት ይፈረጥጣሉ:: አዛዥ ከሌለ ደግሞ ጦር አውራ እንደሌለው ንብ ማለት ነው:: የጀኔራሎቹ ሽሽት ወይንም ፍርጠጣ ሁለት አይነት ገፅታ አለው:-

"አንደኛው ሽንፈቱ የመንግስቱ ሀይለማርያም ሽንፈት ብቻ እየመሰላቸው ይረኩበታል:: ለዚህም ነው እያንዳንዱ የጦር ግንባር 'ጀኔራሎቹ በብዙ ሺ ብር ሸጡት' እየተባለ የሚወራው:: ያገር ፍቅር ስሜት ያላቸው አዛገች ከጦሩ ጋር ሳይላቀቁ ሲደመሰሱ 'ጅሎች፣ መሸሽ ሲችሉ፤ እጃቸውን መስጠት ሲገባቸው' እያሉ ይስቁባቸዋል:: እራሳቸውን የሚገድሉትንማ 'እብዶች ናቸው' ነው የሚሏቸው:: መፈርጠጥ እንደ ጀግንነት የሚቆጠርበት ዘመን ነው:: ባጠቃላይ ጦርነቱ



የመንግስቱ ሀይለማርያም የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ፣ የጀኔራሎቹ መሾሚያ መሸለሚያ ነበር::

"ሁለተኛው የመሸሽ ገፅታቸው ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው ፈሪዎችና ሆዳሞች በመሆናቸው ነው:: የሚገርመው ግን ከሀላፊነት ቦታ የሚቀመጡት ደግሞ እንደነዚህ ያሉት ናቸው:: ለዚህ ተጠያቂው መንግስቱ ሀይለማርያም ነው:: ልብ እንደሌላቸው ስለሚያውቅ አገርን ሳይሆን እሱን የሚጠብቁትን፤ እሱ ከሌለ እነሱ መኖር እንደማይችሉ የሚያውቁትን ቁልፍ ቦታ ላይ ያስቀምጣቸዋል:: ከዚህ በኋላ እንደ እቃ ይጠቀምባቸዋል:: ጀግና ጀኔራሎችን ከሀላፊነት ቦታ ላይ ቢያስቀምጥ ለሱ እንደ ማይተኙለት ያውቀዋል::

"እነዚህ ጉልቻ ጀኔራሎች ግን ሴትና ገንዘብ ከማሳደድ በስተቀር ሌላ ነገር አያውቁም:: እያንዳንዱ ብርጌድና ክፍለ ጦር በተደመሰሰ ቁጥር ለመንግስቱ ጀኔራሎች ሰርግና ምላሽ ነው:: ገንዘብ ባካፋ ይዝቃሉ:: 'ጦሩ እንዴት ተጠቃ? የትስ ደረሰ?' ሳይሆን ጥያቄአቸው 'ገንዘቡ የት ደረሰ? ይኸ ብቻ ነወይ?' ነው:: ከዚህ በኋላ ገንዘብ ቤት፣ ደመወዝ ከፋዮች፣ ደህንነትና ፖለቲካ ሀላፊዎች ካዛዥ ጋር ተከፋፍለው ጦሩን እየመሩ ከተረጋጋ ይዞታ ሲደርሱ መንግስቱ ሀይለማርያም ተቀብሎ ይሾማል፤ ይሸልማል፤ የተሻለ ቦታም ይሰጣል:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ልስጣችሁ:-

"ሻምበል ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ ሆኖ ሲሾም ጀኔራል ሙላቱ ደግሞ የሱ የበታች ሆነው የጦሩ አዛዥ ነበሩ:: ውድቀቱን አይተናል:: ከዚህ በኋላ ነው ቅስማችንም ተሰብሮ የቀረው:: ለገሰ ግን የተሻለ ስራና ሀላፊነት ተሰጠው እንጅ የሆነው ነገር የለም:: ለዚህም ነው ጦሩ:-

«ለገሰ ሲሸሽ ቤተ መንግስት፣
ሚሊሻ ሲሸሽ በጥይት!» ብሎ የገጠመው::

ጀኔራል አበበ ሀይለስላሴ ደብረታቦር ላይ ጦሩን አስጨርሶ ወደ አዲስ አበባ ቢፈረጥጥ የሁርሶ ጦር ትምህርት ቤት አዛዥ ሆኖ ተሾመ እንጅ የሆነው ነገር የለም:: ይህ ድርጊትም ጦሩን አንጀቱን አቁስሎታል:: ጀኔራል አስራት ብሩም ከባህርዳር የፈረጠጠ በወለጋ ዞሮ አዲስ አበባ ሲገባ የሆነው ነገር የለም:: እንዲያውም ጊዜው አጥሮበት እንጅ ከፍተኛ ሹመትና ማእረግ ያገኝ ነበር::

"ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከመፈንቅለ መንግስቱ ወዲህ ሶስት ኢታማጆር ሹሞች ተሹመው ነበር:: አንዱን አንዱ ሲጠብቀው አንድ ነገር ሳይሰሩ እጃችንን አስጨበጡን! ኀዘዝ የሰራዊቱ ግፍ በዚህ አያበቃም:: አብዮታዊ ዲስፕሊን አስተባባሪ ኮሚቴ /አዲአኮ/ ተብሎ የሚታወቀው በ80 ዓ.ም. ፀድቆ ለጦር ክፍሎች ተበትኖ በተግባር ላይ ከዋለበት እለት ጀምሮ ወደር የሌለው ጭፍጨፋ ተካሂዷል:: ጦሩንኮ የጨረሰው ጠላት ሳይሆን ወገን ነው:: የዚህ ጭፍጨፋ አላማ የሚሸሹ ወታደሮችን ለመግታት ይሁን እንጅ ያለቁት ግን ከፖለቲካው ጋር መጣጣም ያልቻሉት ነበሩ:: በዚህ የተነሳም የጦር ክፍሎች ስማቸው

እንጅ ባዶ ነበሩ:: ጦሩክ ከሞተ ቆይቷል:: 'ሟች አውሬ ገዳዩን ያስመሰግናል' እንዲሉ ለወያኔዎች መፎከሪያ ሆንናቸው::

"ይህ ሰራዊት ሲመለመል ባፈሳ፣ ሲረሽን ባፈሳ፣ ቦርድ ሲወጣ በመንጋ፣ ሲሸሽም በጅምላ፣ በመጨረሻም እጅ ሲሰጥ እየተሻማ በጠቅላላ ሆነ!!" አሉና ከተቀመጡበት እንደ መወራጨት አሉ:: አይኖቻቸው መቅላት ይዘዋል::

"ጦሩ ሲሰለጥንም እንዲያሸንፍ ሆኖ ሳይሆን እንዲሸነፍና መሳሪያውን ጥሎ እንዲፈረጥጥ ሆኖ ነው:: ለዚህ ደግሞ የስነልቦና ጦርነት የሚካሄድበት ገና ከቀበሌ ሲታፈስ ጀምሮ ነው:: ከዚህ በኋላ በአእምሮው የሚታየው መግደል ሳይሆን መሞት ነው፤ መማረክ ሳይሆን መማረክ ነው::

"በየ ክፍለ ሀገሩ እንደ አስራት ወይንም ግብር ኮታ ተጥሎ የታፈሰ ወጣት ሀያ ሺና ሰላሳ ሺ ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለብ ለብ ተደርጎ ይወጣና 'አብዮታዊ ሰራዊታችን!' ይባልና በማስ ሚዲያ ነጋሪት ይደለቅለታል:: ነገር ግን አንድ ነገር ሳይሰራ ታፍሶ ይማረካል:: ኋላማ ወያኔ እያሰለጠነ ካድሬ አድርጎ ይልክልን ጀመር:: ወያኔ በዚህም አልተወሰነ፤ 'ጀግና ምርኮኛ መኮንኖችን ኢዲመአን' ብሎ በመሰየም ይኸውና ዛሬ ያተራምሱናል:: 'እሾህን በሾህ' እንዲሉ ...

"ለማያውቅ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ጦር ሰራዊትን በጠቅላላ የሚያዝ ይመስላል:: ግን አይደለም:: እንደ ደንቡ ማዘዝ ነበረበት:: ባዲስ አበባ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ክፍሎች፣ ሙዚቀኛን፣ የመቻል የስፖርት ክለብን፣ ማስተናገጃን... የመሳሰሉትን ከማዘዝ በስተቀር በሌላው ሰራዊት ግን ሀይል ከመቆጠርና ስንቅ ከማቀበል ሌላ የእዝ ሰንሰለትም ሆነ ስልጣን የለውም:: ታዲያ የምድር ጦር አዛዥ መሰንቆና ሳክሰፎን ይዘው አይዋጉ:: ወይንም ኳስ ተጫዋቾችን ይዘው አይሰለፉ:: ቢጨንቃቸው የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያን ዙሪያ አጥር ማስገንባት ያዙ:: ያውምኮ እምቦ ተይዛ ነው:: ምን ያድርጉ! ባይሆን ለጅ መንሻ ግንብ አስገንብተው ይቆዩ እንጅ" አሉና በሀይል ተነፈሱ ሲከነክናቸው የኖረውን ሁሉ ነው የሚዘከዝኩት::

"ሌላው የመከላከያ ሀይላችን አየር ሀይላችን ነበር:: አየር ሀይላችን ዛሬን አያድርገውና በኢትዮጵያ ህዝብ ተፈቃሪ ነበር:: በተለይ በምስራቁ ጦርነት ጊዜ ያሳየው ትርኢት ታሪክ እየቀረ ነው መሰል እንጅ ለዘለአለም ተከብሮ የሚኖር ነበር:: የታንክ ሞተርና ሰንሰለቱን አነጣጥረው ሲመቱት እግረኛውን በወኔ ከነበልባሉ ውስጥ ያስገቡት ነበር:: አየር ላየር ውጊያም ስጋ እንደሚናጠቁ ጭልፊቶች ነበር የሶማሌን ቀርፋፋ ሚግ እስ በሱ ያጋጩት የነበረው:: ከካራ ማራ ጋራ ጋር ሳይቀር አላትመውታል:: ብቻ እንደ አንድ እግረኛ ወታደር ያላንዳች እረፍት ጨበጣ ገብተው ተዋግተዋል::

"አየር ሀይላችን ለዝነኛነቱም ልጅ ተበርክቶለታል:: ከልጅ የበለጠ የሚዳይ ሽልማትም በዚች አለም ላይ ያለ አይመስለኝም:: ታዲያ ያ-ጊዜ አለፈና ሌላ ጊዜ ተተካና እነዚያ ስመጥር አብራሪዎች አለቁና፤ አንዳንዶቹም ተሰደዱና ምን ይቀራሉ በራሽያ የሰለጠኑ ወጣት አብራሪዎች:: ከችሎታ ማነስ ይሆን ወይንም ባመራሩ አለመደሰት የገበሬ መንደርን፣ ገበያ ለመገብየት የተሰበሰበ ህዝብን፣ ቤተክርስቲያን



ለመሳለም የወጣን ምእመና ያጋዩት ጀመር:: አንዳንድ ጊዜም የወገንን ጦር ያበራዩታል:: እነዚህስ ቆርቆሮው የደርግ፣ አብራሪዎቹ የኢህአዲግ ሳይሆኑ አይቀሩም" አሉና ትንሽ ተንፈስ ብለው:-

"ሌላው ጦራችን የባህር ሀይላችን ነበር:: እሱም ባህር ውጦት ቀረ" በማለት ዝግ ብለው በመቆጨት አይነት ራሳቸውን ነቀነቁ::

"ፖሊስም ደጀን ጦራችን ሲሆን ቅድመ አብዮት ጥሩ ዝና ነበረው:: በተለይም ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ በህዝቡ ዘንዳ ተወዳጅ ነበር:: የጠረፍ ፖሊሶችም ከጠላት ጋር አንገት ላንገት እየተናነቁ ጥለው አልፈዋል:: በቢሮ ስራም በኩል ቀልጣፋ ነበሩ:: ወንጀለኛን አሳዶ በመያዝ በኩልም አንቱ የተባሉበት ወቅት ነበር::

"ፖሊስ ድህረ አብዮት ግን ልክ እንደ ሌላው ሰራዊት ሁሉ እሱም ተሰቃይቷል:: ፈጥኖ ደራሽም እንደ ቀድሞው አየር ወለድ ፈርሶ በጦሩ ውስጥ እንዲጨፈለቅ ተደርጓል:: የቀረውም ቢሆን በተለያዩ ጊዜያት ወደ ጦሩ እየተወሰደ ሰጥሞ ቀርቷል::

"ፖሊስ በተለይም ከቅርብ አመታት ወዲህ ስሙ በጅጉ የጎደፈ ነበር:: ከስታዲየም በር ላይ ቆመው የመግቢያ ትኬት በትርፍ የሚሸጡ፣ በሲጋራ ተገዝተው የሰልፍ ቦታ የሚያሲዙ፣ ጨለማን ተገን በማድረግ በቆመጥ የሚነርቱ፤ በሶሻሊዝም ማህፀን ውስጥ ተፈለፈሉ:: በመጨረሻም ፖሊስ እንደ ውሻ ቡችላ ተቆጥሮ የራሱን ምስል በቆርቆሮ ተሰክቶለት ከደረቱ ላይ ለጥፎ እንዲሄድ ተደረገ" ሲሉ እኛ እንደ መሳቅ አልን:: እሳቸው ፈገግም አላሉ:: አንጀታቸው እሯል::

እፊትለፊታቸው እየተመለከቱ ትንሽ ከተከዙ በኋላ:-"የሲቪል ሚኒስትሮችና ኮሚሽነሮች፣ የመምሪያ ሀላፊዎች ሁሉ ለውድቀታችን ተጠያቂዎች ናቸው:: የሲቪል ባለስልጣኖችም መንግስቱ ሀይለማርያምን አይወዱትም ነበር:: የፓርቲ አባል የሆኑት ባላማው አምነውበት ሳይሆን ለማደግ፣ ቤት ለመስራት፣ አንዳንዶቹም ቀን ለመግፋት ነበር:: በዚህ የተነሳ ታማኝነታቸውን ለሱ እየገለፁ የግል ህይወታቸውን ያመቻቹ ጀመር:: ከመጠን በላይ የስልጣን መባለግ ባገሪቱ ውስጥ ተከሰተ:: ስግብግብነት ነገሰ:: ጦሩ በየቀኑ እየተመታ አዲስ አበባ እስከሚጠጋ ድረስ 'እረ እንዴት ነው? ጦሩ በምን ምክንያት ተሸነፈ?' ብሎ የሚጠይቅ አልነበረም:: የሚንጫጫው ያው ተራው ህዝብ ነው:: እሱ ደግሞ ሰሚ የለውም:: ካዲስ አበባ ውጭ ህይወት የለም:: ጦርነት፣ ርሃብ፣ ስደት፣ ሰቆቃ ነው:: አዲስ አበባ ውስጥ ደግሞ ሰርክ ግብዣ፣ ሰርክ ሰርግ ማሸር ይቀልጣል:: ቀኑ አልጠቅም እያለ ሲጨፈር ይነጋል:: የጥፋት ደመና ግን በላያችን ላይ ያንዣብብ ነበር:: ቀና ብሎ ላፍታ የሚያየው ጠፋ እንጅ::

"ባለስልጣን የተባለ ሁሉ ገንዘብ ለማካበት መሯሯጥ ብቻ ሆነ:: እና ደርግ ሲወድቅ ካዲሱ መንግስት ጋር ተስማምተው የሚኖሩበትን መንገድ መቀየስ:: በሚስት ስም፣ በልጆች ስም፣ በወዳጅ ስም ድርጅት መክፈት:: ለክፉ ቀን ንብረት ወደ ውጭ ማሸሽ:: ጀኔራሎቹም ከዚህ ውድድር ውስጥ የገቡት ወደው አይደለም:: ሁኔታው አስገድዷቸው ነው:: ፍትህ ጨርሶ ጠፋ:: በእኩልነት ለመኖር ቀርቶ የበታች ሆኖ መኖር ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደረሰ:: እና ኀዘዝ አገራችንን ተረባርበን መሰለኝ ያጠፋናት:: መንግስቱ ሀይለማርያምን ብቻ መኮነኑ አግባብ

አይመስለኝም:: ተሳስቸ ይሆን?" ሲሉ ተናግረው ሲጨርሱ በጥያቄ አስተያየት አዩን::

"አልተሳሳቱም ጌታዬ፤ ልክ ነዎት:: ለውድቀታችን መንግስቱ ሀይለማርያም ብቻ አይደለም ተጠያቂው:: ከሱ የበለጠ ተጠያቂዎቹ ባንዳ ምሁራንም ናቸው:: አገሪቱ ደክማ አስተምራቸው በሙያቸው አገሪቱን ማገልገል ሲገባቸው ሀሊና ቢሶች በሆዳቸው ክብራቸውን ሸጠው፤ ከነመንግስቱ ስር እያቶሰቶሱ ይችን አገር ቀበሯት! ሰው አልባ አደረጓት!" ስላቸው ቀልጠፍ ብለው:-

"ልክነህ፤ ሆዳም ሰው ከሆዱ ሌላ አገርም፣ ዘመድም የለውም:: ጎበዝ! ከደርግ የተጠጉ ሆዳም ምሁራን የሚያስቁም፣ የሚያሳዝኑም ናቸው:: 'ብልሁ፣ ቆራጡ...!' እያሉ ሲያንቆላጵሱት ኖረው ጉች አድርጓቸው ሲሄድ ቅሌታቸውን ታቅፈው ቀሩ:: ሆዳሞች" አሉ እጃቸውን በቁጣ አወራጭተው::

"እኔ ግን ጌታዬ የመከላከያ ሚኒስቴር መፍረስ ምስጢር ያለው ሆኖ ነው የሚታየኝ:: ካለፈውኮ መማር አለብን:: ደርግ እያታለለ አይደለም እንዴ ያወደመን:: እነዚህስ ያንድ ጎሳ ጦር ገንብተው አንባገነን ቢሆኑስ?" አለ እዱኛ::

"ይሆናሉና! ምን ጥርጥር አለው:: ታዲያኮ እዱኛ ይህን ሁሉ መገንዘብ የነበረብን በፊት ነበር:: ዛሬ መሳሪያቻችንን አስረክበን፣ እጃችንን ሰጥተን 'እንዲህ ሊያደርጉ ነው' ብንል አይሆንም:: ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የሚሰሩትን ማየት ነው:: 'ለኩልነት፣ ለዲሞክራሲ' ነው የቆምነው አይደል የሚሉት? በተግባር ከተረጎሙት ከጎናቸው እንሰለፋለን:: ሸፍጥ የሚሰሩ ከሆነ ግን እነሱ እንደሆኑት መሆን ነው:: ህዝቡም ቢሆን የሚሆነውንና የማይሆነውን ደህና አድርጎ ያውቃል:: ሌላው ቢቀር ጥይት ሳይተኩስ፣ ሸፍቶ ጫካ ሳይገባ በዝምታ ብቻ አድቅቆ ይጥላቸዋል:: ደርግን ያነኰተው ህዝቡ እንጂ እነሱ እንደሚሉት ብቻቸውን አይደለም" አሉ::

ለትንሽ ጊዜ ዝምታ ዋጠን:: ውስጥ ውስጡን ግን ነገር እንፌጭ ነበር:: በተለይ በድሉ ጫኔ በሀሳብ ሰጥሟል:: ይኸው ነው:: ነገር ከሆዱ ሲገባ መነጋገር አይወድም:: እስካሁንም ትንፍሽ አላለም::

ኮለኔልና እዱኛ ቀድመው ሄዱ:: ቀጥሎ በድሉ ሄደ:: እኔ ብቻየን እንደ ተቀመጥኩ ቀረሁ:: ብዙ ካሰብኩ በኋላ ነው ይህን ግጥም የቋጠርኩት::

አገር ተቃጠለች አንድ ነገር ሳይቀር እርጥቡም፣
ደረቁም ባንድ ላይ አረረ፣
ብርጭቆው ብርሌው የንጀራ ምጣድም ሁሉም ተሰበረ፣
እቃ እቃው ብቻ ነው ቁጭ ብሎ የቀረ::
ሲቃዩ እየበዛ ግፉ ገነፈለ፣
እዛዛው ሲተከል ቡቃያው ነቀለ::
እምላክሽን ሳትበድይ አንገትሽን በደፋሽ፣
እረ ምን አረገሽነው እዞ ያስጨረሰሽ?
ኢትዮጵያ አገሬ የጥንት ጠረንሽ የዝባድ ነበረ፣
በዘመነ ደርግስ ጠረንሽ ለውጦ እጣኑ እያረረ፣



በደርግ ጊዜማ እረምኑ ተርፎ፣
ሁሉም በያለበት እንደ ወይራ ቅጠል ቀረ እንጅ አረግፎ!

ወደፊትም ገና እንረግፋለን:: የሚታየኝ ተስፋ ጨርሶ የለም:: ጨለማ ህይወት ብቻ...

# 14

ትናንት ሶሻሊዝም ዛሬ ጴንጠ ቆስጤ እያልኩኝ አላዝንም፣
ምንም ይሁን ምንም ሀቅ ይዞ ከመጓዝ የተሻለ የለም::

የሶስት ቀናቱ ሴሚናር ደብዛው ጠፍቷል:: አሁን አፍላ እየተወራ ያለው ከሰኔ 24 ኮንፈረንስ በኋላ የሽግግር መንግስቱ ሲመሰረት የሶስት ቀናቱን ሴሚናር ተካፍለን የግንቦትና የሰኔ ወር ደመወዛችንን ተቀብለን በደስታ እየጨፈርን አዲስ አበባ መግባት ነው::

ሌላው የሰሞኑ አዲስ ነገር በራሪ ወረቀት በግቢያችን መረጨቱ ነው:: ሁሉም ተመስጦ ያነበዋል:: እርግጠው የመስቀል ምልክት ነው:: «ፊታችሁን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልሱ፤ ይቅር ባይ ነውና ይቅር ያላችኋል» ይላል:: ጠይቄ እንደተረዳሁት ከሆነ ጴንጠ ቆስጤ የተባለ የሀይማኖት ድርጅት ነው:: መመሪያው መፅሀፍ ቅዱስ ነው::በርግጥም አብዛኛው መኮንን ጥራዙ ያበጠ መፅሀፍ ቅዱስ ይዟል:: ምን አይነት ሀይለኛ ድርጅት ነው፣ ይኸውና ባንድ ሳምንት ውስጥ ይበልጡን መኮንን መለመለው:: ወደፊት ሌሎች ድርጅቶች ብቅ ቢሉ ዋጋ የላቸውም:: ካባላቱ ውስጥ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት የደርግ ካድሬዎች የነበሩ:: ቅልጥፍናቸውን አደነኩኝ::

አንድ የንቦች ማናቢያ የነበረ አዳራሽ አለ:: ንቦቹን ዘራፊዎች ስለዘረፉዋቸው አዳራሹ ዛሬ በንቦቹ ምትክ መዘመሪያ ሆኗል::

ዛሬ ጧት መዝሙሩ ካደራሹ ጣራ በላይ ነግሶ ሲሰማኝ ጊዜ ሁኔታቸውን ለማየት ወደዚያው አመራሁ:: ወደ ውስጥ ስገባ መኮንኑ ሁሉ አይኖቹን እንደ ውሻ ቡችላ ገጥሞ «ኢየሱስ ሆይ! ይቅር በለን!» እያለ እንባ ቀረሽ በጭንቀት ያምጣል:: አውራጁ ደግሞ ድምፀ መረዋ ነው:: አእምሮን ይሰልባል:: አንገቴን እስግጌ ሳይ ከላይ ዳር በኩል አየሁት:: በጣም ገረመኝ:: አውቀዋለሁኝ:: የሶማሌ ጦርነት ጊዜ አስር አለቃ ነበር:: እኔ የዚያን ጊዜ ምክትል መቶ አለቃ ነበርኩ:: ዛሬ እሱ ቀድሞኝ ሻምበል ሆኗል:: እረ ኢህአዲግ ደርሶበት እንጅ በሚቀጥለው ሀምሌ ሻለቃ ይሆን ነበር:: ትግራይ ዘምቶ አንድ አይኑን አጥቷል:: ታዲያ ተጀምሮ እስኪጨረስ የፖለቲካ ሰራተኛ ነበር:: ዛሬ ከምነየው ቀሰሰ?

ጓድ፣ የብርጌድ የፖለቲካ ሀላፊ ሲዘምር ቆይቶ ያችኑ የቀረች አይኑን ገለጥ ሲያደርጋት አየኝ:: እፍር አለ:: እኔ ደግሞ ፈገግ ብዬ ኩራ አልኩኝ:: ሆን ብዬ ነው:: እሱና እኔ የምንተዋወቅበት ጉዳይ ነበር::

ታሪክ መቼም ጉደኛ ነው:: ለታደለ በቁሙ ያሳየዋል:: እኔም እንዳቅሜ አየሁኝ:: የዛሬው የሃይማኖት መምህር፣ የትናንቱ ካድሬ

ድሬዳዋ በነበርንበት ወቅት መፅሀፍ ቅዱስ «አድሃሪ ነው» ይባልና ከያለበት ተሰብስቦ እንዲቃጠል ይወሰንበታል። እኔ ሲፈርድብኝ:-

"ጓድ ምናለ ባይቃጠል፤ ተቃጥሎ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?" ብዬ መጠየቅ። እሱ ተቆጥቶ "ጓድ ይኸ ለዘብተኛነት ነው" ብሎ ወረደብኝ።

"እኔ እስከሚገባኝ ድረስ መፅሀፍ ቅዱስ የሃይማኖት ታሪክ ነው። መፅሀፍ ማቃጠል ደግሞ ሀቀኛ አያሰኝም" ብዬ መመለስ። "አይቃጠል ማለትም አድሃሪነትና ጎታችነት ነው!" አለኝ። ያን ጊዜ መኮንን የተባለ ሁሉ አድሃሪ ነበር የሚባለው። በተለይ ኮለኔሎች መከረኞች ነበሩ።

"ድንቁርና ነው" አልኩና በማኩረፍ ፈንጠር ብዬ በመቆም ድርጊቱን አመለከት ጀመር። ያ ሁሉ መፅሀፍ ቅዱስ ቤንዚን ተርከፍክፎበት ተቃጠለ። እኔም በማግስቱ ክፍለ ጦር ፖለቲካ መምሪያ ትፈለጋለህ ተባልኩና በስልክ ተጠራሁ። ስሄድ የቃል ክስ ተመስርቶብኝ አገኘሁ። 'ካድሬዎችን ደንቆሮዎች ናችሁ' ብለሃል የሚል ነበር። መልስ እስከምሰጥ እንኳን ጊዜ አልተሰጠኝም። ለጥብስ አደረሱኝ። በወታደር ፖሊስ ተነድቼ እስር ቤት ታጎርኩኝ። ከዚህ በኋላ ያለምንም ጥያቄ አራት አመት ጠጥቼ ወጣሁ። ያን ያደረገው ጓድ ነው እንግዲህ የዛሬው የሃይማኖት መሪ የሆነው። እኔም በማእረጌ ከማንም በታች ሁኘ የቀረሁት በዚሁ ሰበብ ነበር። ዛሬ ግን ከኮለኔሎቹም ጋር እኩል ነኝ።

ስርአተ ፀሎቱ አብቅቶ ከበሩ ላይ ጠበኩትና ሰላምታ ሰጠሁት፤ ሆን ብዬ ነበር።

"ታዲያስ ጌታዬ" ሲል ተሽቆጥቁጦ እጄን ጨበጠኝ።

"ታዲያስ ጓድ! እንዴት ይዞሃል?" ስለው:-

"ጓድ አትበለኝ" አለኝ ትንሽ ቅር ተሰኝቶ።

"እንዴት?" አልኩት።

"አልፈልገውም። የውሸት መጠሪያ ነው። እነመንግስቱ ሀይለማርያም እኛን ለማታለል የተጠቀሙበት ዘዴ ነው" አለኝ።

"ታዲያ በምትኩ ምን ብዬ ልጥራህ?"

"ማእረግ አለኝ! በማእረጌ ጥራኝ።"

"ማእረግህም የነመንግስቱ ነው" አልኩት ትንሽ ፈገግ ብዬ።

"ከፈለክ በስሜም ጥራኝ። አልቀየምህም። ሁሉም ነገር አክትሟል። የእግዚአብሄር ሀይል ብቻ ነው ማክተሚያ የሌለው" አለኝ ኮስተር ብሎ።

"አንድ ነገር ልጠይቅህ" ስለው ቀልጠፍ ብሎ:-

"ምን ልትጠይቀኝ እንደ ፈለክ አውቄዋለሁ። 'የዚያን ጊዜ ድሬደዋ መፅሀፍ ቅዱስ አቃጥለህ አልነበረም?' ልትለኝ ነው። ማቃጠሌን አልክድህም። አቃጥያለሁ። ያኔየ ጨቅላ ነበርኩ። ዛሬ ግን አውቃለሁ። ብዙ ነገሮችን ተምሬአለሁ። አምላኬንም ይቅርበለኝ ብየዋለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን በስተቀር የሚያዋጣ ነገር የለም። አንተንም ቢሆን ባለፈው የተገናኘን እለት ይቅርታ ጠይቄሃለሁ። 'ምንም አይደል፤ አልፏዋል' ብለኸኛል። አንተን መበደሌንም ላምላኬ



ነግሬዋለሁ። አሁንም ቢሆን በድጋሚ ይቅር በለኝ" ብሎ ወደ ጉልበቱ ጎንበስ አለ።

"በፍፁም! እኔ ቂም አልያዝኩብህም። ብይዝብህማ ኖሮ አላናግርህም ነበር" ብዬ በጄ ቀና ሳደርገው:-

"አመሰግናለሁ። እግዚአብሄር ይስጥህ" አለኝ አነጋገሩን ረገጥ አድርጎ።

"አሜን" ብዬው ፈጥኜ ተለየሁት።ትህትናውንስ ምንየ ተላብሶታል።

ትዝ ይለኛል፤ ከየኔነሽ አሰፋ ጋርም ፍቅራችንን ሳንጨርስ የተለያየነው በመታሰሬ ምክንያት ነበር። ምን አይነት እድል ነው። ባለፈውም እንደ ጀመርነው ተቋረጥን። ዛሬስ ናፍቃኛለች። ሰኔ 24 ቀን ከመድረሱ በፊት አዲስ አበባ ደርሽ መመለስ አለብኝ። ትመጣለች እያልኩ በጉጉት ብጠብቃት አልመጣችም፤ ማን ያውቃል፣ አንድ ችግርስ ገጥሟት እንደሆን?

## ምእራፍ ስድስት

«ስማችን ወያኔ ስድባችን ቅማላም፣
የደርግን ወታደር ነዳነው እንደላም!»

«ኧረ እናንተ ሆዬ ምንም ቀን አልወጣ፣
አንድ አህያ ቢሄድ መንጋ ፍዬል መጣ!»
የኔነሽን ፍለጋ አዲስ አበባ ሄጄ የሰማሁት ግጥም ነበር።

## 15

ከጥዶቹ ቁጥቋጦዎች ስር ነው የተቀመጥኩት። ከፊት ለፊቴ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ትውለበለባለች። እንጋጥጨ አየኋት። ነፋስ ወዲያና ወዲህ ያላጋታል። ከግንዶት ሀያ ወዲህ የሚሰቅላት፣ የሚያወርዳት የለም። ሌትም ቀንም ትውለበለባለች። ባለቤት የሰትም። ኧረ ለመሆኑ የማን ባንዲራ ነች? እሷም ያማራ ባንዲራ ትሆን እንዴ?

ካዲስ አበባ የተመለስኩት ትናንት ነው። አዲስ አበባ ቀዝቀዝ ብላ ጭርታ ውጧት ነው ያገኘኋት። ለምን እንደ ሆነ እንጃ ሰዉ ጨርሶ ተስፋው ተሟጧል። በዘፈቀደ ነው የሚንጠራወዘው። ሲመሽ ሲነጋ ማየት ብቻ... ተስፋ ማጣት መጥፎ ነው። ያዲስ አበባ ህዝብ ደግሞ ሁሉ ነገሩ ተስፋ ማጣት አይወድም። ኧረ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተስፋ ነው የኖረው። ደርግ «አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ ኢማለዲህ፣ ኢሰፓአኮ፣ ኢሰፓ» እያለ በተስፋ አቆይቶቅሎበቤ፣ ትንሽ ተስፋው የተሟጠጠበት «ኢህድሪን»

ከመሰረተ በኋላ ነበር:: ከዚህ በኋላ የሚለው የለውማ:: እነዚህስ ባንድ ጊዜ ተስፋ አሳጡት:: ህዝቡ ኢህአዲጎቹን ፊዕሞ አልተጠጋቸውም:: የጎሪጥ ያያቸዋል፤ ይሸሻቸዋል፤ መጥፎ አዝማሚያ ነው:: ፈጣሪየ «የመንግስቱ ሀይለማርያም አስተዳደር ይሻላል» ከሚባልበት ዘመን እንዳያደርሰን ፈራሁኝ::

ካውቶቡስ እንደ ወረድኩ ነበር በህዝብ ስልክ ለየኔነሽ የደወልኩላት:: ስልኩ መጥራት ሲጀምር ልቤ አመር አመር ይልብኝ ጀመር::

"ሀሎ!" የሚል ድምፅ ሲመጣልኝ፤

"ሀሎ! የኔነሽን ነበር፤ ላገኛት እችላለሁ?... የት ሄደች? ሆለታ? መቼ? ትናንት?... እሺ" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ስሜቴ ሁሉ ኩምሽሽ አለ:: ልክ ከፍም ላይ ውሃ ሲፈስ ትሽሽ... እንደሚለው::

ለመሆኑ ማንን ለመጠየቅ ነው ሆለታ የሄደችው? እኔን ቢሆን ኖሮ ታገኘኝ ነበር:: ደግሞስ ትናንት ከሆነ የሄደችው ዛሬ የት ደረሰች? ኤዲያ ፀባይዋን እያወኩኝ፤ ኧረ እሱስ ያባከናት መሆኑን አለ:: ወይኔ ጎርፉ! በቅናት እርር ኩምትር አልኩኝ:: በየኔነሽ ለምን እንደ ምቀናባት አይገባኝም:: ከበርካታ ሴቶች ጋር ተገናኝቻለሁ:: ካንዳንዶቹም ጋር ዋል አደር ብያለሁ:: ግን አላስታውሳቸውም:: ስለያቸው መለየት ነው:: የኔነሽ ግን አትረሳኝም:: ጠብ እርግፍ አድርጌ ብተዋትም ሳገኛት አዲስ ትሆንብኛለች:: የምተዋትምኮ ስለምቀናባት ነው::

የኔነሽኮ መኝታ ላይ እንደ ሌሎቹ ሴቶች አይደለችም:: የተለየች ናት:: አብዳ ነው የምታሳብደው:: በዚህ ላይ ልስላሴዋ፣ ጠረኗ፣ የከንፈሮቿ መጣፈጥ ማር ከረሜላ ናቸው:: ለፍቅር ንፍግት አታውቅም:: ታዲያ ምን ይሆናል! እንደ አደይ አበባ ሁሉ ይቀስማታል:: እግዚአብሄር ይይላት! ያንን ገላ ለሁሉ ታስዳስሰዋለች::

ካውቶቢስ መናኸሪያ ውጥቼ ቁልቁል ተዳፋሁ:: ለጊዜው ወደየት አቅጣጫ ለመሄድ እንዳሰብኩ አላውቅም:: በጣም በሽቆኛል:: አይፈረድብኝም፤ ከሆለታ በጉምጃታ መጥቼ ሳጣት ምን ላድርግ!

መሀል መርካቶ ካንድ ሆቴል ዘው ብዬ ገባሁና ጥግ ይዤ ተቀመጥኩ:: ሰዉ ድራፍት ይጠጣል:: ሰአቱ ወደ አስራ አንድ ሰአት ይጠጋል:: አንዲት ጠየም ያለች ቆንጆ መጥታ:-

"ምን ልታዘዝዎት?" አለችኝ:: ፈገግታዋ ለዛ ነበረው:: ጨምድዶ ያዘኝ::

"ድራፍት" አልኳትና መለስ ብላ ስትሄድ ባይኖቼ ተከተልኳት:: ትክለ መልካም ናት፤ ሸንቀጥ ያለች:: ከሁሉም ጥርሶቿ ይምጡብኝ:: የተቆለፈ ልብን ይከፍታሉ:: ድራፍቱን ይዛልኝ መጣችና ከፊቴ ላይ አስቀምጣልኝ ፈቀቅ ብላ ጥግ ይዛ ቆመች:: ስርቅ አድርጌ አየኋት:: ፀጉሯም ዘንፋላ ነው::

መሸተኛው ጠጥቶ ለመሄድ ተቻኩሏል:: እፍግፍግ ብሎ እየተጣደፈ ይጠጣል:: ብዙ ሁካታ አይሰማም:: ፈገግታ የሚባል ነገርም የለም::

ትዕግስቱ ያለቀው ሙሽሽ ሲልልኝ ብርጭቆውን ብድግ አድርጌ [illegible] እንደ መጎምዘዝ አለኝ:: ይልቅየ ቅዝቃዜው ያተኮሰ ሰውነቴን አበረደልኝ:: [illegible] አሁንም ጠጥቶ ለመሄድ ይሻማል:: እኔም አጋባሁና



እንድትደግመኝ ጠቀስኳት:: ለምን እንደ ሆነ እንጃ ወደኔ ስትመጣ ፈገግታዋን ታደምቀዋለች:: ብርጭቆውን ስታነሳ:-

"ይቅርታ፤ ጠምቶኝ ነው:: አጣደፍኩሽ መሰል" አልኳት:: ገና አሁን ነበር ያናገርኳት::

"አይ! ምንም አይደል፤ ስራየ አይደል" አለችኝ፤ አንገቷን መታ ስታደርገው ሀብሏን አየሁት፤ ከጠይም አንገቷ ላይ እርፎ ውበት ሰጥቷታል:: ድራፍቱን ይዛልኝ ተመለሰች:: አሁንም አስተውየ አየኋት:: አንጀት የላትም:: ሽልግ ያለ ነው፤ ከፊቴ አስቀምጣልኝ መለስ ስትል:-

"የት ትሄጂ" አልኳት ፈገግታየን አድምቄ::

"የትም አልሄድ" አለችና መለስ ብላ በትከሻየ በኩል ጠጋ ብላ ቆመች:: መቀመጫ ወንበር አልነበረም:: ደግሞ በጃ ትከሻየን ተመረኮዘችው:: ደስ አለኝ:: የየኔነሽን ራስ ምታት የምትፈውስ ክኒን አገኘሁ::

"ሰዉ የት ለመድረስ ነው እየተጣደፈ የሚጠጣው?" ስል ጨዋታ ለመጀመር ያህል ጠየኳት::

"ሰአት እላፊ ሳይደርስበት በጊዜ ጠጥቶ ወደ ቤቱ ለመሄድ ነው::"

"ሰአት እላፊ እስከ ስንት ነው?" አልኳት ልክ እንደማላውቅ ሰው ሁኜ::

"እስከ ምሽቱ አንድ ሰአት ድረስ:: እንግዳ ነህ እንዴ?"

"አዎን! እንግዳ ነኝ:: ከክፍለ ሀገር እንደ መጣሁ ሆለታ ገባሁ:: አጮኛ ነበረችኝ እሷን ልጠይቅ ብመጣ የለችም አሉኝ" ስላት ከንፈሯን መጣ:-

"የት ሄደች አሉህ?"

"ትናንት ሆለታ እንሄደች አልተመለሰችም አሉኝ::"

"እንተኑ ለመጠየቅ ሄዳ ይሆናላ::"

"ሊሆን ይችላል" አልኳትና ትንሽ ዝም ብዬ ቆይቼ "ስምሽ ማን ይባላል?" አልኳት::

"ዕጌ" አለችኝና "ያንተስ?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ሙቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው እባላለሁ:: ምንድን ነው የምትጠጭው? ልጋብዝሽ::"

"ድራፍት" ብላኝ ልታመጣ ስትል:-

"እንዳትመላለሽ ለኔም አምጭልኝ" አልኳትና ብርጭቆየን አጋብቼ ሰጠኋት::

ዕጌ ድራፍቱን ይዛ መጣችና የኔን ከፊቴ ላይ አስቀምጣልኝ የሷን አጋመሰችለት:: ደንገጥ አልኩ:: ጠጭ ከሆነች ኪሴ አይችላትም:: ጥርሶቼን ነክሸ ከያዝኳት አምሳ ብር አርባ ቀርታኛለች::

ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና ከንፈሯን አባብሳ ትከሻየን ደገፍ ብላ በመቆም:-

"ተጫወት" አለችኝ:: የኪሴ መቅለል ቅፅበታዊ ስጋት ወሮኝ ነበር::

"እሺ" አልኳትና ድራፍት ተጎነጨሁ::

"ለመሆኑ መኝታ አገኘ ይሆን?" አልኳት:: አጠያየቁ የቢሆን ይሁን ነበር::

"ልጠይቅልህ እንዴ?"

"አዎን" ስላት ፈጠን ብላ በውስጥ በር ገባች:: ሰአቴን ሳይ ላስራ ሁለት አምስት ደቂቃ ጉዳይ ይላል:: መሸተኛው ቀስ እያለ መሹለክ ይዟል::

ፅጌ ወዲያው ተመለሰችና "እድለኛ ነህ፤ ለትንሽ የመጨረሻውን አልጋ አገኘህ:: ስምንት ብር ስጠኝ" አለችኝ እየተጣደፈች:: አውጥቼ ሰጠኋት:: ሰላሳ ሁለት ብር ቀረኝ:: ጉዶ ፈላ:: እራት አለ፤ ድራፍቱንም ገና አልደጋገምነም:: እሷስ ስንት ትጠይቀኝ ይሆን? ወገቤ ክፍል አለ::

ያልጋውን ሂሳብ ከፍላ መጣች:: ከኔ እልፍ ብለው ይጠጡ የነበሩ ሁለት ሰዎች ሂሳብ ከፍለዋት ሄዱ:: ብርጭቆዎቹን አነሳስታ፣ ጠረጴዛውን ወላውላ አንዱን ወንበር ይዛ በመምጣት ከፊት ለፊቴ ተቀመጠች:: መስተዋት ሆነችልኝ:: በማደሬ ደስ ብሏታል:: ያይኖቿ ቅንድቦች ሳይቀሩ ስቀዋል::

"ተጫወት" አለችኝ ተመቻችታ ከተቀመጠች በኋላ::

"እሽ" አልኳት ፈገግ ብዬ:: ከንግዲህ መሞሸራችን አይደል:: የሂሳቡ ነገር ወገቤን አርቆኛል::

መከራከሩን ደግሞ አላውቅበት:: ያለኝ ምርጫ ሀቁን መናገር ነው:: ትጠጣ፤ እራት እጋብዛታለሁ:: ያለኝ ገንዘብ ለዚህ ይበቃኛል:: ከዚህ በኋላ እሽ ካለች አብረን እናድራለን:: እንቢ ካለችም ተጠቅልየ መተኛት ነው::

እሷ ከድራፍቱ ከደገመች በኋላ እራታችንን ለመብላት ወደ ምግብ አዳራሽ ገባን:: ሰአት እላፊ በመቃረቡ ነው መሰል ጭር ብሏል:: ከመቀመጣችን ነጭ ካኪ የለበሰ ቦይ መጥቶ:-

"ምን ይምጣላችሁ?" አለን::

"ምን ምን አላችሁ?" ስለው ማት ነገር አነበነበልኝ:: እኔ ይህን ሁሉ የምግብ አይነት አላውቅም:: ቶሎ ብዬ:-

"ጥብስ" አልኩት እሱን ሲጠራልኝ:: ፅጌም እሱን አዘዘች::

"ሂሳብ በቅድሚያ" ሲለኝ:-

"ስንት ነው?" አልኩት እጄን ወደ ኪሴ እያስገባሁ::

"አስራ ሁለት ብር" አለኝ:: አውጥቼ ሰጠሁት:: ሀያ ብር ቀረኝ:: ድራፍቱ ገና አልተከፈለም እንጅ ለፅጌ ይበቃት ነበር::

ጥብሱ መጣልን:: ትኩስ ነው:: ደግሞ ስጋ ነው:: እሱስ ፅጌም ስጋ ነበረች:: ኪሴ ነው ደርቆ ያደረቀኝ::

"ብይ እንጅ" አልኳት እንደ መቅለስለስ ስትል ጊዜ:: የየኔነሽን እለህ በፅጌ አበረድኩት::

በልተን ካበቃን በኋላ ተጣጥበን ወደ መጠጥ ቤቱ ተመልሰን ድራፍታችንን እንጠጣ ጀመር:: ሳይታወቀን ነበር አንድ ሰአት የደረሰው:: ሴቶች እቃ መሸካከፍ፣ ሂሳብ ማስረከብ ይዘዋል:: እኔም ለፅጌ እንዳለ ሀያውን ብር አስረከብኳት:: ዘጠኝ ብር ከሀያ ሳንቲም መለሰችልኝ:: ጓደኞቿ ወደ ቤታቸው ውልቅ ውልቅ አሉ:: አሳዘኑኝ:: ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ይመስሉ ነበር:: ወንዱ ወኔው ተሰልቧል...



ፅጌ ሂሳቧን አስረክባ መጣችና ካጠገቤ ተቀመጠች:: አንድ ነገር ልትጠይቀኝ ፈልጋ ትቅለሰለስ ጀመር:: ፈገግታዋ ደግሞ የትህትና አይነት ነበር:: የሴትነት ክብሯ ደግሞ አፍኖ ያዛት:: ቢጨንቃት:-

"ቤቴኮ እሩቅ ነው" አለችኝ::

"የት ነው?" አልኳት::

"ወደ መሳለሚያ ነው::"

"ታዲያ ምን አስጨነቀሽ::"

"ማለቴ ... " ብላ አንገቷን ደፋ አደረገች::

"ማለትሽ?" አልኳት ፈገግ ብዬ::

"አብረን ነወይ የምናድረው ብዬ ነው" አለችኝ::

"ታዲያስ:: አንቺን ብዬ እንጂኮ የማድርበት አላጣሁም:: ለምን እንደሆን እንጃ ሳይሽ ደስ አልሽኝ" ስላት ፈገግታዋ ጨመረ:: ትንሽ አሰብ አደረኩና "ፅጌ" አልኩና ጠራኋት፤ አጠራሬ ራሱ ለዛ ነበረው::

"ወይየ" አለችኝ እሷም በፍቅር አይን እያየችኝ::

"እንዴት መሰለሽ፤ በምን ሁኔታ እንደ መጣሁ ነግሬሻለሁ:: ዛሬ የገንዘብ ችግር አለብኝ:: በሌላ ጊዜ ግን እጥፍ አድርጌ እክስሻለሁ" ስላት ቅሬታ በፊቷ ላይ ሽው ብሎ ሲያልፍ አየሁት::

"ምንም አይደል" አለችኝ:: አመላለሷም በይልኙታ የታፈነ ነበር:: እርግጠኛ ነኝ:: የጋበዝኳት ግብዣና አቀራረቤ ተለሳልሼ እንጅ ፅጌ በዋዛ የምትቀመስ አይደለችም::

ከዚህ በኋላ ወደ መኝታ ክፍላችን አመራን:: ፎቅ ነው:: ደረጃውን ስንወጣ ትንፋሻችን ይፈጥን ነበር:: ክፍላችን ውስጥ እንደ ገባን እኔ ወዳልጋው ሳመራ፣ እሷ በሩን ከረቸመችው:: ካልጋው ጫፍ እግሮቼን አንጠልጥየ ጠበኳት:: ወደኔ ስትመጣ አይኖቿ ማረፊያ አጥተው ተቅበዘበዙ:: ጥርሶቿ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተገልጠዋል:: ከቅፌ ላይ ወደቀች:: ምንኛ የዋህ ኖሬአለሁ:: የቡና ቤት ሴቶች ገንዘብ እንጅ ፍቅር የሚያውቁ አይመስሉኝም ነበር:: ከንፈሮቿን ሳም አደረኳቸው:: ወለላ ማር ናቸው:: ልብሳችንን ለማውለቅ ሽሚያ ገጠምን::

መብራቱን እረስተነው አላጠፋነውም ነበር:: ብዙም ሳንቆይ ሁለተኛውን ዙር ተያያዝነው:: ለካም ነገር ያለው ሁለተኛው ላይ ነው:: የሰማይ የምድሩን፣ የኢሰፓውን፣ የኢህአዲጉን እንቀባጥር ጀመር::

ሟት ሰአቴን ሳይ አንድ ሰአት ይላል:: ፅጌ ውድቅ ብላ ነበር:: ቀሰቀስኳት:: አይኖቿን አሻሸችና "ነጋ እንዴ?" አለችኝ::

"ኧረ እረፍዷል" አልኳት:: አይኖቿ እንደ መርገብገብ አሉ:: ደህንየ ከንፈሮቿን ሳምኳቸው:: ወደ ሰውነቴ ጥብቅ አለችና መልሳ ሳመችኝ:: አድረንበት እንደገና ተናነቅነው:: መብራቱም ሲበራ እንዳደረ ነው:: ማህበራዊ ኑሮው ብቻ ነው የጨለመው...

ተነስቼ ልብሴን ስለባብስ እሷም መልበስ ያዘች:: ፀጉሯ ድራሽ አባቱ ጠፍቷል:: ነፋስ እንደ አመሰቃቀለው የጤፍ ነዶ:: በመልክ በመልኩ ካስተካከለችው በኋላ ቦርሳዋን እንግታ ተከተለችኝ:: መብራቱን ያጠፋነው ክፍሉን ስንለቅ ነው::

ከታች ወርደን ፊታችንን ከታጠብን በኋላ ቁርሳችንን ለመብላት ከሆቴል ወጥተን ወደ አንድ ቁርስ ቤት አመራን:: ግሩም የሆነ እንቁላል ጥብስ ነበር የበላነው::

"እንግዲህ ፅጌ የዛሬን መዋሌ አይቀርም" ስላት:-

"እጮኛህን ፍለጋ ነው?" አለችኝ ፈገግ ብላ:: በፈገግታዋ ውስጥ ግን የቅናት ምልክት እየሁባት::

"እሷን ተያት፤ ያልነገርኩሽ ነገር አለ" ስላት ደስ አላት:: በመካከላችን ጠብ እንዳለን በመገመት::

"ከዋልክ ብቅበላ ታዲያ::"

"እመጣለሁ::"

"እንዳትቀር እጠብቅሃለሁ::"

"አልቀርም::"

ከፅጌ እንደተለየሁ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ቤቱ ነበር:: እማማ ልኬን ከበሩ ላይ ቁመው አገኘኋቸው::

"ጎርፉ!" አሉና በደስታ ጮሁ:: "ልጄ እንደ ዋዛ ወጥተህ በዚያው ቀረህ! እስቲ ግባ" ብለው ድብርክ ድብርክ እያሉ ቀድመውኝ ገቡ::

"ተለቀቃችሁ?" አሉኝ ከተቀመጥኩ በኋላ::

"አልተለቀቅንም:: መቆየታችን የማይቀር ነው:: እማማ ልኬ እስከዚያው መበርታት ነው::"

"እኔማ ምን እሆን ብለኸኝ ልጄ፤ አንተ ተጎዳህ እንጂ:: ይሰፓ ያልሆነውን አይተናኮሉም አሉ:: 'አንተ ዛዲያ ይሰፓ አይደለህ:: ለምን አትነግራቸውም? ወዲህ ደሞ ተማሪ ነህ! ከጣጣው የለህበት:: ይህን ሁሉ አብራርተህ ንገራቸው::... የደርግ ጊዜም ታስሬ ነበር በላቸው::"

"እስቲ እሞክራለሁ" አልኳቸው:: የረሳሁትን ይልቅ ቀሰቀሱብኝ:: ይሆናል መስለኝ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ጀምሬ ነበር:: ፈተና ሲቀረን ነው የተቋረጥነው:: ምን አይነት እድል ነው? ከማድ ላይ መነሳት...

እማማ ልኬ እምበላው ለማዘጋጀት ተፍተፍ ሲሉ እኔ ወደ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ሳጥኔን ከፍቼ ስፈትሽ ለችግር ቀን ብዬ ያስቀመጥኩት ሁለት መቶ አምሳ ብር አገኘሁኝ:: ልክ ወድቆ ያገኘሁት ያህል ነበር የተደሰትኩት:: አምሳ ብሩን ለማማ ልኬ ሰጠኋቸው::

ምሳየን በልቼ ወደ ውጭ ሳልወጣ ከቤት ዋልኩኝ:: እማማ ልኬን ተሰናብቻቸው የወጣሁት ልክ አስራ አንድ ሰአት ሲሆን ነበር:: ወደ ፅጌ ከመሄዴ በፊት ለየኔነሽ ስልክ ደወልኩላት::

"ሀሎ!" የሚል የሴት ልጅ ድምፅ ሰማሁ::

"ሀሎ! የኔነሽን ነበር... አልተመለሰችም?... መቶ አለቃ ጎርፉ ደውሎ ነበር በይልኝ፤ ሆለታ ነው ያለሁት:: ጎሽ እንዳትረሽ" ብዬ ስልኩን ዘጋሁት:: ፅጌን ተለዋጭ በማግኘቴ አልተበሳጨሁም:: አደዋወሌም የቢሆን ይሁን ነበር:: ወደ ፅጌ ገሰገስኩ::

ከምትሰራበት ሆቴል ስገባ ሰዉ ይህን ድራፍት አፍላ ተያይዞታል:: መቀመጫ ፍለጋ ባይኖቼ ዘወርወር ብዬ ሳይ ፅጌን ከወዲያ በኩል ቁጭ ብላ አየኋት:: ፈገግ ብላ ጠቀሰችኝ:: ካጠገቧ ስደርስ ተነሳችና እጄን ጨበጠችኝ::



"ታዲያስ" ብያት ተቀመጥኩ:: ሁለት ሰዎች ካጠገቧ ተቀምጠው ድራፍት ይጠጡ ነበር:: እኔ ሶስተኛ ሁኘ ጠረጴዛ ተጋራሁኝ::

"ምን ይምጣልህ?" አለችኝ ትከሻየን በጇ ደገፍ ብላ:: የሚወዱትን ወይንም የፈቀዱትን ወንድ ሳይሆን አይቀርም እጃቸውን ጣል የሚያደርጉበት::

"ድራፍት" አልኳት:: የጠረጴዛ ባልደረቦቼ አረጋ ያለ ጨዋታ ይዘው ነበር:: ስለጊዜው ሁኔታ ነው:-

"... ምን እንዳያመጡ ብለሃቸው ነው? 'ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ፤ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል' የሚባል አባባል አለ:: ለራሳቸው ቢሉ የህዝቡን ትንፋሽ ያዳምጡ:: አለዚያ ግን የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል:: የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ ከንግዲህ ወዲያ አይታለልም" አለ ጥርሰ በላዛው ሰውየ::

"እንደ ደርግ መላ የሚፈጥሩ ከሆንማ እዳልከው የደርግ እጣ ይጠብቃቸዋል" አለ ራሰ በራው::

ፅጌ ድራፍቱን አምጥታ ከፊቴ አስቀመጠችልኝና ወደ ጆሮየ ጠጋ ብላ "እጮኛህን አገኘሀት?" አለችኝ

"አልፈለኳትም" አልኳት::

"ቀጣፊ!" አለችኝ::

"ሙች" ስላት:-

"ልክ አይደለህም" አለችኝ::

"ልክ ነኝ እባክሽ:: ከተወችኝ መተው ነው:: ይልቅ የምትጠጭው ያዥ:: በነገራችን ላይ አልጋ እንዴት ነው?"

"ይገርለሁኝ" ብላኝ ድራፍት ልታመጣ ሄደች:: ወደ ሰዎቹ ወሬ ጆሮዬን ጣል አደረኩ::

"ለመሆኑ መመሪያቸው ምንድን ነው?" አለ ራሰ በራው::

"ዲሞክራሲ ነው" ሲል ጥርሰ በላዛው ሁሉቱም ሳቁ:: እኔም ፈገግ አልኩኝ::

"ጠሩ ነው አንተው ጉድ የሰራን፤ ሸንጡን ገትሮ ቢዋጋ ይኸ ሁሉ ነገር አይመጣም ነበር" አለ ራሰ በራው::

"ጠሩ ምን ያድርግ ብለህ፤ እንደምንሰማው ከሆነ እያንዳንዱ የጦር ግንባር በገንዘብ ተቸብችቧል አሉ:: በዚህ ላይ ጀኔራሎቹ እየጣሉት ይፈረጥጣሉ" ሲል መለሰለት::

ፅጌ መጥታ ስለቆመች የነሱን ጨዋታ ማዳመጡን ተወት አድርጌ ወደሷ መለስ ብዬ:- "መቀመጫ አጣሽ?" አልኳት::

"የለም፤ በሙሉ ተይዟል" አለችኝ:: እኛ ሶስተኛ ስንይዝ የጠረጴዛ ባልደረቦቼ ሂሳብ ከፍለው ሄዱ:: ብርጭቆዎቹን አነሳስታ ስትመለስ:-

"እራታችንን እንብላ፤ እርቦኛል" አለችኝ:: ገንዘብ እንደያዝኩ አውቃለች::

"እሽ" ብያት ይዠው የነበረውን ድራፍት ጨልጬ ቀድሜያት ወደ ምግብ አዳራሽ ገባሁኝና ጥብስ አዘዝኩኝ:: ቁርጥስ እሷኑ ብቆርጥ ይሻለኛል::

ጥብሱ ቀርቦልን እየበላን እያለን "በቃ በእጮኛህ ጨከንክባት ማለት ነው?" በማለት ከፊቴ ላይ አንዳች ነገር የምታነብ ይመስል ትክ ብላ ታየኝ ጀመር።

"እውነቱን እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ?"

"እስቲ ንገረኝ።"

"እንዳንቺ ድንገት ያገኘኋት ፍቅረኛዬ እንጅ እጮኛዬ አይደለችም። ግን ለብዙ ጊዜ በፍቅር አብረን ቆይተናል" ስላት፡-

"እስቲ እጅን ምታኝ" ብላ እጇን ወደኔ ዘረጋች። መታኋት። ልክ የግሏ ያደረገችኝ ያህል ደስ አላት። እንዳጤንኳት ቶሎ ፍቅር የሚያጠቃት፣ እና ደግሞ ቅናት የሚጠብሳት አይነት ናት። ምስኪን፤ አሳዘነችኝ። ቡና ቤት ገብታ ተንገረገበችው። ዛሬ አንዱን ነገ ሌላውን። በቃ ጥቂት ብሮች መለቃቀም፤ ሽቶ መግዛት፤ ያችን መቀባባት፤ ብልጭልጭ ልብሶች ለብሳ መብለጭለጭ... ጊዜውም ፍሬ የሌለው ብልጭልጭ ጊዜ ነው...

"ቡና ቤት ኖሯል የምትሰራው?" ስትል ጠየቀችኝ።

"ነገሩስ የቢሮ ፀሀፊ ነበረች" ስላት በንቀት ከንፈሯን ለጠጥ አድርጋ፡-

"ይችስ ሸጣሃለች። ደግሞ የቢሮ ፀሀፊዎች ሁሉ አይደል እንዴ የሚጎትታቸው። ቡና ቤት ያለነው በቁርጡ እንሻላለን።"

"እስቲ መሻላችሁን ወደፊት ባንቺ ላያችሁ አይደል" አልኳት።

እራታችንን በልተን ወደ መጠጥ ቤቱ ስንመለስ ሰዉ ሄዶ መጠጥ ቤቱ ጭር ብሎ ነበር። ጊዜውም ጭርር ብሏል... እኛንም ጊዜው አላዘናናንም። ወዲያው ሰአት ደረሰ።

ሂሳቧን እስረክባ እየተጣደፍን ወደ ፎቁ ስንወጣ አደናቅፍዋት ባፍጢሟ ልትደፋ ስትል፡- "እኔ ልደፋልሽ!" ብዬ ቀለብኳት። ጥርሶቿ ሊረግፉ ነበር። በሳቅ ተንካካች። ለብ ብሏታል።

ለካ የፍቅርም ጣእሙ የሚታወቀው ሲደገም ነው። ከትናንቱ የተለየች ሆነችብኝ። አቤት ትንፋሻችን! ላባችን ደግሞ ምንድን ነው? ሰውነታችን ጨርሶ ቀለጠ...

"መጥቼ እጠይቅሃለሁ።"

"እሺ።"

"አይከለክሉም አይደል?"

"አይከለክሉም።"

የፍቅርና የሰላም ሌሊት ነበር። ኢትዮጵያ ብቻ ነች የልጆቿን ፍቅር አጥታ ሰላሟ ተናግቶ የምትታመሰው፤ እኔና ፅጌስ በሰላም አነጋነው።

ጧት ቀድሜያት በመነሳት ልብሴን ስለባብስ በጀርበዋ ጋደም እንዳለች ታየኝ ነበር።

"ተነሽ እንጅ" አልኳት።

"እሁ!" አለች ለመነሳት እየተንጠራራች። ትክት ብሏታል። አይፈረድባትም። ሁለት ሌሊት... ያለእረፍት፤ እኔም በፅናት ይዞው እንጅ ራሴ ኸው ሲልብኝ ይታወቀኛል።

ልብሷን ለባብሳ እንዳበቃች ሃምሳ ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠኋት።



"እቁብ ደርሶብኝ እንጅ አልቀበልህም ነበር። ዝርዝር የለህም?" አለችኝ።

"የምን ዝርዝር?"

"ያምሳ ብሩ። መልስ የምሰጥህ ስለሌለኝ ነው።"

"መልስ አያስፈልገኝም።"

"እንዴ! እስረኛኮ ነህ" አለችኝ።

"እስረኛ አይደለሁም። ታዳሽ ነኝ። አዲስ ሰው እንድሆን" ሳቅ አልኩኝ፤ በገዛ አነጋገሬ። ቃል ሳትናገር ተከተለችኝ።

ቁርሳችንን በልተን አውቶብስ ተራ ስንገባ የሰዉ ትርምስ ለጉድ ነው። ስንጋፋ፣ ላይ ታች ስንል ባንድ ሰአት የሄድን ኸምስት ሰአት ደረስን። ትግስቴን ጨረስኩ። ፅጌን ወደ ቤትሽ ሂጂ ብላት እንቢ አለችኝ። በዚህ ላይ ፀሀዩ እናት ይነድላል። የሰኔ ፀሀይ አይጣል ነው። ፅጌ እኔ በሄድኩበት ትከተለኛለች። ከንፈሮቿ ደርቀዋል። ድክም እንዳላት እርምጃዋ ያስታውቃል።

ግፊያውን ባለመቻሌ አንድ ሀሳብ ስለመጣልኝ እየገሰገስኩ ወደ ስምሪት ክፍሉ ገባሁ። ፅጌም ተከትላኝ በመግባት ከኋላየ ቆመች። ቱታ የለበሰች ሴት ለሹፌሮች የመውጫ ወረቀት ትሰጣለች። ልቅና እንዳላት ተረዳሁ። ሹፌሮቹ ሁሉ ይሽቆጠቆጡላታል።

"የኔ መቤት ችግር ገጥሞኝ ነው። ተባበሪኝ። ሆለታ ሀጅ ነበርኩ። መኮንን ነኝ። ይኸውና ከጧት ጀምሬ እስካሁን ድረስ ብጋፋ ወረፋ አልደረሰኝ አለ" አልኳት።

"አንቻስ?" አለቻት ፅጌን ለኔ መልስ ከመስጠቷ በፊት።

"የኔ ባለቤት ነች" ስላት፡-

"እስከነ ባለቤትዎት ነው እንዴ እጅዎን የሰጡት?" አለችኝ። ተሳሳቅን። ምን ይደረግ። ደግነቱ እንዲህ ብላኝ አልቀረችም። ይዛኝ ወጥታ ላንድ የመለስተኛ አውቶቢስ ሹፌር ሰጠችኝ። ያቆያት።

"ሳምንት እሁድ እመጣለሁ። እንድትጠብቀኝ።" አለችኝ ፅጌ አውቶቢስ ውስጥ ከመግባቴ በፊት ስንሰነባበት።

"የመኪና ችግር አለ። እንደምታይው ነው። ከስራሽ እንዳትሰናከይ።"

"ግዴለህም፣ እንደ ሰው እሆናለሁ።" ብላኝ ወደ ቤቷ ሄደች። አይኖቼ ተከትለዋት ነበር። ተሃድሶ ይሏል እንዲህ ነው። በዚህ ሁኔታ ነበር ፅጌ አድሳ የለቀቀችኝ። የኢህአዲግ ተሃድሶ ነው ደብዛው የጠፋ!

# ምእራፍ ሰባት

*አስበን እንስራ ለነገም እንዲሆን፣*
*ይሁን ይሁን ብለን የማይሆን እንዳይሆን።*

## 16

ቀኑ ሰኔ 24 ቀን 83 ዓ.ም. ነው። የሽግግር መንግስቱ የሚመሰረትበት እለት።

ሌሊቱን ዝናብ ሲወርድ ነው ያደረው። ከውጭ በየጥጉ የተኙት መኮንኖች ሲንጫጩ ነው ያነጉት። ቀኑ አሁንም ቢሆን እንደ ጨፈገገው ነው። የመኮንኖቹም ፊት እንደ ቀኑ ምርግ ያለ ነው። በየመኝታቸው ላይ ተደምመው በሀሊናቸው እንዳች ነገር የሚዳስሱ ይመስላሉ። ከኔ ጎን የሚተኛው መኮንን ተጠቅልሎ እንደተኛ ነው። ፊፅሞ ተስፋ ቆርጧል። ደግሞ ሲጋራ አጭያሽ ነው። ሱስም ሳይገለው አይቀርም። እርሃብም ጎድቶታል። ለምን እንደሆነ እንጃ መኮንኖቹ አያቀርቡትም። ድሃ በመሆኑ ይሆን? ሊገባኝ አልቻለም። እሱም ቢሆን ከማንም አይጠጋም። ደስ ሲለው ትንሽ ከኔ ጋር ይነጋገራል። በተረፈ ዝም ነው። አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ተጠቅልሎ በመተኛት ነው። መኝታ ሲበዛ ደግሞ መጥፎ ነው። እርሃብም ካንጀት ይገባል። ስሙን ገና በቅርቡ ነው ያወኩት። መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ይባላል።

የወታደር ጃኬቴን እስከ አንገቴ ድረስ ቆልፌ በመልበስ፣ ፎጣ ደግሞ በመከናነብ ከመኝታየ ተቀምጨ መፅሀፍ አነባለሁ። ሻምበል በድሉና ሻምበል አዱኛ እንደተኙ እፍላፍ ገጥመው ያንሾካሹካሉ። የሚሉት አይሰማኝም።

መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ድንገት ከተኛበት ወርጫ ሲል ጎኔን በክርኑ ስለጎሸመኝ ትንሽ ፈቀቅ አልኩኝ።

"ይቅርታ" አለኝ ከራሱ ቀና አለና።

"ምንም አይደል" አልኩት። ደጋግሞ አዛጋና ተመልሶ ተኛ። ከነጋ ምንም ነገር አልቀመሰም። አንጀቱ ታጥፍዋል። ብዙም ሳይቆይ ብርድ ልብሱን እንደለበሰ ተቀመጠ። አሁንም ደጋግሞ አዛጋና ትክ ብሎ አየኝ። አስተያየቱ አንድ ነገር የመሻት ነው።

"ምን ልርዳህ?" አልኩት እነበው የነበረውን መፅሀፍ አጠፍ አድርጌ በመያዝ።

"ያንዲት ሲጋራ መግዣ ሀያ አምስት ሳንቲም" አለኝ።

"እሽ" አልኩትና በነጠላ ጫማ ወደ ውጭ ወጣሁና ቆም ብዬ ላፍታ አካባቢውን ቃኘሁት። ዝናብ ያደረባቸው መኮንኖች ልብሳቸውን ያሰጣጣሉ። ጥቂት መኮንኖች ደግሞ ወደ ላይ ወደ ታች ይንከላወሳሉ። ፊታቸው እንደ ቀኑ የከፋ ነው። በሀሳብም፣ በብርድም ተጨባብጠዋል።

ከሲጋራ አዟሪዎች ላይ አንድ ፓኬት ኒያላ ገዝቼ በመግባት ስሰጠው "ምነው መቶ አለቃ ጎርፉ? መግዛቱንማ እኔ እገዛው ነበር። ደግሞ የጠየቁህ ያንዲት ሲጋራ መግገ ነበር። አይይ...! እግዚአብሄር ይስጥህ" አለኝ።



"አሜን" ብዬው ተቀመጥኩ። ተስገብግቦ ነበር ክብሪት ጭሮ አንዱን ሲጋራ ያያያዘው። ጠምቶት ኖሯል። እያከታተለ ያቦነው ጀመር። ሰረቅ እያደረኩ አየዋለሁ። ያለማቋረጥ አንዷን ሲጋራ አጭሶ ጨረሰና ከዚያው ላይ ሌላ ለኮሰ።

"በባዶ ሆድህ ሲጋራው አይጎዳህም? ባታበዛ ጥሩ ነው" ስለው፦

"ይጉዳኝ፤ መኖር አልፈልግም" አለኝ።

"አይዞህ ተስፋ አትቁረጥ" አልኩት። ቶሎ መልስ አልሰጠኝም፤ በጭሱ ውስጥ አንድ ነገር የሚያይ ይመስል ነበር። በሀሳብ እርቆ ሲያይ ቆየና ድንገት ፈገግ ብሎ፦

"ልጆች አሉህ መቶ አለቃ ጎርፉ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የሉኝም።"

"ሚስትስ?"

"የለኝም። ጠብደል ወንደላጤ ነኝ።"

"ታድለህ" አለኝ።

"መታደል አደረከው። እኔ ደግሞ ባልታደል ነው የምለው" አልኩት።

"የለም፤ መታደል ነው። ለምሳሌ እኔ ዛሬ ልጆቼና ሚስቴ ባይኖሩብኝ ኖሮ ላንድ ህይወቴ አልጨነቅም ነበር። የልጅን አስፈላጊነት አጥቼው እንዳይመስልህ። ሁሉም ነገር ሲደላ ነው ደስ የሚለው። በእውነት ነው የምልህ ለጆቼ የሚቀምሱት የላቸውም። በኑሮየ መሰረት የለኝም። በረሃ ለበረሃ ስንከራተት ነው የኖርኩት። ልጆቼ የንጀራ እርሃብ ብቻ ሳይሆን የኔም ርሃብ አለባቸው። እኔም ብሆን ልጆቼ ይርቡኛል፤ ሚስቴ ትናፍቀኛለች። አንድም ቀን ቁጭ ብዬ አጫውቻቸው አላውቅም። ሁልጊዜም በደብዳቤ። መደምደሚያውም ስቃይ ሆነልህ..."

"አይዞህ፤ ዛሬ 24 ቀን አይደለም? የኛም ችግር እልባት ያገኝ ይሆናል?" ስለው እንደ መሳቅ አለና፦

"ከንቱ ተስፋ ነው መቶ አለቃ ጎርፉ። ወያኔዎችን ደህና አድርጌ አውቃቸዋለሁ። ዘመዶቼ ናቸው። ቅንጣት ካላማቸው ንቅንቅ አይሉም። መነሻቸውን ካወክ መድረሻቸውም አይጠፋህ። በቀለኞች ናቸው።"

"ትግሬ ነህ እንዴ ጓድ መቶ አለቃ?" አልኩት ትንሽ ፈገግ ብዬ።

"ንፁህ ትግሬ አይደለሁም። አማራም ነኝ። አንዱም የሚያሳዝነኝ ይኸ ዘር ቆጠራ ነው። እኔ ከማንኛው ወገን እንደ ምሆን ወደፊት እንጃልኝ? አባቴ ጎንደሬ ነው። እናቴ ደግሞ ትግሬ ነች። አባቴ ፖሊስ ነበር። በስራ ምክንያት ትግራይ ሄዶ ነው እናቴን አግብቶ እኔን የወለዱት። ቢደንቅህ ባለቤቴ ግማሽ አደሬ፣ ግማሽ ኦሮሞ ናት። ሀረር 3ኛ ክፍለ ጦር እያለሁ ነው የተጋባነው። እንግዲህ የኛ ልጆች የየትኛው ብሄረሰብ አባል ሊሆኑ ነው?" አለና ሶስተኛ ሲጋራ አቀጣጠለ።

"እረ ሲጋራው ይጎዳሃል!"

"ይጉዳኝ አንተው። ኢትዮጵያ ከንግዲህ የኔ አትሆንም። ንፁህ ዘሮች ይፈንጩባት!" አለ ምርር ብሎ።

"ተው መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል፤ እንደዚህ አይባልም:: በኔ ይሁንብህ፤ ከዛሬው ኮንፈረንስ አንድ ውጤት እናገኛለን:: እርግጠኛ ነኝ የግንቦትን ወር ደመወዛችንን ይሰጡናል::"

"በዚህ ተስፋ አታድርግ:: አጉል ተስፋ በሽታ ነው:: መብታችንን የሚጠብቁ፣ ደመወዛችን የሚሰጡን ቢሆን ኖሮ እኛን ከዚህ ድረስ ማምጣት ባላስፈለጋቸው ነበር:: ሲያታልሉን ነው:: እኛ መቼም ሁልጊዜ እንደተታለልን ነው:: ሀይለስላሴ አስር እጅ ዋሽቶ ነበር:: ደርግ ደግሞ ሺ ጊዜ ዋሽቷል:: እነዚህ ደግሞ ገና ሚሊዮን ጊዜ ይዋሻሉ:: እድገት ነው" አለኝ:: ማፅናናት አልሆነልኝም:: አንገቴን ደፋሁ:: እሱም ዝም ብሎ ሲጋራውን ይለበልብ ጀመር:: ሳየው ፓኬቱ ካላለቀ በስተቀር የሚያቆም አይመስልም::

ሻምበል በድሉ ጫኔና ሻምበል አዱኛ ደቻሳ ከመኝታቸው ተነስተው ጠቅሰውኝ ወደ ውጭ ወጡ:: መፅሀፌን ከራስጌየ አስቀምጬ ተከተልኳቸው:: ፀሀይዋ አሁን ፍዋ...! ብላለች:: ወደ ዳገቱ ሄደው ጠፍታ ቦታ መርጠው ተቀመጡ::

"ለምን ነበር የፈለጋችሁኝ?" አልኳቸው ከተቀመጥኩ በኋላ::

"ከዚያ መቶ አለቃ ጋር ምንድን ነበር ስታወራ የነበረው?" ሲል በድሉ ጠየቀኝ::

"የግል ችግሩን ነበር ሲያወራኝ የነበረው" ስለው አዱኛ ቱግ አለና:-

"ምን የግል ችግሩን ያወራሃል! 'ወያኔዎችን አውቃቸዋለሁ፤ ዘመዶቼ ናቸው...' ይልህ አልነበረም?" አለኝ ልክ እንደ ህፃን ልጅ በማፋጠጥ::

"ይህን ያለኝ ታዲያ ከግል ችግሩ ተነስተን ስናወራ ነው..." ስለው በድሉ ደግሞ አቋረጠኝና:- "ዋናው ነገር ሰውየው የኢህአዲግ መረጃ ስለሆነ ብትጠነቀቅ ይሻልሃል! ትግሬ መኮንኖችን ብዙ ባንቀርባቸው ጥሩ ነው" አለኝ::

"እረ በፈጠራችሁ እሱ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ነው:: ችግር ነው የሚያቆላምመው::"

"አንድም ችግር የለበት:: አውቆ ነው ችግረኛ በመምሰል ተቆልምሞ እየተኛ የሚያደባው:: ደግሞ ካንተ ላይ ነው ጥላውን ያጠላው" አለኝ አዱኛ::

"ምንድን ነው የምታወራው? ለመሆኑ እሱ ከኔ ምንድን ነው የሚያገኘው? ከንቱ ሃጢአት አትግቡ" አልኩኝ ቆጣ ብዬ::

"ብቻ ብትጠነቀቅ አይከፋም:: መኮንኖቹ ሁሉ አውቀውት ነቅተውበታል:: አንተ ብቻ ነህ ያልነቃህበት" አለኝ በድሉ::

ሁለቱን ተከራክሬ ማሸነፍ ስላቃተኝ አኩርፌ ጥያቸው ወደ መኝታ ክፍል ገባሁ:: ሀይለ ሚካኤል ተኝቶ ነበር:: ለካ የመኝታ ክፍላችን መኮንኖች የማያስጠጉት ለዚህ ነው:: እውነት የኢህአዲግ መረጃ ይሆን? እረ ይኸ ኮንፈረንስ ተካሄደ በተገላገልነው::

ኮንፈረንሱ ልክ ዘጠኝ ሰአት ከሀያ አምስት ደቂቃ ሲሆን ተከፈተና መጠነኛ መተዋወቅ አድርጎ የመነጋገሪያ አጀንዳዎችን አፅድቆ ለቀጣዩ ቀን ተቀጥሮ አበቃ::

«ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
ግብሩ እንቁላል ነበር አህን ጊዜ አበሻ!»

በማግስቱ፣ ሰኔ 25 ቀን ኮንፈረንሱ በመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ከመረጠ በኋላ የመነጋገሪያ ቋንቋ አማረኛና እንግሊዘኛ እንዲሆን ተወሰነ:: እንደ አማራጭ አረብኛም ቀርቦ ነበር:: የፈለገ ደግሞ በራሱ ቋንቋ ባስተርጓሚ መናገር እንደሚችል የዲሞክራሲ መብት ተሰጥቶታል:: ሁላችንም ጆሮዎቻችንን ከሬዲዮኑ ለግተናል:: አብዛኛው ተሰብሳቢ እየጎላ ይናገር የነበረው «ስለ መቶ አመት ታሪክ» ነበር:: ያንዷ ብሄረሰብ ተወካይ ምርር ባለ አነጋገር:- «... ከምኒልክ ጀምረን ተጨቁነንና ተረግጠን የኖርን ነን:: እንኳንስ ለመንግስት ስራ ልንመከር ቀርቶ ከሸንኮራ አገዳ ቆረጣም ወጥተን አናውቅም:: ሌላው ቀርቶ ስማችን ጌዶብ የተባለው ገዳሙ እየተባለ ያማራ ስም እየተሰጠን ወግና ባህላችን ተረግጦ ነበር:: ዛሬ ለዚህ በመብቃታችን ከልብ ተደስተናል::»

ሌላው አከራካሪ ነጥብ የኤርትራ ጉዳይ ነበር:: «መዋጋት ለሚፈልግ መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት!» አሉ አዲሱ ፕሬዚዳንት:: እስካሁን የተከፈለው መስዋእትነት መለስ ዜናዊን ፕሬዚዳንት ለማድረግና ኤርትራን እስከ ማስገንጠል ድረስ ነበር ማለት ነው::

ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ ደግሞ የባንዲራ ጉዳይ ነበር:: ለዚህ ጥያቄ ፕሬዚዳንቱ ሲመልሱ ልክ ቁስላቸው የተነካ ያህል ተቆጥተው ነበር:: «... እኛ ከጨርቁ ነገር የለንም! ከጨርቁ በስተጀርባ ካለው እንጂ! ለማንኛውም ስለባንዲራ ጉዳይ ወደፊት የኢትዮጵያ ህዝብ የሚወስነው ይሆናል!» ብለው ባጭሩ ዘጉት:: የኛም የማዳመጥ ስሜት አብሮ ተዘጋ::

ኮንፈረንሱ ስለኛ ጉዳይ አንድም ነገር ሳያነሳ ተጠናቀቀ:: አብዛኛው መኮንን ክሽልሽል ነበር ያለው::

ወደ ማታ ገደማ እኛ ሶስታችን፣ አራተኛ ኮሎኔል ዘርጋው ሆነን ስለኮንፈረንሱ ማንሳት መጣል ያዝን:: ዳገቱ ላይ ነበር የተቀመጥነው::

"እንዲያው ጎበዝ ይኸ አማራ የሚወነጀልበት መብዛቱ:: ሰው ሙቼስ አካባቢ የሚፈጥረውን ሰርቶ ይኖራል:: አሁን አገዳ ቆረጣን ምን አመጣው? ይህም ይሁን ቢሻው:: 'ጌዶቦን ገዳሙ....' ተብሎ የተነገረው እውነት የኢትዮጵያ አጣዳፊው ችግር የስም ለውጥ ነው? ደግሞስ ሙቼ ነው አማራ ስማችሁን ለውጡ ያለው? እረ ወዲያ! ከደርግ የባሰ ሆያ ሆየ!" አሉ ኮሎኔል አዝነው::

"እየ ጌታየ! ወደፊት ከነ አገዳ ቆረጣው ሲያጣው ያነየ ደግሞ 'ድሮስ አገዳ ቆርጠን በሰላም እንኖር ነበር፤ ዛሬስ ከነ አገዳ ቆረጣውም አጣን' ብሎ የሚናገርበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም" አላቸው በድሉ::

"ልክ ነህ:: ይኸ የማይቀር ነው:: በዚህ አይነትማ ምኑን ሰላም ተፈጠረው" አሉት:: አዱኛ ደግሞ ቀበል ብሎ:- "ጌታዬ ባንዲራችንን ፕሬዚዳንቱ 'ጨርቅ' አሏት ሲላቸው:-

"ኤዲያ! ማቅም ይበላት! ከሱ የምንጠብቀው ነው!" አሉት:: በዚህ ጊዜ እኔ ካጎነበስኩበት ቀና አልኩና:-

"ዋናው ነገር ወሳኙ ህዝቡ ነው:: ሁልጊዜ ባለ ጮሌዎች መነዳት የለበትም:: የጎበጠውን ማቃናት፣ የተጣመመውን ማስተካከል አለበት:: የደርግ ድለቃ ይበቃናል:: ጦርነት የኋላ ቀርነት ምልክት ነው::

የሙቶ አመት ታሪክ እየጠቀሱ ጦር ጠማኝ ማለት ወደባሰ ችግር ነው የሚከተን:: በዚያን ጊዜ ስህተቶች ተፈፅመው ሊሆን ይችላል:: ታዲያ እንደነዚያ ያሉ ስህተቶች እንዳይደገሙ መጣር እንጅ ማባባስ ለማንኛችንም የሚበጅ አይምስለኝም:: ታሪክን መጋራት እንጅ ላንድ ብሄረሰብ ብቻ መቆለልም የኋሏ ኋላ ፀፀት ላይ የሚጥል ይመስለኛል:: 'ዘማች አማራ፣ ጦረኛ አማራ፣ ያንድነት ጠበቃ አማራ፣ ነፍጠኛ አማራ፣ ባንዲራ ያማራ፣ ኢትዮጵያ ማለት አማራ' እየተባለ የሚነገረው ትክክል አይመስለኝም:: ስም የሌለው የሰው ስም ያጠፋል:: ታሪክ የሌለውም የሌላውን ታሪክ ያጎድፋል:: ቅርስ የሌለው ቅርስ አልባ ያደርጋል:: ዛሬ የተያዘው ይህን ይመስላል:: አሳዛኝ ኢትዮጵያ!' ስል አምርሬ ተናገርኩ::

"ልክ ነህ" አሉ ኮሎኔል ራሳቸውን እየወዘወዙ:: ከዚህ በኋላ የረባ አልተነጋገርንም:: ድንገዝገዝ እንዳልን ነበር የተለያየነው:: ሰማዩም ክብድብድ ብሏል:: የኛም ፊት ከብዷል...

# 17

የጠበቅነው ቀርቶ ያልጠበቅነው መጣ፣
አባቡን ብንቀብረው ከስር ጊንጡ ወጣ::

በየክፍለ ጦራችን እንድንሰባሰብ በድምፅ ማጉሊያ የተነገረን ቁርሳችንን በልተን እንዳበቃን ነበር:: ከኮንፈረንሱ በኋላ ስንሰበሰብ የመጀመሪያ ጊዜያችን ስለሆነ የታመሙ እንኳን አልቀሩም:: ከሀውልቱ ፊትለፊት ከዳገቱ ላይ ነበር የተሰበሰብነው::

ሶስት የኢህአዲግ አባላት እየተጣደፉ መጡና ከፊት ለፊታችን ቆሙ:: ቶሎ ንግግር አልጀመሩም:: እኛ ደግሞ ቸኩለናል:: አንድ አይነት ውሳኔ እንደያዙልን ቅንጣት አልተጠራጠርንም:: እስበሳቸው አንሾካሽኩና አንዱ ታጋይ ወደኛ ወጣ ብሎ በድምፅ ማጉሊያ በመጀመሪያ ኮንፈረንሱ እንዴት ተጀምሮ በምን መልክ እንደተጠናቀቀ አጠር አድርጎ ካብራራልን በኋላ የድጋፍ ሰልፍ እንድናደርግ ስልት በተሞላበት ሁኔታ በመግባቢያ ቃላት ያጎርፍልን ጀመር:: እኛ ገነፈልን:: አንድ መኮንን ብድግ ብሎ:-

"በመጀመሪያ መብታችንን ጠብቁልን:: ከዚያ ደግሞ ስለ ኢህአዲግ አላማና ፕሮግራም በሰሚናር መልክ ይሰጠን:: ከዚህ በኋላ የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ እንችላለን" ብሎ ሲቀመጥ ሌላው መኮንን ተነስቶ:-

"ሰልፉንም ሆነ ሴሚናሩን ቀስ ብለን እንደርስበታለን:: ጊዜ የማይሰጠው እርሃብ ነው:: ደመወዛችንን ስጡን:: ቤተሰቦቻችን በርሃብ አይለቁ!" ሲል ጠቅላላ መኮንኑ ሀሳቡን ደግፎ አጨበጨበ:: ሶስተኛ መኮንን ተነሳና ደግሞ:-

"እኛ የኢትዮጵያ መኮንኖች እንጅ የደርግ መኮንኖች



አይደለንም:: ለምንድን ነው በማስ ሚዲያ 'የደርግ መኮንኖች' እያላችሁ የምትጠሩን?" አለ::

"ይኸ አያጣላንም:: ወደፊት እንዲስተካከል እናደርጋለን' ሲል ታጋዩ መልስ ሰጠ::

"እኛም ሰልፉን የምንሰለፈው ደመወዛችንን ስትሰጡንና ስታስተካክሉ ይሆናል" ሲል አንድ መኮንን ተሽምቆ መለሰ:: ከዚህ በኋላ ፊዕሞ መጣጣም አልተቻለም:: ከፍተኛ መቃቃር ተፈጠረ:: የኛ ቁጣ እየበረታ መጣ::

"እሽ እረጋ በሉ" አለንና ፀጥ ስንልለት "ያለፍላጎታችሁ በግድ ተሰለፉ አንላችሁም:: ነገር ግን አንድ እውቃችሁት መሄድ የሚገባችሁ ጉዳይ አለ:: ይኸውም በነዚህ ሶስት ቀናት ውስጥ ወደ ጦላይ ትሄዳላችሁ:: የተሃድሶ ትምህርቱን ለመጀመር በዚህ በተጨናነቀ ሁኔታ አይቻልም" ሲለን ጠቅላላችን ኩምሽሽ አልን:: ድንገተኛ መብረቅ ነበር የመታን:: ወዲያው ጥለናቸው ተበተን::

"ያልኩት እውነት አልሆነም ታዲያ ሙቶ አለቃ ጎርፉ" አለኝ ሙቶ አለቃ ሀይለ ሚካኤል:: ወደ ክፍል ጥልቅ ብዬ ከመኝታዬ ላይ ከመቀመጤ :: እሱ ቀድሞኝ በመግባት ከመኝታው ላይ ተቀምጦ ሲጋራ ያጨስ ነበር:: እሱም ጭሷል...

"አንተስ ብለሃል" አልኩት እራሴን እየነቀነኩ::

"እኔ ሀይለሚካኤል ካሁን በኋላ የነሱ መጫወቻ አልሆንም!" አለና ሌላ ሲጋራ አቀጣጠለ:: ሰውነቱም በንዴት ተቀጣጥሏል:: ከዚህ በኋላ አልተነጋገርንም::

መኮንኑ ሁሉ ሌላ ወሬ የለውም፤ ስለጉዟችን ሁኔታ ነው:: ግማሾቹ "ሰልፉን ብንሰለፍ ኖሮ ከዚህ አያነሱንም ነበር" ይላሉ:: ግማሾቹ ደግሞ "የለም፤ ብንሰለፍም ከዚህ መልቀቃችን የማይቀር ነው:: እንኳንም አልተሰለፍን!" እያሉ እልህ ይተናነቃቸዋል:: አንዳንዶቹ ደግሞ "የጦላይ ወባ ቀንጥስ ነው፤ እባቡና ዘንዶውም መከራ ነው:: ብዙ ብሄራዊ ወታደር ተውጦ ቀርቷል" ይላሉ:: እኔ ጦላይን አላውቀውም:: ጭንቅ ጥብብ አለኝ:: እረ ከመሄዳችን በፊት ደግሞ ዕኔ በመጣችልኝና በተሰናበትኳት::

# 18

ዛሬ እለተ ሰንበት ነው፤ ዕኔ እንደማትቀር እርግጠኛ ነበርኩ:: የማለዳ ቤተሰቦች በድምፅ ማጉሊያ ሲያስጠሩ ይሰማኛል:: ወደ ውጭ ስወጣ ሙቶ አለቃ ሀይለ ሚካኤል ልብሱን በሚገባ ለብሶ፣ ፀጉሩን አበጣጥሮ ጫማውን ያስወለውላል:: እንደዚህ ሆኖ ሳየው ደስ አለኝ:: ዘወር ብሎ አየኝና:_

"ሙቶ አለቃ ጎርፉ፣ እፈልግሃለሁ" አለኝ::

"እሽ" አልኩት:: ገብቶኛል:: የሲጋራ መግዣ ሊጠይቀኝ ነው:: ጫማውን አስወልውሎ እንደ ጨረሰ ካጠገቤ መጥቶ ቆመ::

"ለምንድን ነበር የፈለከኝ?" አልኩት::

"ልሰናበትህ ነው" ሲለኝ ደንገጥ አልኩና:-

"የት ትሄድ?" አልኩት ትክ ብዬ እያየሁት:: የተሟላ አለባበስ ይልበስ እንጅ ፊቱ የበረገገ ነው::

"መሄዴ ነው:: ዳግመኛ አንገናኝም:: እስካሁን ድረስ ላደረክልኝ የሞራል ድጋፍ ከልብ አመሰግንሃለሁ:: ከኛ ክፍል የሚተኙት መኮንኖች አይወዱኝም:: በጠላት አይን ነው የሚያዩኝ:: በግማሽ ትግሬ በመሆኔ የኢህአዲግ መረጃ ነው ብለው ይጠረጥሩኛል:: ማን እውነተኛ እንደሆነ ግን ወደፊት ያዩታል:: አንተ ግን ከዚህ ጭንቅ ይገላግልሀ" አለኝ::

"ለተራ አሉባልታው ቦታ አትስጠው:: ይልቅ ልትጠፋ አስበህ ከሆነ ሊይዙህ ይችላሉ" ስለው:-

"አይዙኝም:: ካሁን በኋላ ስጋዬን እንጅ ነፍሴን አያገኟትም::" አነጋገሩ ሁሉ ጠጠረብኝ::

"ከኢትዮጵያ ውጭ ለመውጣት አስበህ ከሆነ ባሁኑ ሰአት የሚቻል አይመስለኝም:: ያልጠበከው እንቅፋት ይገጥምሃል:: እባክህን ይህን አይነቱን አሳብ ሰርዘው::"

"አልሰርዘውም መቶ አለቃ ጎርፉ:: ልጆቼ በርሃብ እየተሰቃዩ ማየት አልቻልኩም" አለና እንደ እንባ ተናነቀው:: እኔም ጭንቅ አለኝ:: የምሰጠው መልስ አጣሁ:: በቅፅበት በመካከላችን ፀጥታ ሰፈነ:: ሁለታችንም መሬት መሬት እናይ ነበር::

"በል ቻው" አለኝ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ:: እጅ ለጅ አልተጨባበጥንም:: ጠቋሚ የማሲዘው ይመስል ቁልቁል ተጣድፎ ወረደ:: ፍዝዝ ብዬ እንደ ቆምኩ ቀረሁ:: ብዙ ተክዠ ቆየሁ:: ከሀሳቤ የነቃሁት በርካታ መኮንኖች በድምፅ ማጉሊያ "ቤተሰብ ይፈልጋችኋል" ተብለው ሲጠሩ ነበር:: ወደ ዳገቱ ሄጄ ተቀመጥኩ:: መቶ አለቃ ሀይለሚካኤልን "ይቅናው፤ያሰበው ይሳካለት" አልኩና ትኩረቴን ወደ ፅጌ አደረኩ::

ዛሬ እንዴት ተውባ ትመጣ ይሆን? ባይነ ህሊናየ ሽቅርቅር ብላ ልክ እንደ ዕጌረዳ አበባ ፈንድታ ታየችኝ:: ትምጣ እንጅ ከንፈሮቿን ግምጥ ነው የማደርጋቸው:: ጥርሶቿን ግን ምን አደርጋቸዋለሁ? አይሳሙ ነገር:: በመጀመሪያ ያየኋት ጊዜኮ ጥርሶቿ ናቸው አቅሌን ያሳጡኝ:: ውሸት ምን ያደርጋል፤ የደም ገንቦ ነች እንጂ በመልክ ከየኔነሽ አትደርስም:: በፍቅር ግን ማንኛቸው ይበልጣሉ? ለመለየት ተቸገርኩ:: አየ የሚቻል ቢሆን ከሁለቱ መሀል ተኝቼ አንድ ጊዜ ወደ ፅጌ ሌላ ጊዜ ወደ የኔነሽ እየዞርኩ ማጣጣም ነበር:: ለምንድን ነው ግን የኔነሽን ካንጀቴ ላወጣት ያልቻልኩት? አንድጊዜ እራቁታችንን አሳብዳኝ ነበር:: ምናልባት በዚህ ምክንያት ይሆን? ከዚያ በፊት ግን እንኳን እራቁቴንና ከብርድ ልብስም ውስጥ ሆኘ መብራት ካልጠፋ በስተቀር አልሞከርም ነበር:: በጣም አፋራም ነኝ:: አጅሬት ግን መብራቱን ሳታጠፋ እራቁቴን አድርጋ ስታንከባልለኝ አደረች:: ከዚያን በኋላ «ሞኝ ያሲያዙትን አይለቅም» እንዲሉ እራቁታችንን ካልሆነ በስተቀር አይጥመኝም:: ሁልጊዜም የሚታየኝ ታዲያ ከኔ ጋር እንደምትቀብጠው ሁሉ ከሌሎቹም ወንዶች እንዲሁ እንደምትቀብጥ ነው:: በሷ የምቀናውም ለዚህ ነው:: ከሌሎች ሴቶች ጋር ብተኛም ላመል መክሰያ



ያህል ካልሆነ በስተቀር የሚጥመኝ ነገር የለም:: ገና ባለፈው ፅጌን አገኘሁ:: እሷም አልጋ ላይ እብድ ነች::

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው፤ ከድምፅ ማጉሊያው ድረስ ዘመድ ይፈልግሆታል" ተባልኩ:: ከተቀመጥኩበት ፈጥኘ በመነሳት ተንደርድሬ ወረድኩ:: ወዲያው አይኖቼ ፅጌን ፈቀዳ ገቡ:: አየኋት:: ካጠገቧ አራት ያህል ሴቶች ቆመዋል:: የሁሉም አስተያየት በመገረም ነው:: የኛ ሁኔታ ሳያስገርማቸው አልቀረም:: ካጠገቧ እስከምደርስ ድረስ አላየችኝም ነበር:: አይኖቿ እርቀው ነው የሚያዩት ፤ እኔኑ ፍለጋ:: ኮት መሰል ቡላ ሹራብ ለብሳለች:: ሻርፕ ነገር ደግሞ ከትከሻዋ ላይ ደርባለች:: ለጭቃው ብላ ቡና አይነት የቆዳ ቦት ጫማ አጥልቃለች:: ከግሯ ስር ነጣ ባለ ቆዳ የተለጎመ አገልግል ጉብ ብሏል::

"ፅጌ" አልኳት፤ ዘወር ስትል አየችኝ::

"ውይ! ወዲያኮ ነበር የማየው!" አለችና በደስታ ድንጋጤ አንገቴን አቀፈችኝ:: ከንፈሮቿን አገኘኋቸው:: ልክ ማር የተቀቡ ያህል ጣፈጡኝ::

"እንቺስ ተሎ ቀናሽ" አሏት አብረዋት የነበሩት ሴቶች::

"አይዟችሁ፤ የናንተም ይመጡላችኋል" አልኳቸውና አገልግሉን ተሸክሜ መንገድ መራኋት...

"እንደዚህ ብዙ ናችሁ እንዴ?" አለችኝ ተገርማ::

"እየውልሽ እንደዚህ ብዙ ነን" አልኳትና መኝታ ክፍል ይዠት ገባሁ:: ጓደኞቼ ብድግ ብለው በክብር ተቀበሏት:: ከመኝታየ ላይ አስቀመጥኳት:: የእንግድነት ፍርሃት ይታይባታል:: እየተገላመጠች ክፍሉን ቃኘች::

"እይውልሽ እንደዚህ ተቆላልፈን ነው የምንተኛው::"

"ምንም አይደል" አለች ከንፈሯን መጣ:: ምንጊዜም ቢሆን ቤተሰብ ሲመጣ ያረፍንበትን ካሳየን በኋላ ወደ መናፈሻ ይዘን ነው የምንወጣው:: ምግብም ሆነ ጨዋታ ከዚያው በየዛፉ ስር ነው::

"ተነሽ" አልኳት እኔ ቀድሜ በመነሳት::

"የት ልንሄድ ነው?" አለችኝ እየተነሳች::

"ውጭ መናፈሻ አለ፤ ከዚያ ነው" አልኳትና እሷን አስቀድሜ ወጣን:: እነ አዱኛ አገልግሉን ይዘው ቀድመውን ሄደዋል::

"አትምጭ ስልሽ በጭቃ ደከምሽ::"

"እንኳንም መጣሁ፤ ደስ ነው ያለኝ::"

"የመኪና ችግር አልገጠመሽም?"

"የመኪናውን ችግር አታንሳው:: አውቶቢስማ ስቃይ ነው::"

"ታዲያ በምን መጣሽ?"

'አስራ ሁለት ብር ከፍየ በታክሲ መጣሁ" ስትለኝ እራሴን ነቅንቄ ዝም አልኩኝ::

"ምነው? በመምጣቴ ቅር አለህ እንዴ?"

"ለምን ቅር ይለኛል፤ በዚህ ጭቃ በመድከምሽ አሳዘንሽኝ እንጅ::"

"ለኔ መድከምስ አታስብ::"

እነ በድሉ ከትልቁ ዛፍ ስር ሄደው ተቀመጡ:: ጥሩ አድርገዋል:: ለድጋፍም፣ ለጥላውም ትልቅ ዛፍ ጥሩ ነው:: ቁጥቋጦ ምንጊዜም ቁጥቋጦ ነው...

ዙሪያውን ከበን ከተቀመጥን በኋላ አገልግሉን ከፈትነው:: የዶሮ ወጥ ከንቁላል ጋር፣ በመልክም ነጭ ጤፍ እንጀራ እፍን አድርጋ ነው ያመጣችው:: አልተረፈችም:: ያችኑ የሰጠኋትን አምሳ ብር ለዚሁ ተግባር ነው ያዋለቻት:: ገለጥለጥ አደረገችልን:: እሷ ለመቁረስ ፈራ ተባ ስትል እኛ ሽሚያ ገጠምን:: አበላላችን ይኸው ነን:: ለማያውቀን ሰው እናስፈራለን:: ይሉኝታ የሚባል ነገር አናውቅም:: አየ ሙያ! ቁንጅና ብቻ አይደለችም:: የኔነሽ በዚህ በኩል እጇን ትሰጣለች:: አንድም ቀን የሰራችውን ቀምሸላት አላውቅም:: ሳያትም ድስት ጥዳ ወጥ ሰርታ የምታውቅ አትመስለኝም:: አዲስ የሚከፈቱ ክትፎ ቤቶች ግን አያመልጧትም:: ደግሞ ወንድ እስከትላ ነው የምትሄደው:: እኔንም አንድ ሰሞን ይዛኝ ትዞር ነበር:: ዛሬስ ደስ አይበላት፣ ዕፄ አለችልኝ::

"ብይ እንጂ፣ ምን ዳርዳር ትያለሽ" ብዬ አንድ እንቁላል በፍትፍት ጠቅልየ አጎረስኳት::

"ለራስህ ብላ፣ እኔ በጄ እበላለሁኝ" አለችኝ:: እነ አጅሬ እብድ የወረወረው ድንጋይ እያስመሰሉ ከጎረሱ በኋላ አጥንቱና እንቁላሉ ሲያልቅ ፍትፍቱን እንዳለ ትተውት ተነሱ::

"ብሉ እንጂ ተዋችሁትሳ" አለች::

"ዝምበይ፣ እነሱ ሳይጠግቡ አይተውም" አልኳት:: ከኛ የተረፈውን ያካባቢው ልጆች እሰፍስፈው ይጠባበቁ ስለነበረ ለነሱ ሰጠናቸው:: ተረባረቡበት::

"እረ አገልግሌን!" አለች ስቃ፣ ሽሚያ ሲገጥሙ አገልግሉን ወዲያና ወዲህ ሲመነጫጭቁት ጊዜ::

"ልጆች፣ እንደ..! እረ ቀስ በሉ!" ብዬ ተቆጣኋቸው::

እነ በድሉ እጃቸውን አባብሰው፣ መራርቀው ጥለውን ሄዱ:: ምንጊዜም ቢሆን ሚስትም ትምጣ ወዳጅ ምግብ የጋራ ነው፣ ጨዋታ ግን የግል ነው:: ልጆቹም አገልግሉን አጋብተውልን ሄዱ::

"መቼ ነው የምትለቀቁት?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ቢደንቅሽ ገና ወደ ጦላይ ሊወስዱን ነው" ስላት ደንገጥ ,ብላ:-

"ጦላይ ደግሞ የት ነው::"

"በጅማ መስመር ነው::"

"ከዚያ ወስደው ደግሞ ምን ሊያደርጓችሁ ነው?"

"ትምህርት ትማራላችሁ ይሉናል" አልኳት ፈገግ ብዬ::

"ትምህርት ጨርሳችሁ መስሎኝ ስራ የተቀጠራችሁት?"

"ነበር፣ ነገር ግን ደርግ ስላደነቆራችሁ እኛ እንደገና እናድሳችሁ ነው የሚሉን::" አልኳት አሁንም ፈገግ ብዬ:: እንገቷን ደፋ አድርጋ ዝም አለች::

ዕፄ ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ "ለመሆኑ እጮኛህ መጥታ ጠየቀችህ?" ስትል ጠየቀችኝ:: ጥርሶቿ ብልጭ ሲሉ ህይወት ይዘራሉ::

"አልመጣችም::"

"እስቲ ሙች በለኝ::"



"ቅሌታም ነች" አለቻት::

እስከ ስምንት ሰአት ድረስ ከተጫወትን በኋላ መኪና ላሳፍራት ወደ ከተማ አብረን ወጣን:: አውቶቢስ ተራው ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ ትንሽ ወጣ ይላል:: ስንደርስ መኪና የለም:: ተሳፋሪው ግን በሁለት መስመር ተሰልፍዋል:: ከኋላ ሄደን ቆምን::

"ወይ ዛሬ! መኪና ቢገኝም ወረፋ አይደርሰኝም" አለች እንደ መጨነቅ ብላ:: እስከ ዘጠኝ ሰአት ድረስ ተገትረን አንዲት መለስተኛ አውቶቢስ ብቻ መጣች:: ወዲያው የቻለችውን ያህል ጭና ተፈተለከች:: አስር መኪናም ቢመጣ ሰልፈኛውን ጨርሶ የሚያነሳው አይመስልም:: ከኋላ እየመጣ ይጨመራል::

"ዕፄ፣ ይኸ ነገር ነገም የሚደርስሽ አይመስለኝም:: ስለዚህ ወደ ከተማ እንመለስና ሌላ መኪና ብንፈልግ ይሻላል" አልኳት::

"ይሻላል፣ እንደ ባቱ ታክሲም ቢሆን ካገኘሁ ጨምሬ እሳፈራለሁ" አለችና ተመለስን:: መሀል ከተማም ቢሆን መኪና የሚባል ነገር የለም:: እቃ የጫኑ መኪና ጋቢናው ባዶ የሆነ ባየን ቁጥር ሁለታችንም እንገታችንን እናስጋለን:: ሹፌሮቹ ግን ጭቃ እረጭተውብን ይሄዳሉ:: ሰአቱም አስር ሰአት ሆነ:: ዝናቡ ደግሞ ማንጠባጠብ ያዘ:: ሰጠ እየተሯሯጠ ከመንገድ በላይ ካለው ሆቴል ገባ:: እኛም አብረን ገባን:: ዝናቡ የምሩን ለቀቀው::

"አንተን ጨምሬ አስቸገርኩህ" አለችኝ ከተቀመጥን በኋላ፣ ልቧ ተንጠልጥላለች::

"አንቺ እኔን ብለሽ ተቸገርሽ እንጂ እኔን ምን ብለሽ ታስቸግሪኛለሽ! መቼም ካሁን በኋላ ሄደሽ ለስራ አትደርሽ:: ለነገው እንደሆነ አድረሽም ቢሆን ትደርሻለሽ" አልኳት::

"ማደር ይቻላል እንዴ?"

"ለምን አይቻልም? ሆቴል ሞልቷል::"

"ማለቴ አንተ ውጭ ማደር ትችላለህ?"

"ለምን አልችልም? እችላለሁ::"

"እኔማ እንግዲያው ለዛሬ ፈቃድ ወስጃለሁ::"

"ለነገስ እንግዲያው ተለምነሽ ነው::"

"በል እሺ" ስትለኝ ልቤ በደስታ ዳንኪራ መታች:: እሷን አስቀምጬ በጀርባ በር ፈጥኜ በመግባት አልጋ ተከራይቼ ተመለስኩ::

"አገኘህ?" አለችኝ::

"አዎን" አልኳት:: ለምንድን ነው ግን አይኖቻችን የተሰራረቁት? እስካሁን ድረስ ለማደር ስላላሰብን ነው መሰል የፍቅር ስሜት አልተቀሰቀሰብንም ነበር:: ማን እስከ መኝታ ሰአት ይጠብቃል::

"ተነሽ ከመኝታ ክፍላችን እንሂድ፣ ከዚህ ጫጫታ ነው" አልኳትና ተያይዘን ገባን:: ወዲያው በሩን ዘጋነው:: ከዚያ ካልጋው ጫፍ ተቀመጥንና በዝምታ ተያየን:: እንደ መቅለስለስ ስትል እቅፍ አድርጌ ሳም አደረኳት::

"ቆይ ጫማየን ላውልቀው" አለችኝ የልቧ ምት ናር ናር እያለ:: ለቀኳትና እኔም ጫማየን አወለኩት:: ከዚያማ ምን ተይዞ! እንደ

ተጠማጠምን ገነት ገባነው... ስስማትኮ ነው የበለጠ የምረካው:: ከከንፈሮቿ ላይ የማር ጠብታ አለ::

አምሮታችንን ከልተን ስንወጣ ዝናቡም አባርቷል:: ከሆቴሉ ስንገባ እምብዛም ሰው የለ:: ቢራ ብንጠይቅ የለም ተባልን:: ለብርድም ቢሆንን ብለን መሎቲ ኮኛክ አዘዝን::

"እራትስ ምን እንዘዝ" አልኳት::

"እኔ ምንም ነገር አልቀምስም:: ቀን የበላሁትም ጎደል አላለ::"

"ባይሆን ለሁለት አንድ ጥብስ ይምጣልን" አልኩና አዘዝኩ:: ጥብሱ መጣልን:: ደግሞ የበግ ነው:: ያውም ለጋ ጥብስ:: እሱስ ፅጌም ቀንበጥ ነች:: ምን ይሆናል ታዲያ! ቡና ቤት ገብታ እንደ ሸንኮራ አገዳ ልትመጠጥ ነው:: ከንፈሮቿን ማንም አልፎ ሀጅ ሊስማቸው ነው:: በራሴ አስቤ በቅናት ተቃጠልኩ::

"ጉረሽ እስቲ፤ ኧረ ግሩም ጥብስ ነው::"

"አንተ ጉረስ፣ እኔ ጠግቤያለሁ" አለች አንዳንድ ፍሬ ስጋ በማንሳት፤ እኔም ብሆን አጎራረሴ የጥጋብ ነበር:: ነካክተን ተውነው:: ከመጠጡ ይልቅ ደጋግመናል:: ሞቅ ብሎን ነበር ወደ መኝታ ክፍላችን የገባነው::

በጥሩ ሁኔታ ጠላይ ተሸኘኋት:: ጥሩ የፍቅር ስንቅ... ጧት አሳፍሬአት እየተጣደፍኩ ካምፕ ስደርስ አዱኛና በድሉ ከኮሎኔል ዘርጋው ጋር ቆመው ያወራሉ:: ውጭ በማደሬ እንደ ማፈር ብዬ አይቼ እንዳላየኋቸው ሁኘ ወደ መኝታ ክፍል ልገባ ስል:-

"ና ወዲዚህ ጎርፉ" አሉኝ ኮሎኔል:: መለስ አልኩና:-

"እንደምን አደራችሁ ጌታዬ" ብዬ እጆቻቸውን ተራ በተራ ጨበጥኳቸው:: እንዳች ድንጋጤ ወሯቸዋል:: ፈገግታ የሚባል ነገር ከፊታቸው ላይ የለም:: እርግጠኛ ነኝ:: የጠላዩ ጉዞ ይህን ያህል ቅስማቸውን አይሰብረውም:: ሌላ የሆኑት ነገር አለ::

"ደህና አድረሃል፤ የት ጠፍተህ አድረህ ነው?" አሉኝ፣ ኮለኔል ሀዘን በተሞላበት አስተያየት እያዩኝ::

"አንዲት ልጅ ትናንት መጥታብኝ እሷን ለማሳፈር ሄጄ መኪና ሲጠፋ ጊዜ ከተማ አድረን፤ አሁን አሳፍሬያት መምጣቴ ነው::"

"ወይ አገጣጣሚ! አይገርማችሁም?" አሉ ወደነ በድሉ ዞረው::

"እየለፈለፍን ነው ጌታዬ፤ አልሰማን ብሎ ነው" አለ በድሉ ዝግ ባለ አነጋገር::

"ትናንት ጧት ያ መቶ አለቃ ሀይለሚካኤል ምንድን ነበር ይልህ የነበረው?" ሲል አዱኛ ጠየቀኝ::

"የት ለመሄድ እንዳሰበ አልነገረኝም እንጅ 'መሄዴ ነው ከንግዲህ አንገናኝም' ብሎኛል:: እንደ ተረዳሁት ከሆነ መጥፋቱ መሰለኝ::"

"መቼም ከኛ የምትደብቀው ምስጢር አይኖርም ጎርፉ:: የነገረህ ነገር ካለ ንገረንና እንመካከርበት:: መከንኑ ትናንት ካንተ እንደተለየ ከዚህ ታች ራሱን በገመድ ሰቅሎ ተገኝቷል" ሲሉኝ:-

"ኧረ!!" አልኩ በድንጋጤ ደርቄ:: በሁለት እጆቼ እራሴን ያዝኩኝ::



"እና የሆነ ወረቀት ፅፎ ከኪሱ ውስጥ ተገኝቷል አሉ:: ያንተንም ስም ጠቅሷል አሉ:: ለምን እንደፃፈህ የታወቀ ነገር የለም:: ኢህአዲጎቹ ከትናንት ጀምረው ይፈልጉሃል" ሲሉኝ ድንጋጤ ወረረኝ::

"ለምንድን ነው የሚፈልጉኝ? እኔን ሰቀለው ብለው ነው?" አልኩ:: ከሰውየው ሞት ድንጋጤ ወደ ራሴ ጭንቀት ከመቅፅበት ተሸጋገርኩ::

"ለምን እንደፈለጉህ የታወቀ ነገር የለም:: ደግሞ ያጋጥሚው ነገር እንጅ:: እሱ እራሱን ሲገድል ያንተ ውጭ ማደር" አሉ በመጨነቅ::

"መክረነዋል ጌታዬ! በገዛጁ ነው መዘዝ ያመጣው፤ አሁንም ጊዜ ሳያጠፋ ቢጠፋ ይሻላል! መቼም ያላንዳች ምክንያት የሱን ስም አልጠቀሰው:: አንድ ነገር መኖር አለበት:: እነሱ ደግሞ ከያዙ አይለቁም:: እውነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ ለምን ይሰቃያል" ሲል አዱኛ የራሱን ሀሳብ ሰነዘረ::

"መጥፋቱ እንኳን ጥሩ አይሆንም:: አድራጊ መምሰል ነው::" ሲሉ ኮለኔል ሀሳቡን ተቃወሙ:: በዚህ ውይይት ላይ እንዳለን:-

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው፤ የምድር ጦር ማስተናገጃ ባልደረባ የነበሩ፣ ከኢህአዲግ ፅፈት ቤት ቢሮ ቁጥር 3 ድረስ በመምጣት ሪፖርት እንዲያደርጉ" በድምፅ ማጉሊያ ነበር የተጠራሁት:: እራታችንም በሀይል ተነፈስን:: ፊቴ ኮስተር ይበል እንጅ ድንጋጤ ወሮኛል:: ከምጠላው ነገር ቢኖር በገዳይነት መወንጀል ነው::

"አይዞህ አትደንግጥ፤ ሀቁን ንገራቸው" አሉኝ ኮለኔል:: ፈንጠር ፈንጠር እያልኩ ስራመድ እነሱ ቀስ ብለው ከኋላዬ ተከተሉኝ::

የኢህአዲግ ፅ/ቤት እሩቅ አይደለም:: ከዚያው ከግቢያችን ውስጥ ነው:: ደቂቃ አልፈጀብኝም:: ቢሮ ቁጥር ሶስትን በሩን እንኳኩቼ ስገባ ፀጉሩን ያንጨፈረረ፣ ፊቱ ገጠጥ ያለ ወጣት ኢህአዲግ ቁጭ ብሏል:: የሚፅፈውም፣ የሚያነበውም ፋይል ነገር ከፊቱ የለም:: የፊጥኝ አስረው ያስቀመጡት ይመስላል::

"ምን ነበር" አለኝ ኮስተር ብሎ::

"መቶ አለቃ ጎርፉ እንደሻው እባላለሁ:: አሁን ተጠርቼ ነው" አልኩት እኔም ኮስተር ብዬ::

"ምን አሁን ብቻ፤ ኧረ ከትናንት ጀምረን ነው የምንፈልግዎት:: እስቲ ይቀመጡ" በማለት ከፊት ለፊቱ እንድቀመጥ ወንበር አሳየኝ:: ፈጠን ብዬ ተቀመጥኩ:: ከዚያም ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ አንዲት የተጣጠፈች ወረቀት አወጣና:-

"እስቲ ይችን ወረቀት ያንብቧት" አለና ሰጠኝ:: ተቀብዬ ገለጥ በማድረግ ማንበብ ጀመርኩኝ:: ሲጋራ አቀጣጠለና እያጨሰ አጮልቆ ያየኝ ነበር::

"የወታደር ልጅ ነኝ:: አባቴ እድሜውን ሙሉ ሲንከራተት ኖሮ ጡረታ ወጥቶ እንኳን ማረፊያ አጥቶ በዳግም ዘማችነት ዘምቶ የኤርትራ መሬት በልቶት ቀርቷል:: እኔም በግሩ ተተክቼ ያቅሜን ያህል እናት አገሬን አገልግያለሁ:: በውትድርና አለም 23 አመት አገልግያለሁ::

"ያምስት ልጆች አባትና ባለ ትዳር ነኝ:: በምስራቅ፣ በሰሜን ከመንከራተት በስተቀር ያካበትኩት ሀብት የለም:: ዛሬ ታዲያ ልጆቼን

ምን ላብላቸው? ፊፅሞ የሚቀምሱት ነገር የለም፡፡ እርሃብ ጊዜ አይሰጥም፡፡ በርሃብ ማለቃቸው ነው፡፡ ቁሜ እየሄድኩ ደግሞ ልጆቼ በርሃብ ሲያልቁ ማየት ልሸከመው የማልችለው ስቃይ ነው፡፡ ይህን በማስብበት ወቅት ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ውጭ ሆነ፡፡ የነበረኝ ተስፋ ሁሉ ተሟጠጠ፡፡ ስለዚህ እራሴን ከመግደል ሌላ አማራጭ አላገኘሁም፡፡ መገላገል ነው ከማንኛውም ነገር...

"ውድ ልጆቼ! እራሴን የሰዋሁት ለናንተ ፍቅር ስል እንጅ ጠልቻችሁ እናንተን ለመገላገል ስል አይደለም፡፡ ቁሜ ካልጠቀምኳችሁ እኔ ሙቼ 'የሙት ልጆች' ተብላችሁ ብትረዱ ይሻላችኋል፡፡ የናንተ ባላደራም የኢትዮጵያ ህዝብ ነው..." በጉያው ሸጉጦ! የጎረሰውን አጉርሶ ያሳደጋችሁ፡፡

"ውድ ባለቤቴ! መሪር ሀዘን እንዳይገባሽ፡፡ በተቻለሽ አቅም ልጆችሽን ለማሳደግ ሞክሪ፡፡ እኔ ተዋርዶ መኖርን ህሊናየ ሊቀበልልኝ አልቻለም፡፡ ጥርጣሬ እንዳይገባሽ፡፡ እራሴን በራሴ ነው የገደልኩት፡፡ ለማንኛውም ነፍሴ ይቅርታ ትጠይቅሻለች! ይቅርታ አድርጊላት...

"ውድ ወዳጀ! የጥቂት ቀን ጓደኛዬና አፅናኜ ሙቶ አለቃ ጎርፉ! አንተንም ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቅሀለሁ፡፡ የምጠፋ መስሎህ ሀሳቤን ለማስለወጥ ጥረት አድርገህ ነበር፡፡ ለመሆኑ የምጠፋው አልሰረኩ! አልገደልኩ! አልቀጠፍኩ! ለምንድን ነው? ያለ ስራየ የኢህአዲግ መረጃ ነው ስለተባልኩ? እስቲ ያለ ስሜ ስም የሰጡኝን ይስፋቸው፡፡ እኔስ ለጭራሹ ተገላግያለሁ፡፡ ብዙ ለመፃፍ ያሰብኩት ነገር ነበር! ግን ጠፋብኝ፡፡ አእምሮየን ጭንቅ ጭንቅ አለኝ፡፡ ለማንኛውም በኔ መሞት አትፀፀት፡፡ ለኔ እፎይታ ነው፡፡ አንተም ቢሆን ተዋርዶ መኖርን በፀጋ አትቀበል፡፡ ሆዳም ሰው ብቻ ነው በሆዱ እየተገዛ ውርደትን ክብሩ አድርጎ የሚኖረው፡፡ በል ለጭራሹ ቻው! ሀይለሚካኤል ግዛው፡፡"

እንብቤ ስጨርስ ቀና ብዬ በረጅሙ ተነፈስኩና "የሚያሳዝን አሟሟት ነው" አልኩኝ፡፡

"ለመሆኑ ከስዎ ጋር ግንኙነታችሁ እስከምን ድረስ ነበር?" አለኝ ሲጋራውን እያቦነነ፡፡

"ያው አብረን ባንድ ክፍል ውስጥ በመተኛት ነው፡፡ የተዋወቅነውም ከዚሁ ነው፡፡"

"ለህይወታቸው መጥፋት ምክንያት የሆነው የኢህአዲግ መረጃ ናቸው ተብለው መጠርጠራቸው ይመስልዎታል?"

"በዚህ እንኳን እራሱን የሚያጠፋ አይመስለኝም፡፡ በርግጥ በነገሩ በጣም አዝኖበታል፡፡ እንደ ገባኝ ከሆነ ግን ለመሞቱ ምክንያት የሆኑት ልጆቹ ናቸው፡፡ ጧት ማታ 'ልጆቼ የሚቀምሱት የለም' እያለ ያዝን ነበር፡፡"

"ከዚህ ውጭ የሚያውቁት ነገር የለም?"

"በጭራሽ አላውቅም"

"እሽ፤ ስፈልግዎት ይመጣሉ" ብሎ አሰናበተኝ፡፡ ከቢሮ ስወጣ እነኮለኔል በትካዜ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው፡፡

"ምን አሉህ?" ሲሉ ኮለኔል ቀድመው ጠየቁኝ፡፡



"የኔን ስም ከፃፈው ወረቀት ላይ ጠቅሶ ስለነበረ የማውቀው ነገር እንዳለ ብለው ነው፡፡"

"ለመሆኑ ምን ብሎ ነው ያንተን ስም የጠቀሰው?"

"የምጠፋ መስሎህ ሀሳቤን ለማስለወጥ ሞክረህ ነበር፡፡ እራሴን በመግደሌ እንዳይፀፅትህ፡፡ 'ይቅርታ አድርግልኝ' ነው የሚለው፡፡"

"በመጨረሻ ታዲያ በምን ተለያያችሁ?"

"ስንፈልግህ ትመጣለህ" አሉኝ፡፡

"ጣጣው ገናነው አትለኝም ታዲያ!"

"ሟቹ ያሳዝናል እንጅ እነሱስ ዳግመኛም አይጠይቁኝ፡፡ ይህን ያህልም ትኩረት አልሰጡት፡፡ የሚጠይቀኝን እንኳን በማስታወሻ ለመያዝ አልሞከረም፡፡"

"ትኩረትማ ምኑን ትኩረት ይሰጡታል፡፡ ጥይት ከማባከን እራሳችንን በገመድ እየሸመቀቅን ከተገላገልናቸው ጥሩ ነው እንጅ" አሉ ተቆጭተው፡፡

"ሰምተዋል ጌታዬ! ሁለተኛ ክፍለ ጦርም አንድ ሻለቃ ማላታይን ጠጥቶ ሙቷል" አለ አዱኛ፡፡

"ሰምቻለሁ፡፡ አንድ ሻምበልም ሽጉጥ ጠጥቶ ሞቷል፡፡ ምን አደከማችሁ! በዚህ ሳምንት ብቻ አምስት መኮንኖች መሞታቸው ነው፡፡ ጠላይ ስንሄድ ደግሞ ወባ ይጨርሰናል" አሉ ኮለኔል በብርቱ አዝነው፡፡

የጠላይ ጉዞ ደግሞ ተሰነቀረብን፡፡

# 19

ገነት ገብተን ነበር ለሶስት ቀን እድሳት፣
ጠላይ ተመረጠ ታርቆ ለመውጣት፡፡

ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ጀምረው ወደ ጦር ትምህርት ቤቱ ሲገቡ የዋሉት አውቶቢሶች ግቢውን ሞልተውታል፡፡ ከሌሊቱ አስር ሰአት ጀምረው ነበር አንደኛ ክፍለ ጦርን ማጓጓዝ የጀመሩት፡፡ ለጊዜው «ጉዞው የማይመለከታችሁ ወዲህ ወዲያ እንዳትንቀሳቀሱ» ስለተባልን በየበራችን ላይ ቁመን እንመለከት ነበር፡፡ ብርዱም አጥንት ይቆረጥማል፡፡ የመኪናው ጩኸት፣ የመኮንኖቹ ጫጫታ ምስቅልቅል ያለ ትርኢት ነበር፡፡ ልክ ከንጋቱ አንድ ሰአት ሲሆን የመጨረሻው አውቶቢስ ከግቢው ለቀቀ፡፡

ከጉዞ የተረፍነው መኮንኖች በሀሳብ ክልውስውስ አልን፡፡ ኮለኔል ዘርጋው ቀድመውን ሄደዋል፡፡ እኛ ሶስታችን ግን ገና ተራችንን እንጠብቃለን፡፡ ስለጠላይ የሚወራው ወሬ መቼም አስጨንቆኛል፡፡ እንዲያው የበሽታ አይነት ሁሉ መጠራቀሚያ ነው አሉ፡፡ እኔ ጠላይን አላውቀውም፤ ቢጨንቀኝ፡-

ኦጋዴን ወርጀ በጥይት ሳልሞት፤
እንዴት ጠላይ ሄጀ በትንኝ ልሙት አልኩኝ::

በዚሁ እለት አራት ሰአት ተኩል ሲሆን ከጉዞ የቀረነው እንድንሰበሰብ ተደረገና የሆለታ ከተማ የጤና ባለሙያዎች ናቸው ተብለው ባንድ ዶክተር መሪነት መጥተው ንግግር አደረጉልን::

"... ምክርም፣ ማስጠንቀቂያም፣ ማሳሰቢያም ነው:: የጤና ጉዳይ በመሆኑ ችላ ልንለው አንችልም:: በርግጥ ከሞራል አንፃር ሲታይ ሊሰማችሁ ይችላል:: እኛ ደግሞ ከሀላፊነት አንፃር ስናየው ሌላ ምርጫ የለንም:: እንደ እውነቱ ከሆነ በናንተ አፍረናል:: ጨብጥ፣ ቂጥኝ ... የመሳሰሉትን በሽታዎች በመድሃኒት እንኳን ማዳን አልቻልንም:: የናንተ ከዚህ መምጣት እናንተ የፈጠራችሁት ችግር ባይሆንም፤ ለሆለታ ህዝብ ግን ጠንቅ ነው የሆናችሁበት:: በርግጥ ቀላሉ መንገድ ለህዝቡ ነግሮ እናንተን እንዳያስጠጋ ማድረግ ነበር..." በማለት እየተናገረ እያለ:-

"ብስብስ! አንተን ብሎ ዶክተር!" ብለነው አውከተን ጥለነው ሄድን::

"እውነት ይኸ ዶክተር ነው? በጭራሽ አይደለም! አንዱን ወያኔ ጋዋን አልብሰው አቅርበውት ነው!" አለ አዱኛ በሽቆት::

"ነገሩስ ዶክተር ነው:: መኮንኖቹ ውሽማውን ስለቀሙት በበቀል ነው የሰደበን::" አለ በድሉ::

"እናንተው ጊዜው አዘንበሎብናል" አሉ አንድ ጠና ያሉ ሻምበል:: ያም ሆነ ይህ ለቀቅንለት:: በሶስት ቀናት ውስጥ ሁለቱም ክፍለ ጦሮች ተጠናቀን ጣላይ ገባን:: ጓድ ዶክተርም ሆለታን አንድ ላንድ ይያዛት፤ ይስፋው:: ሰው ያለሰው ግን ባዶ መሆኑን የኋላ ኋላ ይገባው ይሆናል::

# ምእራፍ ስምንት

በዘመነ ደርጉ ናውጌ ናውጌ፣
በኢህአዲግ ጊዜ ከጣላይ ከረምኩኝ በማእረግ ተይጌ::

## 20

ጣላይ የገባነው ማታ ነበር:: እንደ እድል የቀናው አልጋ አገኘ:: ያልቀናን ደግሞ ቅጠል ዘንጣጥፈን፣ ሳር በጃችን በጫጭቀን እንደ ነገሩ ጎዝጉዘን ከዚያ ላይ ተጋድመን አደርን:: ታዲያማ በማግስቱ ጧት ያልጋው ርብራብ ስለተዘረፈ ጣውላ ቢጤ ለመፈላለግ እንደ ዋዛ ወጣ ብዬ ቀረሁ:: ኧረ ጉድ ነው የሆንኩት! ያደርኩበት ክፍል ጠፍቶኝ ብወጣ ብወርድ ላገኘው አልቻልኩም:: ካንዱ ክፍል ወጥቼ ከሌላው ክፍል ስገባ ከዚያኛው ክፍል ያየሁትን አያለሁ:: ጣራው፣ ግድግዳው፣ በረንዳው አንድ አይነት ነው:: ልክ እንደ መንታ ልጆች ለመለየት ያስቸግራል::



ካንዱ ብሎክ ተነስቼ ከሌላው ስሄድም ያው ነው:: ካንዱ የሻለቃ ካምፕ ተነስቼ ወደ ሌላው ሻለቃ ካምፕ ብሄድም ካምፑ አንድ ነው:: ብርጌድ ከብርጌድም መለየት አይቻልም:: ሳር ቅጠሉ፣ ዛፉ፣ ሁሉም አንድ አይነት ነው:: እንዲሁ ስንከራተት፣ በባዶ አፌ ከዘጠኝ ሰአት ደረስኩኝ:: የሚያውቁኝ መኮንኖች:-

"ምን ጠፋህ?" ሲሉኝ:-

"ምንም" አላቸዋለሁ:: ምንላድርግ? ያደርኩበት ክፍል ጠፍቶኝ ለማለት አፈርኩኝ:: እንዴት እንደ ህፃን ልጅ ያደርኩበት ክፍል ጠፋኝ እንደ ወጣሁ እቀራለሁ? ቅሌት ነው፤በኋላማ ደከመኝ:: አረማመዴ እጥፍ እጥፍ ሆነ:: አፌ ደርቋል:: ውሃ ጥምም ይዞኛል፤ እርሃብ እየበገበገኝ ነው:: ማታ የረባ አልበላንም ነበር:: ዳቦቆሎ መሳይ ነገር ቆረጣጥመን ያደርነው:: የማደርገው ባጣ ከመንገዱ ዳር ካለው ትልቅ ዛፍ ስር ሄጄ ግንዱን ደገፍ ብዬ ቆምኩ:: ምንላድርግ፤ ደከመኝ:: መኮንኖቹ ወዲያና ወዲህ በጥንድ በጥንድ ሆነው ይንጠራወራሉ:: መንገዱ ዙሪያ ጥምጥም ነው:: ፍሬ አላገኘሁበትም እንጅ አስር ጊዜ ይሆናል የዞርኩት::

ከዛፉ ስር እናቱ ገበያ እንደ ሄደችበት ህፃን ፍዝዝ ብዬ እንደ ቆምኩ ከወደ ፊት ለፊቴ ኮለኔል ዘርጋው ቸኮል ቸኮል እያሉ በመሪድ ሲመጡ አየኋቸው:: አቤት ደስታዬ! የተጫጫነኝ ነገር ሁሉ ለቀቀ አለኝ:: ፈገግ ብዬ ከዛፉ ስር ስወጣ እሳቸውም አዩኝ::

"ጎርፋ!" አሉኝ ከፊቴ ላይ ምን እንዳዩ እንጃ ሰላምታ እየቃጣቸው:: ተቃቅፈን ትከሻ ለትከሻ ተሳሳምን::

"እንኳን ደህና መጣችሁ ልላችሁ ብመጣ አንተ የለህ፡ እነበድሉኮ ተጨንቀዋል:: ያደርክበት ክፍል ጠፋህ እንዴ?" አሉኝ በጥርጣሬ አስተያየት እያዩኝ:: ደግሞ ለመሳቅ አቆብቁበዋል::

"ለስምስ አልደብቅዎትም ጌታዬ:: ብወጣ ብገባ ያደርኩበት ክፍል አልጠፋብኝም መሰለዎት" ስላቸው በሳቅ ፈንድተው ሊሞቱ፡

"ገና ሳይህኮ ነው ግራ እንደ ተጋባህ የተረዳሁት" አሉ ስቆ ያወጡትን እንባ በመሀረባቸው እየጠረጉ::

"እንዲህ አይነት ቅሌት ገጥሞኝ አያውቅም:: ከኦጋዴን በለጠ አደናጋሪ መሬት የለም:: ለዚህ ግን ተወዳዳሪ የለውም:: አሁንም አዲስ አበባ በየት አቅጣጫ እንደ ሆን አላወኩትም" ስላቸው እንደ ገና በፍር እስከሚሉ ሳቁና:-

"ኧረ ባክህ በሳቅ አትግደለኝ" አሉኝ አሁንም አይኖቻቸውን በመሃረብ እየጠረጉ:: "በል እንሂድ ላድርስህ" በማለት መንገድ ጀመርን::

"መቼስ አይጣል ነው ጌታዬ፤ እኔ ለተጎዳሁ የማዝነው ለናንተ መሳቂያ መሆኔ ነው::"

"አንተኮ ብቻ አይደለህም ጎርፉ:: እኛ የመጣን እለት እንዲህ ስንቶቹ ተዋርደዋል መሰለህ:: አንድ ሻምበል ለሽንት ወጥቶ የመለሻው ጠፍቶት ከዚያው ሽንት ቤት ተገትሮ አድሮ ጧት ተገኝቷል:: አንድ መቶ አለቃ ደግሞ እንደ ዋዛ ወጥቶ መመለሻው ጠፍቶት ሲዳክር አምሽቶ፤ አሳድሩኝ እንዳይል ደግሞ ማፈር፤ እንደ ጦጣ ከዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ አድሮ ጧት ሳይወርድ ተገኝቷል:: እስጠጉን እያሉ

በየክፍሉ የሚያድሩትማ ብዙ ናቸው:: ሰሞኑን ስንስቅ የነበረው በዚሁ ነው:: ጠላይ ለንግዳ ደራሽ አስቸጋሪ ነው:: በጥንቃቄ ልዩ ምልክት ካልያዝክ በስተቀር እንደ ሰባራ አህያ ስትዟዟር መዋልህ ነው:: ቀደም ሲል ብራዊ ወታደሮች ከዳን ይሉና ሲዳክሩ ውለው ካምፑን ሳይለቁ ይያዙ ነር" በማለት ተረኩልኝ::

እነ አዱኛ ገና ሲያዩኝ ሳቃቸውን ለቀቁት:: ኮለኔልም እነሱን ተከትለው ይስቁ ጀመር::

"ምን ያስቃችኋል?" አልኩ ቆጣ ብዬ:: ማንም አላናገረኝም:: እየተባበሉ እንባ እስከሚወጣቸው ድረስ ሳቁ:: እኔ የኮዳ ውሃ እነሳሁና በባሁዶ አንደቀደኩት::

"ጌታዬ የት አገኙት?" አላቸው በድሉ ጠጋብሎ::

"እኔን ሊጠይቅ ሄዶ ኖሮ እኔን ሲያጣ ጊዜ ከዚያው ቁጭ ብሎ ነበት::"

"እስቲ ሙት ይበሉኝ" ሲላቸው:-

"ለምን ትሞታለህ?" ሲሉት እንደ ገና በሳቅ ይንፈቀፈቅ ጀመር::

ንድድ አልኩኝ፤ አዱኛ ደግሞ ወደኔ ጠጋ ብሎ:-

"የኔ ጎርፍ፤ ጎርፉ በለህ" አለኝ::

"እንተን ይጠረግህ! አሁን እርቦኛል" አልኩት::

"ሽረ ባካችሁ በሶ መሳይ በጥብጡና ስጡት" ሲሉ ኮለኔል በድሉ ቀበል አሉ:-

"ምነው ጌታዬ! በባህላችን እንግዳ ክቡር ነው፤ እስዎን ሊጠይቅ ሄደ እዴት አላስተናገዱትም?"

"ባለቤቱ ወደ ገበያ ሄዳ ከባዶ ቤት መጥቶ ነው" ሲሉ ቀለዱ::

ወዲያ አዱኛ በሶ በጣሳ ሲበጠብጥልኝ በድሉ ደግሞ ዳቦቆሎ ዘግኖ ሰጠኝ ባቄላ ክምር እንደ ገባ መንጋ ፈየል ይህን የደረቀ ዳቦቆሎ ቁርጥምም አደርግ ጀመር:: በሶውንም ሰጠኝ:: ተቀብዬ ባንድ ትንፋሽ ለጋሁት ለመም እያለ ነበር የገባው::

ልድገምህ?" አለኝ::

እዎን" አልኩት:: ሀይለኛ እርሃብ ተለቆብኛል::

ለኢህአዲግኮ ልናመለክት ነበር ጌታዬ" አለ በድሉ::

ምን ብላችሁ" አሉት::

ሬዲዮ እንዲያስፈልግልን ነዋ::"

ባካችሁ ተውት አሁን:: ከድካሙ ወዲህ የፈራው የናንተን ሽሙጥና ቀልድ ነው::"

ለኔል ሲጫወቱ ቆይተው ሄዱ:: እኔም ደክሞኝ ስለነበረ ተጠቅልዬ ተኛሁ:: ይልቅየ ቆንጆ አልጋ ሰርተው ጠበቁኝ:: እግዜር ይስጣቸው:



# 21

## «ጦሩ ላይዋጋ ይሰለጥናል!»

ጦላይ በገባን ማግስት ያገኘነው አባባል ነው:: በድርግ ጊዜ ምን ያልተባለ ነገር አለ? ጦላይ ከገባን አንድ ሳምንታችንን ይዘናል:: በመጠኑም ቢሆን ተላምደነዋል:: እባቡ፣ ዘንዶው፣ ጊንጩ፣ የወባው ትንኝ እየተባለ የተወራው ሁሉ ከመጠን በላይ የተጋነነ ነው:: እስካሁን ድረስ በእባብ የተነደፈም ሆነ በዘንዶ የተዋጠ የለም:: በርግጥ ወባ እንዳለ ይነገራል:: ቢሆንም ጊዜው ክረምት ስለሆነ ይህን ያህል የሚያሰጋ አይደለም:: ጥናም ቢል ከመስከረም በኋላ ነው:: ለጊዜውም ዲዲቲ ተረጭቶልናል::

ባለፈው ጦላይ በገባን ማግስት ያደርኩበት ክፍል ስለጠፋብኝ በሽቁ ስለጦላይ ያልኩት ነገር አልነበረም:: ዛሬ ግን በሚገባ አጢኛታለሁ::

ከሆለታ ተነስተን ምእራብ አዲስ አበባን እያቆራረጥን ከጅማው መንገድ በመግባት ጉዟችንን በረጋ ሁኔታ ቀጠልን:: በመንገድ የሚያየን ህዝብ ሁሉ በሀዘን ከንፈሩን ይመጥልን ነበር::

ምሳችንን ወሊሶ በልተን ጉዞአችንን በመቀጠል ከወልቂጤ አስር ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ተጓዝን ዋናውን ጎዳና ለቀን ወደ ቀኝ በመታጠፍ የምእራብን አቅጣጫ ያዝን:: የጠጠር መንገድ ነው:: አንድ ትልቅ ወንዝ አለ፣ ከዚያ እስከምንደርስ ድረስ የመንገዱን ዳር ተከትለው አልፈው፣ አልፈው አዳዲስ የሰፈራ መንደሮች ተቆርቁረዋል:: ከወንዙ ወዲያ ግን ግቤ እስከምንደርስ ድረስ ምንም አይነት የሰው ዘር አላየንም:: ጭልጥ ያለ በረሃ ነው:: ሆኖም ግን የክረምት ወቅት በመሆኑ በልምላሜ ተውጦ አይንን ይማርካል:: ዛፎች ቅጠል ለብሰዋል፤ መሬቱ በሳር ተሸፍኗል:: እርቃኑን የሆነ ነገር የለም:: እኛ ነን ከንግዲህ ከሰው ዘር እርቀን እርቃናችንን የቀረን ...

መንገዱ በመጠኑ ስላች እየሰራ፣ ቀናታ እየጨመረ ይሄድና ግቤ መዳረሻ ላይ ያዘቀዝቃል:: የምእራቧ ፀሀይ ፊትለፊታችን ትመታን ነበር:: ሹፌሮች የፀሀይ መከላከያ ባለቀለም መስተዋታቸውን ጋርደዋል:: ከፊትለፊታችን ከግቤ ወንዝ በርቀት አንድ ትልቅ ጋራ ተገትሮ ይታያል:: ፀሀይዋ ከዚያ ላይ ቁማ እንደ ጦር የምትወጋን ትመስላለች::

ግቤ ወንዝ ስንደርስ አፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ጎሽቷል:: መሬቱ ረባዳ ስለሆነ እረጋ ብሎ ነው የሚጥመለመለው:: ሳር ቅጠሉን ያግበሰብሰዋል:: እኛም ተግበስብሰን ነው የመጣነው...

ወንዙን ተሻግረን እንደ ገና ወደ ምስራቅ ደቡብ ታጥፈን አንድ ሀያ ኪሎ ሜትር ያህል እንደሄድን ከታ የተባለች ትንሽ ከተማ አለች:: ከተማ ስለሚሏት ከተማ አልኳት እንጅ መንደር ናት:: ከወሎና ከደቡብ ሸዋ መጥተው የሰፈሩ ናቸው:: ወደፊት እንጃ እንጅ ዛሬስ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት ሳያራርቃቸው በፍቅር ተሳስበው ነው የሚኖሩት::

ከከታ በኋላ መንገዱ ለጥ ያለ አግድመት ነው:: አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ሄድን ደግሞ ዋዩ የምትባል ከተማ እናገኛለን:: ዋዩ በመጠኑም ቢሆን የከተማነት ባህሪ አላት:: አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣

አንድ ሆቴል፣ በርካታ ትንንሽ ሱቆች፣ የሰፈር መጠጥ ቤቶች አሏት። ሳምንታዊ ትልቅ ገበያም አላት፤ ቅዳሜ ቀን ነው የሚውለው።

ከዋዩ በኋላ አንድ አግድመት ተፈትልከን ካንድ ወንዝ ውስጥ እንደርሳለን። መጠነኛ ድልድይ አለው። እሱን ከተሻገርን በኋላ የጦላይ ማሰልጠኛ ማእከል ክልል ነው። ከዋናው በር መዳረሻ በስሚንቶ የተገነባ ጠፍጣፋ ግንብ አለ። ከላዩ ላይ የብረት ቆብ የደፋ ባንድጁ ክላሽ ጠመንጃ፣ በሌላ እጁ ደግሞ ጡርንባ ይዞ የሚነፋ ስእል ተስሎበታል። የክተት ጥሪ መሆኑ ነው። ስናስከትት ኖረን በመጨረሻ እኛው ከተትን። ፅዋ አይደል!

ጡሩንባ ነፊውን እንዳለፍን መንገዱ ለሁለት ይከፈላል። መሀል ለመሀል አትክልቶችና አበባዎች አሸብርቀውበታል። የቸርችል ጎዳናም እንደዚህ አያምር። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ያለውን ውስጣውስጡንና የመንገዶቹን ቅያስ ከናዝሬትና ከድሬዳዋ ወይንም ከባህርዳር ጋር ማነፃፀር ነው። አበባው ተንተርክኮ ሲያዩት መንፈስን ያድሳል።

የመግቢያውን በር አስከፍተን ገባን። በስተግራ በኩል የማሰልጠኛ ማእከሉ ዋና መስሪያ ቤት ይገኛል። ባላንድ ፎቅ ሲሆን ዘመናዊ ህንፃ ነው። ካናቱ ላይ እንደ ተለመደው «ካብዮታዊ መሪያችን ከጓድ መንግስቱ ሀይለማርያም ብልህ አመራር ጋር ወደ ፊት!» የሚል በቀይ ቀለም ተፅፎ በሩቁ ይነበባል። መርተው መርተው ዝምባብዌ ደርሰዋል። እኛም እሳቸውን በመከተል ከጃን ሜዳ ተነስተን በሆለታ አድርገን ይኸው ጦላይ ደርሰናል። ካሁን በኋላስ ንቅንቅም አንላት! «ወደ ፊት!» እያልን ወደ ኋላ ተፈንግለናል። አጅሬ ግን እውነትም ብልህ! «ወደፊት!» እንዳሏት ተፈተለኩ፣ እረ ከሳቸው ያላነሱ ብልሆችም አሉ! ጦሩን ትጥቅ አስፈትተው ጣሊያን ኤምባሲ የተሸጎጡ። ይብላኝላቸው፣ ፓስታ ያልቅና ውጡ የተባሉ እንደሆነ እንጂ ዛሬስ ታድለዋል። ቅንቡርስ ቅንቡርሱ ባለስልጣን ነው እንደኛ ተጋፎ ሰንዳፋ የገባው። ይኸ እንግዲህ «በብልሁ መሪያችን» ጀርባ ታዝሎ የኖረ ነው። የራሱ ጭንቅላት የሌለው...

ከዋናው መስሪያ ቤት ትንሽ ከፍ ብለን ወደ ቀኝ ታጥፈን ትንሽ አለፍ እንዳልን የባህል ማእከል አዳራሽን እናገኛለን። ይህ አዳራሽ በጣም ዘመናዊ ነው። አዲስ አበባ ካሉት ቲያትር ቤቶች ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ካዳራሹ አለፍ እንዳልን ያንደኛ ክፍለ ጦርን ካምፕ እናገኛለን። እንግዲህ የሰሜኑን አቅጣጫ አንደኛ ክፍለ ጦር ሲይዝ የደቡብን ደግሞ ሁለተኛ ክፍለ ጦር ይይዛል። አወቃቀራችንም በክፍለ ጦር፣ በብርጌድ፣ በሻለቃ፣ በሻምበል ነው። በዚህ መሰረትም ሁለት ክፍለ ጦሮች፣ ስድስት ብርጌዶች፣ አስራ ስምንት ሻለቆች፣ ሰባ ሁለት ሻምበሎች አሉ። እያንዳንዱ ሻለቃ የራሱ የሆነ ምግብ ቤት፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አለው። መኖር የምንችለው ግን አንድ ሻምበል ጦር ባንድ ብሎክ ነው። በዚህ ድልድል መሰረት እኔና በድሉ፣ አዱኛ ሆነን የምንኖረው 1222 ነው። ይህ ማለትም አንደኛ ክፍለጦር፣ ሁለተኛ ብርጌድ፣ ሁለተኛ ሻለቃ፣ ሁለተኛ ሻምበል ማለት ነው።

በሁለተኛ ክፍለ ጦር ማዶ ያይሮፕላን ማረፊያ አለ። ከዚህ ነው እንግዲህ ባንቴናቭ የከተተው ወጣት ሁሉ ተከቶ ወደ ተለያዩ የጦር ግንባሮች የሚወሰደው።



ባጠቃላይ ጦላይ የመንገዶቿ ቅያስ፣ የዛፎቹ አተካከል፣ ያበባዎቹ ፍካት የበረሃ ገነት አሰኝቷታል። በዚህ ላይ የወፎቹ ዜማ፣ የጦጣዎቹ ሁካታ ልዩ ደስታን ይሰጣሉ። ዛፎቹ ቀንዘልና ቀንዘላቸውን አገጣጥመው የቆርቆሮውን ቤት ውጠውታል። ባይሮፕላን እንኳን ሆኖ ቁልቁል ማእከሉን ማየት አይቻልም። ሌላው ቀርቶ ካንደኛ ክፍለ ጦር ሆኖ ሁለተኛ ክፍለ ጦርን ማየት አይቻልም። ወዲያና ወዲህ ባልን ቁጥር ፀሀይ አይመታንም፣ ጥላ ለጥላ ነው መንገዳችን።

ጦላይን በርቀት ለሚመለከታት ደግሞ የበለጠ ትማርካለች። ለጥ ካለና በደን ከተሸፈነ ልምጥ ዋልካ ላይ ነው የተመሰረተችው። በስተምእራብ በኩል እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ጋራዎች የተፈጥሮ መከታ ሆነዋታል። ከጋራዎቹ በስተጀርባ ያለውን አገር ማየት አይቻልም። ከነዚሁ ጋራዎች የሚነሱ ሁለት ወንዞች ማእከሉን አማክለው ግቤ ወንዝ ሄደው ይጨመራሉ። በወንዞቹ ውስጥ ለውስጥ ዘንዶ አለ እያሉ በፊት ከዚያ አሰልጣኝ የነበሩ መኮንኖች ያስፈራሩናል። እኔ ግን ያለ አይመስለኝም። ጦጣዎች ናቸው ሲያሽካኩበት የሚውሉት። ከካምፑ ድረስ በመምጣት አሹፈውብን ይሮጣሉ።

የጦላይ አየርም ተስማምቶናል። እንደ ጊዜው አልጠመመብንም። እስካሁን የሞተም፣ የታመመም የለም። ይልቅ እዳ የገባነው ሁለት ድርጅቶች ተቋቁመው ጠቅላላ መኮንኑን ማመስ በመጀመራቸው ነው።

1ኛው. ሸብር ፈጣሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሸፈዲድ)

2ኛው ሞራል ገንቢ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሞገዲድ) ይባላሉ። ሁለቱም የተለያዩ አላማዎች አሏቸው። ሸፈዲድ መኮንኖቹና ኢህአዲጎቹ እንዳይጣጣሙ ወይንም እንዲጋጩ ይጥራል፤ አባላቶቹ ገንዘብ ቤቶች፣ ደመወዝ ከፋዮች፣ ካድሬዎች፣ የደህንነት አባላት፣ አዛዦች ናቸው ይባላል። ሞገዲድ ደግሞ የሌለ ተስፋ እየሰጠ እኛን በቁም የሚያጠወልግ ድርጅት ነው። የዚህ ድርጅት አባላት ከኛው መካከል የወጡ ጥቂት እንጀራ ፈላጊዎች ሲሆኑ ከኢህአዲጎቹም ውስጥ ቃል አቀባይ አላቸው። ሌሎች በህቡእ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም እንዳሉ ይነገራል። ዲሞክራሲ በደንብ ስላልሰፈነ ገና ይፋ አልወጡም። መቼ ይሆን ግን ከዚህ ሁሉ ውዥንብር የምንገላገለው? እስካሁን ያሉን ነገር የለም።

## 22

ምንም ቢቸግረኝ አጥቼ ብነጣ፣
ሲጋራስ አልሸጥም ካገሬ ሳልወጣ፣
የትናንት መኮንን ተብየ አልጠራም፣ 'ጆብሎ ሲጋራ አምጣ!'

ጆብሎ መኮንኖች በካምፑ ውስጥ በስፋት ተንሰራፍተዋል። በየመንገዱ ዳር ለዳር የጉልት ገበያ ጀምረዋል። ሲጋራ፣ ቃሪያ፣ ነጭ ሽንኩርት መሸጥ ይዘዋል። እረ ነጭ ሽንኩርትስ መድረሻ አሳጥቶናል። ከውጭ ወደ መኝታ ክፍላችን ስንገባ የሽንኩርቱ ሽታ ወደ ውጭ መልሶ

ይገፈትራል:: ምግብ አዳራሽም እንዲሁ ስቃይ ነው:: ባጠቃላይ ቤት ደጁ ጠንብቷል:: ደግነቱ ሁሉም ስለሚበላ እንደ ነውር አልተቆጠረም:: «ሸተትከኝ» የሚልም የለም:: የማይወድ ቢኖርም በግዱ ፊቱን አጨፍግጎ ሁለት ፍሬዎችን መብላት አለበት:: የህይወት ጉዳይ ነው:: እሱ ካልተበላ ወባዎ አንድ ቀን አታሳድርም እሉ:: በዚህ የተነሳ ሁሉም ነጭ ሽንኩርት ይከስክሳል:: አንዳንዱ መኮንንማ አንድ ራስ ሽንኩርት ከስክሶ የሚጨርስ አለ:: እኔ ፈርዶብኝ እንኳን ልበላ ይቅርና ሲበሉ ሳይም ያንቀጠቅጠኛል:: እነ በድሉ ተቆጥተውኝ ለሁለት ቀናት ያህል ሁለት ሁለት ፍሬዎችን ከሸ ከሸ አድርጌ ነበር:: የገዛ አፌ ጠነባኝ:: ከዚህ በኋላ «ወባዎ እንዳሻት ታድርገኝ» ብዬ ተውኩት:: ካፍንጫቸው የሚወትፉትም አሉ:: የረጋ ንፍጥ መስሎ ተለጉዶ ሲያስጠላ:: ያ ሁሉ ትቢተኛ ኮለኔልና ሻለቃ ህይወቱን ለማቆየት የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም:: ጉድጓድ ብል ጉድጓድ ትዝ አለኝ::

ጠላይ ከገባን ጀምሮ ዋነኛ ስራችን ጉድጓድ መቆፈር ነው:: ለምን ግዙፍ ግዙፍ ጉድጓዶች እየቆፈርን እንደምናጠራቅም አልገባኝም:: ጥልቀት 2 ሜትር፣ የጎን ስፋት 2ሜትር፣ ርዝመት 8ሜትር የሆኑ በርካታ ጉድጓዶች በየሻለቃው እየተቆፈሩ ነው:: ዛሬስ ሰግተናል:: የኋላ ኋላ ለኛው ማዳፈኛ እንዳይሆኑ እንጂ::

ሌላው ስራችን በሳምንት አንድ ቀን የምግብ ማብሰያ እንጨት መልቀም ነው:: ጫካ እንሄድና የቻለ ግንድ ተሸክሞ ይመጣል:: ያልቻለ ጭራሮ አንከርፍፎ ይገባል:: ሻለቃ የለ ኮለኔል፤ እንደ መብሉ ስራውም እኩል ነው:: ስራችን በጉድጓድ ቁፋሮና በእንጨት ለቀማ ብቻ አያበቃም:: ምግባችንንም ተራ እየገባን በጥይት ሳጥን ተሸክመን ወደ መመገቢያ አዳራሾች የምናመጣው እኛው ነን:: የቦታው እርቀት ደግሞ ከማድ ቤት እስከ መመገቢያ አዳራሽ ያለ እርቀት አይደለም:: ከካምፑ ሶስት ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል:: የምግብ ሸክሙም ማእረግ አይለይም::

ባለፈው እሁድ ታዲያ ባህል አዳራሽ አጠገብ አንድ ትርኢት አየን:: ማእረጋቸው ሌ/ኮለኔል ነው:: አብሯቸው የተሸከመው መቶ አለቃ ነው:: እሱ ፊት ፊት፤ እሳቸው ከኋላ ናቸው:: እንጀራውን ተሸክመው ቱስ ቱስ እያሉ በዚያ ሲያልፉ ሚስት ካዲስ አበባ ባለቸውን ሊጠይቁ መጥተው ኖሮ ድንገት ግጥምጥም:: ሚትስ ሆየ ኡኡታቸውን መልቀቅ:: በዚህ ጊዜ ባል ሀፍረት ይይዛቸውና የተሸከሙትን ሳጥን አምዘግዝገው መጣል:: እስቲ ጓደኛቸውን እንኳን «ጣል መጣሌ ነው» ቢሉት ምነበር? ክፉኛ ነው ትከሻው የተጎዳው:: ከዚያማ ባልና ሚስት እንገት ላንገት ተቃቅፈው መላቀስ:: እኛ ደግሞ ድራማውን በነፃ መመልከት:: ከዚያማ አንድ መኮንን ሴትየዋን አስለቀቃቸውና:-

"ይተው እንጅ! ነውር ነው! የሞቱ መሰለዎት እንዴ!" ማለት::

" ምነው ሸዋ! ሞት ከዚህ ወዲያ አለ እንዴ! ሞትስ በቁርጡ ይሻላል!" ብለው በምሬት ተናገሩ:: በዚህ በዚህ ምክንያት እሮሮ ስላበዛን ነው መሰል ዛሬ እንጀራ ሸክሙ ቀርቶልናል:: ባንድ ትራክተር እየተጫነ በየሻለቃው የምግብ አዳራሽ እየዞረ ይታደላል::

ሆስታ ሳለን ደመወዝ ካልተሰጠን ሰንል የነበረው ጠላይ ከሄድን በኋላ ደግሞ መውጫ ቀዳዳ ፍለጋ ሆነ:; በቃ! የደመወዝ ነገር አከተመ::



# 23

በደርግም ስብሰባ፣
በኢህአዲግም ስብሰባ፣
ኧረ መቸ ይሆን ሰርተን የምንገባ?

ስብሰባ ቆይተን ገና አሁን መውጣታችን ነው:: የተሰበሰብነው በየሻለቃችን ነበር:: ስብሰባ አይበለው:: የነጭ ሽንኩርት ሽታ የምገባበት ነበር ያሳጣኝ:: አንድ ሻለቃ ጦር አንዳንድ ራስ ሽንኩርት በልቶ በዚህ ላይ ባፍንጫው ወትፎ የመጣው በርካታ ነው:: የትንፋሹ ግለት፣ ከበርሃው ሙቀት ጋር ተዳምሮ የት ልድረስ ያሰኛል:: መቼ ይኸ ብቻ!! መኮንኑ ከመቶ ዘጠና ዘጠኙ እጅ አጫሽ ነው:: እንደ ጃርት ታፍነን ሙተነው ነበር:: ጭሱ ሲግፈጠፈጥ ምጣድ የተጣደበት የገጠር ቤት ምስጋና ይንሳው:: በመስኮት በኩል እንኳ ንፁህ አየር እንዳይገባ ወንበር ስለማይበቃን መስኮቱን ከበው የሚቆሙት መኮንኖች ከዛፍ ላይ የሰፈረ ንብ ይመስላሉ:: አቅለሸለሸኝ:: ሊያስመልሰኝ ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር::

ኢህአዲጎቹም ስብሰባውን የሚመሩት እንደ መፋቂያ ሲጋራ ከከንፈራቸው ሰክተው ነው:: ይኸው ናቸው:: ሲያልቅባቸው ከዚያው ላይ መለኮስ ነው:: ትንሽ ፋታ የሚያገኙት በጃቸው እንደያዙት ሲናገሩ ብቻ ነው:: ደግሞኮ የኢህአዲግ አባል የሆነ ሁሉ የማያጨስ አላየሁም፣ ታዲያ የኛዎቹን መኮንኖች:-

"ለምንድን ነው አዳራሽ ውስጥ በስብሰባ ጊዜ የምታጨሱት?" ያልናቸው እንደ ሆነ:-

"ተመልከቱ ኢህአዲጎቹን፤ ደግሞ የዲሞክራሲ መብታችን ነው" ይሉናል:: ኧረ ዲሞክራሲ ግራ አጋብቶናል! ከትናንት ወዲያ አንድ መቶ አለቃ እንዲሁ በምሳ ሰአት ሲጋራ አቀጣጥሎ እያጨሰ ምሳውን በላስቲክ ሳህን ተቀብሎ ከኔ ጋር አንድ ጠረጴዛ ተጋራን:: ታዲያማ ሲጋራውን በግራ እጁ ያዝ አድርጎ በቀኝ እጁ እንጀራውን እየቆረሰ ሁለት ጊዜ ያህል ጎረሰና እንደ ገና ደግሞ ከሲጋራው ይምግ ጀመር::

"ጓድ መቶ አለቃ፣ ምግቡ ነው መቅደም ያለበት ሲጋራው?" አልኩት ጥርሶቼን ብልጭ አድርጌ::

"ሁለቱም የዲሞክራሲ መብቴ ነው" አለኝ:: ይድነቅህ አለና ወደኔ ጢሱን አቦነነብኝ:: ምን ላድርግ፤ ተናድጄ ምሳየን ሳልበላ ወጣሁኝ:: ይኸ ይሆን ዲሞክራሲ ማለት?

ትናንት ማታ ደግሞ አንዱ ያስም በሽተኛ "እባካችሁ ጓዶች ሲጋራ በተወሰነ ሰአት አጭሱ:: ቢቻልማ መኝታ ቤት ባታጨሱ ጥሩ ነበር" ብሎ ቢማፀን ከያቅጣጫው ተነሱበት:: ቡትቶ ጨርቅ ነው ያደረጉት:: ስሎ ዝም አለ:: ለካ እንደዚህ ምግባረ ብልሹዎች ኖረናል? በዚህ አይነትስ «የደርግ መኮንኖች» መባል ሲያንሰን ነው:: ባምሳሉ አድቦልቡሎን ኖሯል!

ዛሬ የተሰበሰብንበት ጉዳይ ግን ከሰሞኑ ለየት ያለ ነበር:: ስብሰባውን የመራው ታጋይ ሀጎስ ይባላል:: ለኛ ሻለቃ ላስተማሪነት የተመደበ ነው:: ባንድ ስብሰባ ላይ አይቸዋለሁ:: ሲናገር ትንታግ ነው::

ነገር ስጋውን አላምጦ ጨርሶታል:: በየሻለቃው የተመደቡት ታጋዮች በሙሉ አስተማሪዎች ተብለው ነው የሚጠሩት:: ምን እንደ ሚያስተምሩን ለብዙዎቻችን እንቆቅልሽ ነው የሆነብን:: ቢጨንቀኝ:-

"እነዚህ ታጋዮች አስተማሪ የሚባሉት ምንድን ነው የሚያስተምሩን?" ብዬ በድሉን ጠየኩት::

"ስለ መቶ አመት ታሪክና ስለዲሞክራሲ፣ ስለብሄር፣ ብሄረሰቦች መነጣጠል" ብሎ አሳቀኝ::

ታጋይ ሀጎስ ሲጋራውን ቡልቅ ቡልቅ አደረገና "ያው 'የድጋፍ ሰልፍ እንሰለፍ' ብላችሁ በጠየቃችሁት መሰረት እንድትሰለፉ ተፈቅዶላችኋል:: ስለዚህ በዛሬው እለት መፈክር የሚያዘጋጁ፣ የካርቱን ስእል የሚስሉና ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑ ሰዎችን ትመርጣላችሁ" ሲለን ጭጭ አልን:: ከሰሞኑ "እንሰለፍና እንገላገል፣ ደመወዛችንን የያዙት ሰልፍ ባለመሰለፋችን ነው" እየተባለ ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ ተደርጎ ሁላችንም ለመሰለፍ ተስማምተን ነበር::

"የተናገርኩት ለቤቱ ግልፅ አይደለም እንዴ?" ሲል ጠየቀ::

"ኧረ ግልፅ ነው" አሉት ከፊትለፊት የተቀመጡት::

"እንግዲያማ ተጨማሪ ሀሳብ ስጡበትማ" አለ:: ከዚያ ጠና ጠና ያሉ መኮንኖች እየተነሱ የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ እንደሚገባን በስፋት አስረዱ:: እኛም በመስማማት አጨበጨብን:: በዚሁ የሰልፉን አዘጋጅ ኮሚቴ መርጠን ኣዳራሽ ወጣን:: የሸንኩርቱ ሽታ ግን አሁንም አለቀቀኝ:: እንጃልኝ በዚህ ከቀጠለ አንድ ቀን ከስብሰባ ላይ ማስመለሴ የማይቀር ነው:: ኧረሱስ የኢህአዲግ ስራም ያስታውካል::

# ምእራፍ ዘጠኝ

በቀን ደክመን ደክመን እውነቱን ያጣነው፣
አሁን በጨለማው ለምን እንደክማለን ደስታን ላናገኘው?

## 24

«የቀድሞው መንግስት የጦር መኮንኖች እጃችንን ከተጨማለቀው ስርአት ለማንፃት ዝግጁ ነን!!"» ነገ ከምንይዛቸው መፈክሮች አንዱ ነበር:: ገና ከማታው ጀምሮ የዝግጅት ኮሚቴው መፈክሮችን ለየሻምበሉ ጦር አከፋፍሏል::

ካልጋየ ላይ ጋደም ብዬ መፈክሩን አትኩሬ እያየሁ በቁጭት ተጠበስኩኝ:: ፊቴ ተጨማዷል:: እንደኔው በየመኝታቸው ላይ ሆነው መፈክሩን አትኩረው እያዩ ፀጉራቸውን የሚነጩ ነበሩ:: ከናካቴው ምንም ያልገባቸውም ነበሩ:: ልክ በማግስቱ እንደሚሞሸሩ ሁሉ



ይጨፍሩ ነበር:: ምንፈቀዱኝ:: እነሱ የሚያኮርፉት ሆዳቸው ሲጎድልና ሲጋራ ሲያጡ ብቻ ነው::

"አፈር ይብሉና! የዝግጅት ኮሚቴ ተብዬዎች የመረጥናቸው እኛን የሚያዋርድ መፈክር እንዲያወጡ ነው እንዴ?!" አለ አዱኛ ደቻሳ:: ሙክ ብሎ ነበር የተናገረው::

"ቀስ በል!" አለው በድሉ ጫኔ ቆጣ ብሎ::

"ምኑን ቀስ እለዋለሁ! እነመንግስቱ ባጨማለቁት ስርአት እኛ ተጠያቂ እንሆናለን እንዴ!" አሁንም ቀስ ብሎ መናገር አልሆነለትም::

"ጤናም የለህ! ምናለ ዝም ብትል!" ደግሞ ተቆጣው::

"ለምን ዝም እላለሁ? ከዚህ የበለጠ ምን ይመጣል? እንዳህያ መፈክር አሸክመው ሊነዱን ነው!" አለ እንደ እልህ እየተናነቀው:: ለትንሽ ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና እየተንካኩ የሚስቁትን አፍጥጦ እያየ "እነዚህን መፈክር ማሸከም ብቻ ሳይሆን መድፍም ማስጎተት ነበር! አሁን ምኑ ደስ ብሏቸው ነው እንደ እንቁራሪቶቹ የሚያሽካኩት!" አለ:: ሳቃቸውን ቆም አድርገው ዘወር ዘወር እያሉ አዩት::

"አንተ ጤናም የለህ እንዴ!" ስል እኔም ተቆጣሁት:: ዳግመኛ ትንፍሽ አላለም፤ ተሸፋፍኖ ተኛ:: እኔም ተጠቅልየ ተኛሁ:: እንቅልፍ ግን አልሞከረኝም::

ከውጭ የእንቁራሪቶቹ እልልታ ይሰማኛል:: ደስታቸው ይችው ክረምት ነች:: ከዚያ ወዲያ ጭጭ ይሏታል:: ዛሬ ግን እልልታቸው መቁረጫ የለውም:: ቀንም፣ ሌትም ከኩሬ ኩሬ እየተዛለሉ ፍቅራቸውን ይጨርሳሉ:: የፍቅር መጨረሻ ትንሽ ኩሬ...

የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴዎች ጫት እየቃሙ ሲወጡ፣ ሲገቡ ነው ያነጉት:: ልክ ወጧ እንዳማረላት ሴት:: እኛንም የቀሰቀሱን ልክ አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ነው::

ሀምሌ 18 ቀን 1983 ዓ.ም. እለተ ሀሙስ ነው:: ጦላይ ከትናንት ጀምራ ብራ ናት:: የዛሬዋ እለትም ቁልጭ ያለች ቀን ነች:: ቁርሳችንን ከበላን በኋላ በየሻለቃችን ተሰለፍን:: መፈክሮች ይኸጎደጎዳሉ፤ የባህል ዘፈኖች ይቀልጣሉ:: የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በብዛት ይዘን እናውለበልባለን::በዚህ አጋጣሚ «ጨርቅነቷን» ሰርዘን ደምና አጥንት የተዋሀዳት መሆኗን ለማሳወቅ እየተቀባበልን በመያዝ ጉሯሯችን እስከሚነቃ እንጮሃለን:: ደግሞ የማንንም የድርጅት አርማ አልያዝንም:: የኛን ሻለቃ የሚመራው ሰልፈኛ የያዛት በራ ልታመልጥ ስትል የተያዘች የአንዲት ነጭ እርግብ ስእል የሚያሳይ ነው:: ትርጓሜውም «ሰላም ልታመልጠን ስትል ያዝናት» ማለት ነው:: ከኛ ኋላ የሚከተለን ሰልፈኛ ደግሞ 3ኛ ሻለቃ ነው:: እሱ የያዘው የካርቱን ስእል ደግሞ ሁላችንንም አስቆናል:: በውድድሩም አሸናፊ የሆነው ይኸው ሻለቃ ነው::

«አብዮታዊ መሪያችንን» የወታደር ልብስ አልብሰው ከሳሏቸው በኋላ ከወደ ግንጭላቸው በኩል ልክ የችምፓንዚ ግንጭል አስመስለውባቸው እግሮቻቸውን እንደ ሽረሪት እግሮች አቅጥነዋቸዋል:: ያጠለቁት ጫማ ደግሞ አካፋ ያክላል:: በቴሌቪዥን እንደሚታዮት የህፃናት ፊልም ነው ያስመሰሏቸው:: ካጠገባቸው ደግሞ ለመብረር

ያኮበኮበ ዳሽ ፋይፍ አይሮፕላን አለ:: ብር ያጨቁበትን ቦርሳ አንጠልጥለው ወደሱ የሚሮጡ ይመስላሉ:: ከካርቱን ስእሉ ግርጌ የተፃፉት መፈክሮች:-

«ትንሽ ትንሽ እንድማ! አንድ ሰውና አንድ መሳሪያ እስከሚቀረኝ ድረስ እዋጋለሁኝ» የሚል ነው:: ሰልፈኛው ያሰማው የነበረው መፈክር ደግሞ:-

«የዝምባብዌ መንግስትና ህዝብ ፈርጣጩንና ፋሽስቱን መንግስቱ ሀይለማርያምን ለኢትዮጵያ ህዝብ አሳልፎ መስጠት አለበት! የሀገርን ሀብት የዘረፉ ባስቸኳይ ለፍርድ ይቅረቡ!» የሚል ነው::

ተጥመልምለን የባህል አዳራሽን እንዳለፍን ጋዜጠኞች ፎቶ ለማንሳት፣ በቴሌቪዥን ለመቅረፅ ይሯሯጡ ጀመር:: ልክ ጣላይ አደባባይ ስንደርስ ቦታ ቦታችንን ይዘን ቆምን:: ይዘናቸው ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ:-

- የብሄሮችና የብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት የዲሞክራሲ መብት ነው!
- ኢህአዲግ የሰላምና የዲሞክራሲ ዋስትና ነው!
- ህዝባችን የተጠማውን ሰላም ያግኝ!
- የሰላምና የዲሞክራሲ ኮንፈረንስ የኢትዮጵያ ህዝብ ምጥ የወለደው ነው!
- የተጎሳቆለችውን አገራችንን መልሰን እንገነባለን!
- የህዝቡ የበላይነት ይከበራል! የሚሉ ናቸው::

የክብር እንግዶች መጥተው ቦታቸውን እንደ ያዙ የሰልፉ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የመግቢያ ንግግር አድርገው ፕሮግራሙን ለሚመራው መኮንን ለቀቁለት:: ከዚህ በኋላ በተከታታይ ሶስት ግጥሞች ተነበቡ:: ሁሉም ግጥሞች ከብሶት የመነጩ ነበሩ:: አቅራቢዎቹም ወጣት መኮንኖች ናቸው:: ከጨለማ ህይወት ላይ መውደቃቸውን ግጥሞቻቸው ይጠቁማሉ:: ተስፋን እያጭሩም! ያስቆዝማሉ እንጅ::

ሁሉም ነገር ተብሎ ካበቃ በኋላ የማእከሉ ሀላፊ ንግግር ለማድረግ ሲነሱ ለክብራቸው ርችት ተተኮሰላቸው:: ወዲያው እርጭ ሲል መናገር ጀመሩ:: ባማረኛ ነበር የተናገሩት:: መነፀር አድርገዋል:: የቀይ ዳማ ናቸው::

"... ወደፊት በዚህ ማእከል ውስጥ ላጭር ጊዜ በምትቆዩበት ወቅት ጥሩ ጥሩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ ብለን እንገምታለን..." በቃ ይኸው ነው:: ሌላው ስለሽግግር መንግስቱ፣ ስለቻርተሩ አላማ ነው:: ይኸ ደግሞ ምናችንም አይደል:: በዚሁ የሰልፉ ፍፃሜ ሆነ::

ይች "አጭር ጊዜ ቆይታ" የምትለዋ አባባል የሁላችንንም ጭንቅላት በጥብጠዋለች:: ለሶስት ቀናት ሴሚናር ተብለን ሆለታ ገብተን ይኸውና ሶስተኛ ወራችንን ይዘናል:: ይች አጭር ጊዜ ደግሞ ትረዝም ይሆን?



# 25

ጉድ አይመጣ የለም እያደር ጉድ መጣ፣
«እመኑ» ተባልነ እምነን ብንመጣ::

ሌሊቱን ሲዘንብ ነው ያደረው:: ከንጋም በኋላ ካፊያ ቢጤ ነበር:: እየቆየ ግን ፈተት እያለ መጣ:: የጣላይ ያየር ፀባይ ይኸው ነው:: ይዘንብና ወዲያው ፀሀይ ትወጣለች:: ከዚያ ደግሞ ጭቃው ምጥጥ ይላል:: ታዲያ ይኸ የዋልካ ጭቃ ስንረግጠው እንደ ካትራሚ ንክስ ንክስ ያደርግና ወዲያው ተተምትሞ ሀስፋልት ሆኖ ቁጭ ያላል:: ሲዘንብ ደግሞ ሙልጭልጭ ይልና አፍርጦ ይጥላል:: ዛሬስ አፍርጦ የጣለን የኢህአዲግ ነገር ነው:: እያደር ከበደን፤ ሰልፍ ተሰልፈን እንጀቱን እናራራለን ብለን ነበር፤ እሱ ግን ሸቦ እንጀት ሆነ:: እንደ ኮራን ብንቀመጥ ይሻለን ነበር:: በመሰለፋችን ያላሱብነውን መዘዝ መዘዙብን:: አውቀነዋል፤ አጭሯን ጊዜ ለማስረዘም ነው::

ዛሬ ስብሰባ እንደ ምናደርግ የተነገረን ማታ ነበር:: ያው እንደ ሁልጊዜው በየሻለቃችን ነው የተሰበሰብነው:: አዳራሹ ጢም ብሎ ሞልቶ የመስኮቱ ዙሪያ እንደ አጥር ክርችም ብሏል::

የነጭ ሽንኩርት ሽታ አንጀት ያማስላል፤ አፍንጫን ይቆርጣል:: ሲዘንብ ስላደረ ነው መሰል የሙቀቱ መጠን ቀነስ ያለ ነው:: የሲጋራው ጭስ ግን የማርፈጃውን ጉም ተክቶ ወደ ኮርኒሱ ይበናል:: ተጠራቅሞ ካፊያ እንዳይሆን እንጅ...

ታጋይ ሀጎስ ጉሮሮውን ጠራረገና "ዛሬ የተሰበተብንበት ምክንያት ባለፈው ያካሄድነውን ሰልፍ ለመገምገም ሲሆን ዋናው ትኩረታችን ግን 'የበደልነውን ህዝብ መልሰን እንክሳለን!' የሚለውን መፈክር ሳትይዙ በመቅረታችሁ ሰልፉ የተሟላና ከልብ ነበር ለማለት አንችልም:: ስለዚህ ዛሬ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተወያይተን የዚህን መፈክር ፅንስ ሀሳብ ተረድታችሁና አምናችሁ ካወጣችሁት ያቋም መግለጫ ጋር ተጨምሮ ይተላለፋል" ሲል አብራራልን:: ለካም ያቋም መግለጫው በሬዲዮ ያልተላለፈው ለዚህ ነው:: ቤቱ በግለት እጁን አወጣ:: ላንድ ሻምበል እድል ሰጠው::

"በመጀመሪያ ለምጠይቅህ ጥያቄ ተገቢ መልስ ስጠኝ፣ ለመሆኑ ሰልፉ የኢህአዲግ ነው የኛ?" ሲል ጠየቀው::

"ሰልፉ የኢህአዲግ አይደለም፤ የናንተ ነው:: ሆኖም ግን የመቆጣጠር ሀላፊነት አለብን" ሲል መለሰለት::

"በመቆጣጠሩ በኩል ያላችሁን ድርሻ እኛም እንቀበለዋለን:: ሰልፉን ግን የጠየቅነው እኛ እስከሆንን ድረስ የምንይዘውንም መፈክር መወሰን ያለብን እኛ ነን:: በርግጥ እናንተን የሚፃረር መፈክር እንዳንይዝ መከልከል ትችላላችሁ:: ይህም ቢሆን የዲሞክራሲን መርህ ይፃረራል:: ነገር ግን እናንተ የምትፈልጉትን መፈክር እንዴት እንሸከማለን?" በማለት ተናግሮ ተቀመጠ:: በርካታ መኮንኖች ደግሞ እጃቸውን አወጡ:: ሀጎስ ለማንኛውም እድል ሳይሰጥ እራሱ:-